ሙሉጌታ ተስፋዬ

# የባለቅኔ ምህላ

©
በፅሁፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የስነ-ፅሑፍና ኪነ-ጥበብ ሥራዎች ባለመብትነትን በተመለከተ ከአንቀፅ 1647 እስከ አንቀፅ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመፅሐፉ አንድ አንቀፅ እንኳን መልሶ ማሳተም፤ መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሰራጨት አይፈቀድም፡፡

የመጀመሪያ ህትመት 2003 ዓ.ም

የኮምፒዩተር ፅሑፍ ዮርዳኖስ ሀብተስላሴ
ሌይአውት ዲዛይን አሸናፊ ጌታቸው

ISBN 978–99944–824–2–9

ስንዱ መፃሕፍት
Sinedu Books

ስንዱ አበበ አሳታሚ
SINEDU ABEBE PUBLISHING HOUSE
ፖስታ 21728 ኮድ 1000
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
sendab37@yahoo.com

# አመስግኗቸው

- ዮርዳኖስ ሀብተስላሴ ለዚህ መፅሐፍ ዝግጅት የነበረሽን ትጋትና ትህትና በልጆችሽ ተደስተሽ አግኝው::

- ለዣ ሚሼል ኮርኒዮ

JEAN-MICHEL CORNU DE LENCLOS የዚህን መፅሐፍ ህትመት በግማሹ ባታግዘኝ ከነብስጭቴ ሕይወትን ልገፋ እገደድ ነበር::

- አሹዬ (አሸናፊ ጌታቸው) እናም ታጊ (ገጣሚ ታገል ሰይፉ) ምን ያህል ጥሩና ቅን ሰዎች ናቸው- አንባቢያን በገጣሚውና በአሳታሚዋ ስም አመስግኗቸው::

ስንዱ አበበ

«አስቀድሞ ቃል ነበረ፣ ቃልም ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ።»
የዮሃንስ ወንጌል

# የተረገመው ባለቅኔ

ስብሐት ለአብ ገብረእግዚአብሔር

የተነሳሁት ውስጤ ስለሚኖረው ሙሉጌታ ተስፋዬ በዚህ ድንቅ አጋጣሚ ለመመስከር ስለሆነ፣ በኔ ዓለም ውስጥ በገጣሚነቱ ብቸኛ እኩያው ስለሆነው ስለዊልያም ሼክስፒር በመናገር ልጀምርላችሁ። ስሜቴን ብቻ!

ለመዝናናት ለመደሰት ጊዜ አግኝቼ ሳነበው፣ ድሮ የፃፈው ሼክስፒርና አሁን የማነበው እኔ ተዋህደን ያሁኗን ሰዓቴን የግል ገነት እንፈጥራለን። «ገነት» ስል ህይወትን ከነማሯ ከነሬትዋ ማጣጣም ማለቴ ነው - እና ከነእንባዋ ከነሳቋ! ከነምስቅልቅል ድንብርብሯ!

አንባቢ ሆኜ ሳየው፣ ሼክስፒር የእንግሊዝኛ ልሳን ያስተማረኝን እድል ደጋግሜ ለማመስገን አብቅቶኛል። በነገራችን ላይ፣ እንግሊዞች ሼክስፒራቸውን የሚመጥን ቅፅል፣ ሹመት ወይም ማሞገስ ቢያጡ The Bard (አዝማሪው) አሉት። ስነ-ግጥሞቹ (በድራማዎቹ ውስጥም እንኳ) እንደ ሙዚቃ ስለሚጥሙ!

ስለሙሉጌታ ግጥሞች እኛ ዘወትር የምናነበው ያገሩ ልጆች ይህን ከላይ የፃፍኩትን ብንመሰክረው፣ ብንጮኸው፣ ብናስተጋባው ሲያንሰው ነው። አንዷን ግጥሙን ብናነብለት ይሆን ነበር የሱ ምርጫ፣ አሁን ግድ አይኖረውም እንጂ (ኧረ በህይወት በነበረበት ጊዜም ቢሆን ግድ የለውም ነበር ...) እኛ ነን ያንጊዜም አሁንም ግድ የሚሰጠን። እሱ ተነሳበት፣ ፃፈ፣ በቃ። እዚያው እፃፈበት ቦታ ረስቶት ወይም አውቆ ትቶት ሊሄድ ይችላል።

ስንዱ (እሱ በወሎ ባህላቸው «ጉኖዬ!» ብሎ የሚያቆላምጣት) ባትሰበስባቸው ኖሮ ተበታትነው ይቀሩ ነበር። ባመሰግናት አሳንሳታለሁ። ምክንያቱም እሷ ሰብስባ ያሳተመችልን የገዛ አድናቆቷ ስለፈነቀላት ብቻ በመሆኑ።

የግሌን ሼክስፒር ላስታውሳችሁና፣ የስነ-ቃል ጥበቡ ከሱ እኩል የተለየ እንቁ ባለቅኔ በገዛ አገሬ በቅሎ «በግምባር አገኘሁት!» ሙሉጌታን ስንዱ ቤት ነው የተዋወቅኩት ... ከሷ ቤት ውጭም አግኝቼው አላውቅም። ለዚያውም አንድ ዘጠኝ ጊዜ ያህል ቢሆን ነው። ለኔ በቂዬ ነበር።

ባሁኑ ጊዜ የግጥም ስብስብ በየወሩ ሁለት ይታተማል ይሉናል አሳታሚዎች። ግጥም እንደ በረዶ ከሰማይ በinspiration ይንጠባጠባል እንበልና፣ የሙሌክስ ግጥሞች እንደ እንቁ እያንፀባረቁ፣ በትውስታችን ውስጥ ዘላቂ ናቸው።

ለተነሳሁበት ጉዳይ ይሄ ይብቃንና፣ ታትሞ ደርሷችሁ ካነበባችሁት በኋላ፣ ገጣሚው እንዴት፣ መቼ፣ በምን ድባብ ውስጥ እንደሚፅፍ ልዘረዝርላችሁ እችላለሁ። ነቄ ቲፎዞ ሆኜ ስላስተዋልኩት በሌላ በኩል ስናያቸው ግን ሼክ'ና ሙሌ የዘመናቸውን ያህል ይራራቃሉ። ሼክስፒርን የሚወደውና የሚያደንቀው ጓደኛው (Ben Jonson ፀሀፌ-ተውኔትና ባለቅኔ) ባሁን አማርኛ ልተርጉምላችሁና «የኔ ሼክስፒርዬ፣ ምሁርነቱ ትንሽ Latin እና ሚጢጢዬ Greek ቢሆንም፣ መላውን ዓለምና የሰውን ልብ የሚያውቅ» ይላል።

ሙሉጌታ ግን ከቅዳሴ እስከ ቅኔ ከዛም ተሻግሮ ቁርአን፣ ሀዲስንና መንዙማን የሚያውቅ ምሁር ነው። ይህም ባንዳንዶች ግጥሞቹ ውስጥ ይታያል። እግዜርንም ሽይጣንንም በእኩል ንቀት እየገረመመ ሲያናግራቸው እንደ ዳኛ ነው። ምንም ምክንያት ሳላገኝለት እውስጤ የሰረፀ ጥርጣሬ አለኝ። በሞተበት ቦታና ሰዓት ከሰይጣን ጋር እየተፋጠጠ እየተናነቀ ነበር ይሆን?

እዝጌርም ሰይጣንም የለም የሚሉ አንባብያን ካሉ፣ እዝጌርም ሰይጣኑም የመሰሉት የራሱ ህሊና የፈጠረቻቸው ህልም ወይም ቅዠት ናት በሉ። ሌላ ማለት ብትፈልጉም መብታችሁ በህገ-መንግስቱ የተጠበቀ ነው።

፳፻፪ ዓ.ም

# ማውጫ


1. ብርዕ በደም ዕንባ! .................................................. 1
2. እነሆ .................................................. 2
3. እንሆ .................................................. 5
4. ትንቢተ ትጉሓን .................................................. 8
5. እውነት ከመንበርህ የለህማ! .................................................. 11
6. መስፍኔ .................................................. 16
7. ተንጋላ የሞተችውን የመንታ እናት ጣር አየሁት .................................................. 19
8. ዋጋ እንዴት ልጠይቅ? .................................................. 24
9. አለዚያ ወደዚያ .................................................. 25
10. የቀረንን እንጫወት .................................................. 28
11. እነሆ...ገድ! .................................................. 31
12. ከሰው መርጦ ለሹመት .................................................. 34
13. አስምአኒ .................................................. 37
14. የማረሻው ሹም ሽር .................................................. 40
15. ግዝመ ሥውር መሬት .................................................. 49
16. ውድነሽ በጣሙ .................................................. 52
17. እንደሰዶም .................................................. 58
18. ሹመት .................................................. 60
19. ከናፈቅኩህ በቃኝ .................................................. 61
20. ከወሎ ልጅ ውሎ .................................................. 62
21. ምንም ነኝ ግን አማራ .................................................. 63
22. አዲስ ዓመት .................................................. 67
23. ግሼ ዓባይ ግዮን ... .................................................. 68
24. እኔ መዩ .................................................. 69
25. አክሱም ... የብቃት ስም .................................................. 72
26. ከህሊና ልምሻ የዕምነት ክትባት ይሻል .................................................. 75
27. የካህን ሱባዔ .................................................. 76
28. ሃበሻነት ምንድን ነው? .................................................. 77
29. ድስቱር .................................................. 80
30. የጎራው ወይራ ዝየራ .................................................. 83
31. ከነዓን ነው ዘንድሮ .................................................. 84
32. «መጽሀፈ ጥበብ» .................................................. 87
33. የናት ልጅ ወንድሜን .................................................. 91
34. «ጥበበኛውን አለማወቅ ገደለው» .................................................. 93
35. የምስራች ተበሰረ .................................................. 95
36. እምጽዋይሽ ሐረር .................................................. 96

37. ጌታ ሆይ … ነፍሴን ባርካት ..................................... 98
38. ኩኩሉ … አለ «ዲበኩሉ» ........................................... 101
39. ወደሚቀጥለው ......................................................... 102
40. አዎ ባላገር ነኝ ......................................................... 103
41. እንደቸርነትህ ......................................................... 104
42. እልልል … እልልታ ................................................ 105
43. ቃል ........................................................................... 106
44. የጥምቀት ጨረቃ ..................................................... 107
45. ካየኸው በላይ ማን ይነግርሃል? ................................. 108
46. እሷና እኔ ................................................................ 110
47. አንድምታ ................................................................ 117
48. የእምዬ … የልደት ስጦታ ........................................ 123
49. ምነው አንተ ሙሽር .................................................. 125
50. እግዚኦ ....................................................................... 127
51. የባለቅኔ ምህላ! ......................................................... 128

# ብርዕ - በደም ዕንባ!

በኔው 'ኔ ጥራና
በኔው 'ኔ ብራና
ባፅሜ ቀሰም ብርዕ
    በህይወት ማቅለሚያው
        ጠርቤ ስለቁጥ
የኑሮን ሽቁጥቁጥ
የራሴ ጉልቻ ... አንገቴ አለ ዘምበል
የደም ወዜ ጠለል ... እንባዬ አለ ከምበል
በሞት ሞት ጣረሞት ... «በልቤ ልብ በል!»

ሥጋት እንደውጋት
ነፍሴን ሲሰንጋት
በቅኔ እንቆቅልሽ ... ቁልቁል ተቆልፌ
በእምነት ... እምም እመ-እዝነት
በህልም ዓለም ሽምጥ ግልቢያ ተሰልፌ
        ለሥጋ ታርቄ
        ለገላ መርቄ
        እርቃኔን ወጥቼ - ግብኔን አስጥቼ
        የጎኔን ጨረስኩት - ሆዴን ስሸነግል
        ለነገ ራሴ ስንቅ - ለቋንጣዬ አገልግል::

ካምና ከታች አምናው
የጉልበት የጤናው
ቢታይ ሁለንተናው - «ሁሉ» ሁለመናው
የልቤ ልብ በል - ለልቤ ሲጠናው
ብቻ ላይኔ ብቻ - ላይኔ ለብረቱ - ላይኔ ብቻ ቀናው!
ለታይታ ለዝናው ...
በሰው ፊት በሸንጐ ለወግ ማ'ረግ ዝናው!!

        አዎ!   በኔው 'ኔ ጥራና
        በኔው 'ኔ ብራና
        በብርዬ ስለቁጥ
        የኑሮን ሽቁጥቁጥ
ደም እንባ - ደም እንባ - እንበለ እንባ ደም
ሕይወት እንጉርጉሮ - በአታሞ አይታደም::

(ለሚነቁኝ - ለማያውቁኝ)

29/7/84

# እነሆ

እነሆ መንገዱ ተከፈተ ...
አራስ ልጅ ፈነደቀ ... ወላድ ተንከተከተ...
ሳቅ በሳቅ ሆነ አገሩ ...
ለማረሻ ሊውል ነው ዘገሩ ...
ለነገሩ ... ነገር ካለውም ነገሩ
ሰንኮፉ ካልተነቀለ ...
ዘለዓለም ሲያለቅስ አይኖርም
            ቁልቋል እሾህ በሥሩ ከበቀለ ...

እነሆ መንገዱ ተከፈተ ...
ጆሮም እየሰማ ሊያድር - ዓይን እየተመለከተ
                    - ክንድም እየመከተ
እንግዲህ ዛሬም ተራው የኛው ነው
ያገር ልጅ እንዳክምባሎ
ቁልቁል በራብ ተተክሎ
            ምኑን አስችሎን ተኛነው ...
የላካችሁልን ስንቅ አነቀን ...
ውለታችሁ አስጨነቀን ...
ደሞ አምሮባችሁ ... በቀያችሁ
            አብረን ስንፈነድቅ ማየት ናፈቀን ...

እነሆ መንገዱ ተከፈተ ...
ፍንትው ብሎ ይታያል ፀዳሉ ...
ያገር ልጅ ሥጋጃ አንጥፎ ...
            እፎይ ሲል በድልዳሉ ...
እዬዬም ባይገድ ሲዳሉ ...

እነሆ መንገዱ ተከፈተ ...
በመስኬቶ ጠላት እንደነዶ ከምሮ
            እንደ ላዳ ሬጠስ አንበሳ ...
ደም ምድር በማረሻ እየበሳ ...
በፍቅር ሊያይ አበሳ ...

ሰማይ ጠቅሶ እንደንስር
            ባንዳ ይርበደበድ የዳመና ካባ ተከናንቦ
አሁን ደሞ በጠራው ሰማይ
            በኪነ ጥበቡ የሰላም ዝናብ አዝንቦ ...

አዝመራው ጣል ከምበል ሲል
ፎጢ.ማውና ዋሽንቱን እየተሰለቀ
ለቃ አምባሰልን
ወጣሁ ሲል ...
አቀበቱን ቢያሽሟጥጡት ...
የፈረስን ልክ ባናውቅም
ሰው ሲወጣበት
ምን ሊያጡት
ሥርዓት ያስተማረውን ሕዝብ ...
ሰልፉን ሳያሳምር ...
በምን አቅሙ በተጠንቀቅ ቁሞ ...
በሰንደቁ ፊት ሊዘምር
የገባውን ሳያስተምር ...
የበደለውን ሳይምር

እጅ ነሳን ኢትዮጵያውያን ፊት ...
ላባት ጋሻ ለናት ወንፊት
ላገር ክብር - ለልጅ ትውፊት
ስሞታ መንገር የወንድም ባይሆን ...
በናታችን ሴት ነንና
ለናት ልጅ ሲያወጉት
ነውር የለውም ...
ዛሬን በትላንትና ...

ከጠላት በላይ ያቆሰለን ...
የኛው ጉጥ ነው እኛን የመሰለን
በባዕድ ጉርሻ ተደልሎ ... 9 ለሁለት እያወጋ ...
ጉያችን ሥር (ተጠልሎ) ተቀምጦ -
ጡት ሥራችንን የወጋ ...
ዕድሜ ለደጀኑ ሕዝብ እኛስ ተወጣነው እንደምንም
ከዚህ በኋላ ግን ደም አላርፍ ብለው ቢያሳክኑ...
የሚሆነውን እኛ አናምንም
ስንነግረው ያልሰማውን ቆስቁሰን አሰፋንበት ...
ለቀላዋጭ አፍጣጭ ደሞ... ምሱን አሷረፍነውና ...
ያላመጠውን እስኪውጥ
ካይነ ልቦናው ጠፋንበት

መሐል ቤትም ለሰፈረ
በኢትዮጵያዊነት ስም በራሱ
ነውር ላፈረ...
ይብላኝ ለሱ ... ፀፀቱ ምሱ

እነሆ መንገዱ ተከተፈ ...
እነሆ ትንሳዔ ባተ ...
ሕዝብ ቁና ባይሰሉም
              እንዳምላክ ...
ዓይን አለውና የሊላክ ...
ባይጥልም ካነጣጠረ ...
ቢያምንም ከጠረጠረ ...
ከሁለት አንዱ ዕድሜው ካላጠረ ...
አገሩስ ምን አገር ሊሆን ...
    ሰው አቻውን ካልፈጠረ።

የንጉሥ ዳዊት የገና ስጦታ ...

# እንሆ ...

እንሆ በረከት ... እንሆ መለከት
ደሞ ለመመከት ...
ምን ገዶ ...?
እንሆ ፈረሱ ...እንሆለት ሜዳው
ሁሉም እንደ ህልሙ ...
እንደጥሙ ይቅዳው!
ሁሉም እንደታየው ... እንዳስመለከተው
እንዳቅሙ ይከንዳው
ሁሉም እንደመሻው ... እንዲመቸው አርጎ
በወግ ያሰናዳው
ምን ገዶ ...

እንሆ በረከት ...
እንሆ ጥንድ አይንህ ... እንሆተ ዕዝን
ነፍስህ ፊት አቁሞ ... የልብህ ሲመዘን
እንሆ ማስተዋል ... እንሆልህ ማድመጥ
እጅ እግር አጣጥፎ ... ቅልውጥ ከመቋመጥ
እንሆ ሥርዓቱ እንሆ ብልሃቱ ...
ይኸን ማስማማት ነው ... የኑሮ ምትሐቱ ...
ምን ገዶ ... ?

እንሆ በረከት
እንሆ ዝናሩ ... እንሆ ዲናሩ ...
ለጨው ለበርበሬው ... ለውሎ ላዳሩ ...
እንሆ ሽሽቱ ... እንሆ መሻቱ ...
ለጥበብ ራዕይ ... ለዕድሜ መልካም ጠረን
ለዘለዕለም ሽቱ ...

እንሆ በረከት ...
ምን ገዶ ...
እንሆ እልፍኙ ... ያሳብ ቆሎ እፍኙ
እንሆልህ ሜዳው ... እንሆ ልማዱ ...
እሱን ካልታከተው ... ችሎ ከመከተው
ያውለት ጥማዱ ...

ያራስ ቤት አንጀቱ ... እንሆ ማጀቱ ...
ባንድ እንደመብላቱ ... አብሮ ለማርጀቱ ...

እንሆ በረከት ...
ምን ገዶ ...
እንሆ ምንጣፉ ... እንሆ መጣፉ ...
ያባዙትን ሂሳብ ... አካፍለው ሊያጣፉ
እንሆ ወራቱ ... እንሆ ጅረቱ ...
ኃጡና በረቱ ...
የልባም ቤት ድባብ ... ያ ነው መሰረቱ
እንሆልህ ማተብ ... እንሆ ኪታቡ ...
አንገት ራስ ሲችል ... ያንጀት ሲታተቡ ...
እንሆ መላ ምት ... ደሞ እንሆ ግምት
ዋልጌም እንዳያፍር ... ነውሩን እስኪሸምት
እንሆልህ ትጋት ... እንሆልህ ንጋት ...
ብትችል ፈልጋት ...
ያንለት ይሞታሉ ... ፍርሃትና ሥጋት ...
ምን ገዶ ...

ደሞ አለ መለከት ...
ተመልከት
እንሆልህ ቁንጣን ... እነሆልህ ሥልጣን
ከጉድ አውጣን ስንል ... በጉድ የሚያወጣን
እንሆ ማረሻው ... ሞት ምሬት ማስረሻው
እንሆ ሲምቢሮ
ያሳብ ቢራቢሮ ...
የሳት ዳር ጨዋታ የመደብ ግብ ግብ
እጅም ሰብሰብ እንዲል ... ምላስም እንዲያድብ
እንሆ ግሸ አባይ ... ያባት ዙፋን ጉባይ
ምንም ለፍቅር ያድራል ... ከያዙት በፀባይ

እንሆልህ ዳሽን ... እንሆ ነጭ ሣር
ሲወድ እንደስንድድ ... ሲጠላ እንደምሳር
ይኸን ካልፈታልህ ... ያሳይሃል አሳር

እንሆ በረከት ...
ምን ገዶ ...?
እንሆልህ ጋሻህ ... እንሆልህ ዋስህ
ወይ ግዳይ መጣያህ ... ወይ
ቅሌት ማፈሻህ
ምን ጊዜም ያንተው ነው
የኔ ያልከው ድርሻህ
ለዚያውም ባድራሻህ

እንሆ ሞባይል እንሆ ካዲላክ
አንተ ተቀምጠህ ... እሱ ቆሞ እሚላክ
ምን ገዶ ...?
ሁሉን እንሆተ ... እንሆተ ሁሉን
የሰው ሞኝ የለውም ... ሲገልጥለት ውሉን
እንሆተ ዓመል ... እንሆተ ሽመል
አንድም ለመሞሸር ...
አንድም ለመጥመልመል
ብሎም ለመገመል!
እነሆ በረከት ... እነሆ መለከት
ይለኛል መለኮት ... በህሊና መስኮት ...
የናንተን አላውቅም
የኔን የፈንታዬን ... ድርሻዬን ልመልከት

በገብርኤል ማግሥት
ታኅሣስ ፴፭

# ዘመነ ሱታፌ - ሓሌታ
# ትንቢተ ትጉሓን ...

ወዳጅ እስኪዛመድ ... ጠላት እስኪላመድ ...
ገስጋሽ እስኪራመድ ... ንፉግ እስኪጠመድ ...
ባለቤቱ ሲያፍር ... ቀላዋጭ ሲያጋፍር ...
እጁን በደም ነክሮ ... ወጪት ሲፈረፍር ...
ሰማዕት እልፍ ምዕት ካይን ቅንድብ ርቆ ...
በድን አንጠባርቆ ...
ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል ...
ተከድኖ ማየት ነው ... ተጥዶ ሲበስል ...
ዘመነ ሱታፌ ሓሌታ
ትንቢተ ትጉሃን ...
ንጋት ጎህ ቀደደ ... ፈነጠቀ ብርሃን ...
ንቁ እየፈቀቀ ...
የደበተው ሁሉ የትም በባረቀ ...
በተፈራረቀ ...
ያባ ቢላዋ ልጅ ፍንትው እንደጀምበር ...
በእልፍኝ በር ባኅበር ...
ምስጢር ቁጥር ፈቶ ... ከዘመን ተጋፍቶ
ዓይን ልቦናውን ፍንትው አርጎ ከፍቶ
አሳየን ፀዳሉን ...
እኛም እንዳሰብነው እነሱም እንዳሉን
ሳይሆን ብናገኘው ... እልል በቅምጤ ...
ለዚያም ለዚህ ሳልል ... ለዚያውም በድምጤ
ዘመነ ሱታፌ ሓሌታ
ትንቢተ ትጉሃን ...
ልጅ ከናቱ ታርቆ ... ማርያም ቅብቅብ ጠሞ
ታየች እመብርሃን ...
የዘመነ ሉቃስ ንግር ሲፈለፈል ...
ለካ ሰው ጥንድ ነው ... ያንድ ራስ መንትያ ...
አንድ ነው ሲካፈል ...
መጣ ብላቴና ...
ሥር ውልዱ «ካቴና ...»
ረጥቦ ጎማምዶ ተራምዶ እሚሻገር ...
ያገር ካስማ ማገር ...
ነውር ነው ብለን ነው በሞኝ ፊት መናገር

እንጂ ... ልቡ ለሰማ ሰው
ምን ያደርግለታል ... ቅኔ ቤት ሰዋሰው
እንደረኛ ኳሳ ነፍሱን ከለበሰው ...
ቃሉ ከተዋሰው ...
ዘመነ ሱታፌ ...
ትንቢተ ትጉሓን ...
ንጋት ጎህ ቀደደ ... ተገለጠ ብርሃን ...
ፍቅር ጎጆ ወጣ ...
ጥልን የሚበጥስ የዕምነት ሾተል ስለት
ካፎቱ ተመዞ ... እያቅራራ መጣ ...
አለኝ ያሉት ሁሉ ... ሁሉም እጁን ሰጣ
ሰው ሆኖ የኖረው ... እጁን እንዳወጣ
ሁሉም እህ እያሉት ያኔ እየተሰማ
ያልጣዱት ሞጌጐ ... ጋግሩብኝ ሲል ሰማ
አቅሉን የሳተውን ልቡን መልሶለት ...
ብግን ያረገውን መለኮት ልሣለት ...
ራዕይ ሰልሦለት ...
ላገር እድር በቅቶ ...
ዘብ ይቆማል ነቅቶ ...
ማጹ ተረግርጎ ... በላተኛ ሲያድም
እህል እህል ብሎ ... የሞተውን ወንድም
ያኔ እያስታወሱ ... ሳግ ካልዘጋ በቀር
ምኑ ይጠየቃል ...
ለሞተው እንጀራ ... ከናኘበት ማፍቀር
ክስና ፍርድ ቤት
ወረዱ ወህኒ ቤት ...
ዳኛውስ ምን ዳኛ ... በጨው በበርበሬ
ችሎቱስ ምን ችሎት ... በገባር በበሬ
በቃ ሸኘናቸው ...
ያ የሚያምኑት አንቀጽ ...
ህጉ ይሁናቸው
ስደት አደብ ቀርቶ ...
ኳሮ ተሰማራ ... እሱም መስቀል አርጎ ...
በማተብ አውሎ ... ዙሮ እሚያይበት ላይ
አስራ እንደማማ ነውር ከፈን አጥቶ ...
ሞት እያጣጣረው ብናይ ባደባባይ...
አልታደምንም እኛ ለሸንጎ ለጉባይ ...
ሥጋ ተሸክሞ መቃብር ከመውረድ
እንደቄራ ሰንጋ ይሻላል መታረድ ...
የነፍሳችን ምንዳ ሰማይ አረብቦ
የምን ጎንበስ ቀና ለቂጣና ለርቦ

ዘመነ ሱታፌ ሓሌታ
ትንቢተ ትጉሓን …
ሰነፍ አረፍቆ እንቅልፉን ይጥገበው
የነቃው ይበቃል … ቃሉን ያነገበው …
እንዲህ ነው እንዲህ ነው እንዲህ ነው
ለየለት …
ወዬ ግን ወዬ ግን ወዬ
ለወዬለት …

ስዕድሜ ትውፌት
ጳጉሜ 5/94

# እውነት ከመንበርህ የለህማ!

ምነዋ መንግስተ ሰማይ! የምህረትሽ ቀን ራቀ?
ምነው ትንግርትሽ ረቀቀ?
ምነው ኪዳንሽ ታጠፈ ... ወዝሽ ወዘናሽ ነጠፈ?
እንደ ዳጉሳ ድፍድፍ ... ላቦትሽ ተንጠፈጠፈ
አሳርሽ ጠሎ አሰፈፈ
        ምነው እርሾው ተሚጠጠ... ጎታው ጎተራው ታጠጠ
        ረሃብ ላንቃው ፈጠጠ ... ያዳም ልጅ አፅሙ ገጠጠ
        ምነው ጭር አለ ቀየው! ሀሩር ነዲዱ በረታ
        ኮርማው ጥማዱ ተረታ
ምነው ነበልባሉ አየለ! ማሳው ተንቀለቀለ
ነቀለ ሞፈር ሰቀለ! ተገድራ ደቀለ
ምነው ምድር ጨነገፈች ... ዝላ ተርገፈገፈች
ካስማ እንደተደገፈች ምነው ሳታብብ ረገፈች፡፡
        ምነው የናት ጡት ደረቀ ... አራስ ልጅ ተስረቀረቀ
        ምነው አንጀቱ ታለበ ... በውኑ ተለበለበ
        ኮሶ ስንብቱን ለለበ
        ምነው ወላድ ተንሰለሰለ ... ልሳነ ቃሉ ሰለለ
        በቁሙ ከስሞ ከሰለ፡፡
አቤት የርግማን ቁርሾ ...
በንጣይ እርሾ መነሾ
ምነው ላይፀድቅ በቀለ?
የሰው ልጅ ዋጋ ቀለለ
ትቢያ አፈር ተቀላቀለ፡፡
ሆድና ጀርባው ተጣብቆ
አንጀቱ በራብ ተሰብቆ
እንደፈረሰ ክራር ቅኝት
ሰርቅ እንዳነቀው ድብኝት
        ወለሰ! ስልቱ ስለቱ
        ሰው፤
        ያ ሰው ጠንካራው ብርቱ
        የጥንቱ የጥዋቱ የመሰረቱ፡፡
ውሳኔው ተርመጥምጦ፣
ተፈጥርቆ ተዳምጦ
ተሞዥርጎ ተሸምጥጦ

ምነው ጓሽቶ ሆመጠጠ
እንደ በሬ ጨው ሆረጠ?
ባፍላው ተዝለፍልፎ አረጠ፡፡
እንደመወከል አጎዛ ... በችንካር ተገድግዶ
ይግባኝ እንዳይል ታግዶ
እንደወይራ ፍልጥ ተማግዶ
ምነው ኩኩ ብሎ ሳይነቃ ... ምነው ሳይጠረቃ መከከ
በስሎ ሳይሰላ ደከከ፡፡
ተፈጥሮ ፊቱን ጨፍግጎ
እንደ ግራዋ ስር መርግጎ
ሁዳዱን እያነደደ
አቤት ባዩን እያሳደደ
እንደ ግራ ግመሬ ... በነፍር ጥፍሩ እየለቀመ
የረጨነውን እየቃመ
ጉልማችንን ሲያመክነው
ወረታችንን ሲያበክነው
እኮ ማንን ልንኮንን ነው?
የመቅሰፍት ደመና ሰሮ ... ሽቅብ ጠቅሶ ሲያርመሰምስ
እንደወረግ ተደርምሶ ... እያንቃቃ እኛን ሲያምስ
ወገብ ከፍሎ ... ደረት ገምሶ
አቅም ሲከላን አቅምሶ
እኮ! እስከመቼ እግዚእትነ
እኮ! እስከመቼ ክራራይሶ?
የቀን ጨለማ ሲወረን
እህል ሸማኔው ደውሮ ... ለጆቢራ ሲወረውረን
አይቀጡ ቅጣት ቀጥቶ ... ቀሪ ወሬነጋሪ የሚያሳጣን
እኮ! ምን በድለን? ምን አጥፍተን? ምን በወጣን?
የምን ቅጣት ነው ይሄ? ቀጥፎ እንደተያዘ ጩልፋት
አርሶ አደፋርሶ በበሉ ... የምን የራብ ትሩፋት
ከንቱ ውዕቱ ልፋት፡፡
እኮ እንደኖህ ዘመን ንፍር ውሃ
ዘር ሳይተኩ ታክቶ መጥፋት?
ምነው ዲበኩሉ ቤዛ ዓለም
ጎህ ቀዶ በቀን መጨለም?
በጠኔ ርዶ መስለምለም?
እኮ ያንጀትን ባንጀት መፋለም?
ምነው? ምነው አዛውንቱ በየጉድባው
ጋሜው ድምድሙ ኮበሌው ... በየጥጉ በየደረባው
ወድቆ ደርቆ ሲነፈራ
ምነው ተፈጥሮስ ጡር አትፈራ?

ምን ይሉታል ይሄን ብይን? ... አንቀጽ ገልጦ ሳያጣቅስ
ምን ይሉታል ይሄንን ፍርድ ...
እንዲህ ያለጉድ አለ'ንዴ?
እግዜር ወንዱ ...እግዜር መንዴ!
ደረቅ ጡት እየጠባን ... ቁረንጮ ስንገተግት
ከመንግስተ ሰማይ የምህረት ግት፡፡
ምነው የማርያም ልጅ ... የስርየትህ ቀን ራቀ
ምነው ታምርህ ረቀቀ?
በየጥሻው ተወትፈን ... እንደተምች ስንረፈረፍ
ቅኔ በበቀቀን ሲዘረፍ
አቀርቅረን ስናንቋርር
ቅሬታችንን ስናንቃርር
እንደቀላጤ አክንባሎ ...
ቁልቁል ባፍጢም ተተክለን
በእርኩስ አመዳይ ተበክለን
እንዲህ የትም ስንቀር እያየህ ዝም ካልክማ
እውነት ... እውነት ከመንበርህ የለህማ!
እንደሰባራ ቅል ደቀን
ድበን በራብ ተደቅድቀን
እርሻው ማረሻው ሲከዳ ... ሰማይ መሬቱ ሲያብል
እያየህ ዝምካልከኝ ... እኔስ እንደሌላው የለህም ብል
ምንተዳዬ ብትፈርድብኝ
መቼም አሽተህ አትቅመኝ
እንደውልብኝ
ናዳ እንደሚጥል ጭላዳ ... ድርቅ ሲሳለቅብን
እየናደ እያነደደ ... የገሞራ ድኝ ሲለቅብን
እያየህ ዝም ካልክማ
እውነት ... እውነት ከመንበርህ የለህማ!
ጀንበር ትንታጓን ረጭታ ... ሰብ ዓለሙን ስትፈጀው
አብ ወልድ ቃልህ ካልበጀን
ድርሳን ትንቢትህ ካልዋጀን
አንተስ ምንህ መለኮት ... እኔስ ለምን ያንተ ባሪያ
ሆዴን ሁዳዴን ሳምልክ እንጂ ...
ትንሳኤ እንደሌለው እሪያ
ያንተን ጉድማ አየሁት
ያንተን ገድልማ ለየሁት
ማረኝ  ሲሉት የሚመር ... የማይታደግ አላመልክም
ወትሮም የተማረ ቄስ እንጂ ... የሰው ልጅ መላክ አይልክም
ለካ ሲያጋልጥ ይቆምጣል ... ወራት ሲጥል ይከፋል
እንዳመለ ጉድጓድ እህል ... ሞት በክፉ ይከረፋል፡፡

ለካስ ሰውነት ባዳ ነው
ለካ ሰው መሆን ዕዳ ነው
እህል ውሃ ቢያደነድነው
ሲያጣ ሲነጣ በድን ነው።
የኛስ ይሁን እንዳሻው፡-
ለእጥፍ ፈተና ከፈጠርከን፤
ለፍታችሁ ተፍታችሁ ኑ ካልከን
ለቀብር አፈር ከወጠንከን።
ግን፡- ግን ... ብላቴናዎቹ ምን በደሉ?
የማንን አደራ በልተው ... የማንን አማና አጎደሉ?
እምብርታቸው ያላረረ ... አጥንታቸው ያልከረረ
ሰማይ በቀል እንደቋጠረ ... እጣቸውን እየመነጠረ
መንገዳቸውን እያጠረ
እንደደራሽ ውሃ አግተልትሎ
በራብ አኮርማጅ ተልትሎ
ከእናት እቅፍ በግፍ ነጥቆ
ምሱን ሊቃመስ ተባጥቆ
ሲሰለፍብን ባጭር ታጥቆ
እያየህ ዝም ካልክማ ...?
እውነት ... እውነት ከመንበርህ የለህማ!
እንደ ታዛስር ሰንሰል አሰልስሎ እያበሰበሰ
እንደሙሬ እየጠረገ ... እያጋበሰ
የዘፀዓት ትንቢቱ ደርሶ ሰብ ዓለም ከል ከለበሰ
በማን ሊዳኝ ነው ቅጣቱ
የሰው ዘር አንዲት ቅንጣቱ
ያባወራ ባለአውራጣቱ።
እንደበልግ አውድማ ነዶ ... ምድር ለቅልቆ ከምሮ
ነፍስ ከእስትንፋስ ነጥሎ ... ሲኦል እቶን ውስጥ ሞጅሮ
በነበልባል መንሽ እየዘራ በረሃብ አራገበው
ሰው እርጥቡን አንገበገበው።
ነፍስይማር! እርካቡ ረገበ
ቀብርም አስከሬን ጠገበ
ፀሀፊም ድርሳን ዘገበ።
ጥንብ አንሳን ግብር ጠርቶ በራሪ ጋር ይወዳጅበት
ስለት እንደዋጀበት እያጋፈረ ይባጅበት
ወትሮም የሞት ምሬትን ያልቀመሰ ...
  የራብ እሳት አይዋጅብበት
እንዲህ አይንን ጡር እያስከፈለ
እንደበቆሎ እሸት እየጠበሰ እየፈለፈለ

ባይበላውም ያባለው!
መቼም ተጠቀም አላለው
አይወልዴ አባ ግድ የለው፡፡
በየጥሻው ተወትፈን፣ እንደተምች ስንረፈረፍ
ቅኔ በበቀቀን ሲዘረፍ
አቀርቅረን ስናንቋርር፣
ቅሪታችንን ስናንቃርር
እንደቀላጤ አክንባሎ ቁልቁል ባፍጢም ተተክለን
በእርኩስ አመዳይ ተበክለን
እንዲህ የትም ስንቀር እያየህ ዝም ካልክማ
እውነት ... እውነት ከመንበርህ የለህማ!

1987ዓ.ም.

መመረጣችሁንና መጠራታችሁን ታፀኑ ዘንድ
ከፊት ይልቅ ትጉ
(መፅሐፍ ቅዱስ)

# መስፍኔ

ሲጠራ አቤት ብሎ የተማረ
ሲልኩት ወዴት ብሎ የዘመረ
ሲያዙት እንዴት ብሎ የመረመረ
ሲመረጥ ተመርቆ
ከልቡ አይርቅም ርቆ
ውሉን አይስትም ረቆ
ማመን ከመስማት ነውና መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል
ተጠርቶ የተማረ ተመርጦ የተመረቀ
እንደፋና ድርብ ድግ ቅኝት
ያንጀቱን ባንጀት ያጠብቃል
የልቡን ባይኑ ይጠብቃል
ሲማር ...
በህገ ልቦና ጥበብ እድሜን እንደሸማኔ ደውሮ
እንኳን ወደሚሄዱበት በአይነ ህሊና
ቅድመ ዓለም ተወርውሮ
ከራሱና ከምኞቱ ተሰውሮ
አባትና እናት እንዳቀደ
በራሱ ካልቀለደ
ባሰቡት ልክም ባይሆን ... የእውነት አነጣጥሮ ለመጣል
ሰው ሆኖ ከተፈጠረ ... ለጥሬ ዱለት ባይበቃም
ወንድ ልጅ አሞት መች ያጣል
ራስ የሚችል አንገት
ሽቅብ የሚቃትት ጉልበት
ቢላ እማይደፍረው ጉበት
እሱማ አለ እንጂ አለበት!
ለወለደችው የታዘዘ ... ለፈጠረው ያጎነበሰ
ለለቱ ፈረሰም ብንል ... አድሮ ይጠድቃል እንጂ
አፈር በልቶ መች በሰበሰ
አታዩትም ደምሰውን ወንድሙን እንኳ ደስ ያለህ ለማለት
ባለበት ... በዋለበት

በሌለበት ... ፅንፈአለም እስኪሰማለት
በፍቅር ልቡ ደማለት
እና ... ይችን ቀን የባረከ
ቤዛ አለም አማኑኤል ... ፍቅሩን ባቡ ላይ ተረከ
ወልዶ መሳምንና ... ዘርቶ መቃምን ለሰጠው ሰው
ምን ቀረኝ ብሎ ያዝናል ... ሰማይና ምድር ከተዋሰው
ለፅድቁ አንድምታ ምልት
ክንዱን አዝሎት እንዳይመክት
ከልጆቹ አንዱን በሞት ተነጥቆ
አንዱን ያስመርቃል ለጥቆ
የልጅም አሥራት አለውና ... መለኮት መርጦ ለወሰደው
ሳይጠግን አይሰብር ጌታ ...
ከጠራቸው መኃል ለይቶ ለምረቃ ፈቀደው
የወለደ አንጀት ባይችልም.. ኃዘን መብቃቱ ግን ግድ ነው
የለበሱት ከል ካልወለቀ ... የቆሎ ተማሪ ለምድ ነው
እና ሁሉም ይበቃል ... የሄደም አለበት ይቅናው
ያለም በፍቅር ይጠብቃ
አቡ እናትህ እንዳታዝን ... ካይንና ከልቧ አትራቅ
አባትህ እንዳይነቅፍህ ... ላመንክበት ቀጥበል
ተግ በል እንደ ብራቅ
ወንድምህ እንዳይንቅህ
ልብህ ብቻ ይሁን ሥንቅህ
በደል ብቻ ይሁን ትጥቅህ
እህትህ እንዳታፍርብህ
ክንድህን ሳትንተራስ
የነፍስህ እጦት እንዳይርብህ
ወዳጅህ እንዲኮራብህ
ከቃልህ አትጉደል ... ሳታት ቁም በምኩራብህ
ጠላትህን አንተው ፈልገው
ለሱም ቢሆን አንተነትህን ምን ብትሰስት አትንፈገው
ስሜት እንደ ድንጉላ ፈረስ ... ሽምጥ ማስጋለቡ ባይቀር
ወንጀል አይደለም ማፍቀር
ሁሉም በእርሱ ነውና ... እሱ ያልገባበት ስለማይሰምር
በጥርጣሬ እየፈረጅክ ... ኃሳብህን ባሳብ አታስምር
አሁን ደሞ አንተ አልኩት ቅድም አንቺ ብዬ
የኔን ለሱ ትቼ የሱን ተቀብዬ
ልምጣ ወይስ ልቆይ ... የቱ ይሻለኛል
ከነበረ ይልቅ ... ዓመተ ይለያል
ሙሌ አንዴ ይለኛል ... አብርሃም ወንድሜ
ቆሞ የሚጠብቀኝ ... እኔ ተጋድሜ

ሰፋ አርጊው ቦታውን ... መቼም መምጣቴ አይቀር
ከሞት አያስጥልም ... ወትሮም ኗሪ ማፍቀር
መስፍኔ ሽቅርቅር
እንደ ቡን እንደ ጫት ስትይኝ ቅርቅር
የጠናብኝ ለታ
አለሁ አለሽበት ... ለፍቅርሽ ውለታ፡፡

ተረት ሰፈር

# ተንጋላ የሞተችውን
# የመንታ እናት ጣር አየሁት

ጉድ ይገርማል ... አህያ ከጅብ ይከርማል
　　　　አሉ
አዎ ... እንደሰራ አይገድል
ምናለ ... እንኳን የራሴ ባቄላ ፈሶ የሰው ጤፍ
　　በወረንጦ የምለቅመው ጎበዝ
　　　　አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል
ቀን ሲያረጅ ስንዴ ከእንክርዳድ ያዳቅላል
ሆነና
ክንዴን ሳልንተራስ የሳር ጎጆዬን ክዳን
　　እቡይ ባላምባራስ እንደሃሮ ሰበዝ ለመምዘዝ
ሞቴ ነው አለ ይርዳው ማሙዬ
　　የገደለው ባልሽ ... የሞተው ወንድምሽ
እንዴት ሊወጣ ነው የፈሰሰው ደምሽ ...?
ቢሏት
የመንታ እናት ተንጋላ ስትሞት አይቼ
እኔም እንደሷ በጥንድ ፍቅር ለይቼ
ግራ የገባ ግራ አጋብቶኝ እያዛጋ ደብቶኝ
የማረገው ባጣ ... ልባም እንዳጥቢያ ተፈልቅቆ ወጣና
ዛቢያ ቆርጠሽ መገራ ...
መላ መተሽ ገራገር ... ፈረስ ቢያግዝሽ ፎገራ
የልብ ያደርሳል ወገራ ... ቢለኝ
እንደገና የተወለድኩ መሰለኝ ...
እንዳለችው የኔ ቢጤ ገራ ገር ነገር
መስሚያ ጆሮ አጥተን እኛ ስንቸገር
እንዴት ሸክላው ምጣድ ... ምንም ሳይናገር
ለማ ለማሸጋገር
ቃል ያላስረጀውን የወይራ ፍልጥ
　　እሳት ሲፈጀው
ኖሮ የሚበጀው
ላዩ በድን ታቹ በድን
መሃል ቤት ነፍስ አድን
ወስዶ ከአዳም ዘር አበልጅነት ተጠብቆ ዕድሜ ቀጠለ
እየተቃጠለ

ዛዲያ በፈሊጥ ብንነግራቸው ካልገባቸው
እኛስ በፍልጥ ብናስረዳቸው
እኛን ከበደን እንጂ
        እነሱስ የፈቀዱት ነውና ምን ተዳቸው
ሲጠቀሚቸው እምቢ ካሉ
        በመድፍ መፍቀድ ምን ይገዳል
ካያያዝ እንጂ ይቀደዳል
ወትሮም ካነጋገር እንጂ ይፈረዳል ...
መጀን ...
        ሰው ስንል ሰው ፈጀን አይደል
እንኳን ሰው ሲበደል ... ወተት እየሸፈተ
ያሁኑ ይባስ ሞት ካንገት ደረሰ አሉ የታገሱት
እንደደስታ አምበሳ ምድር የሚበሳ ክርን ይዘው
        አደጌር ሳያስገቡ የሰላም ዳስ ጥለው የደገሱት
መጀን...
እንደኛማ ክራሞት
በውኑ ... ካንገት ከደረሰማ ሞት
ወይ ጎጃም ወይ ዳሞት
ምን አልጫ ቢሆን ... ጉበት ላይ የተለጠፈ አሞት
ለጥሬ ዱለት የተመኙትለት
አሻፈረኝ ለማለትንኳ ወኔ ቢያንሰው
የት ይቀራል መፈራገጡ
        በጣር መቃተቱ እንደሰው
አዎ ...
ይህኔ ነው መፍራት ... ይህኔ...
        በደመነብስ ሲወራጭ
መልካው በደም እንዳይራጭ
ባቋራጭ
እንደንጥል ቆራጭ
መራጭ እንዳይወድቅ ከምራጭ
መጀን ...
ሰው ስንል ሰው ፈጀን
ሞትማ ካንገት ከደረሰ ... ከቀረ አዙሮ ማየት
ዛሬን በትላንት መለየት
ምናለ የፊት የፊቱን እንደጓያ ነቃይ
እንደድልግሞ ሸቃይ
ትላንትን አናንቆ ለለት ጉርስ በሶስት ታንቆ
ተመንቆ ምኞት ብቻ ሰንቆ
አካኪ ዘራፍ ቢፎገላ ...
ምነው አፈር በሆንክ ይላላ
ላፈር የታጨ ካፈር የተሰራ ገላ ...

ትላንትና በስቲያ ... በህልሜ ነግሼ
ፈረስ የሚያስጋልብ ... ዳስ ጥዬ ደግሼ
ለመጣ ለሄደው ... ማሳለፍ ሳያንሰኝ
በፈገግታ ማርኮ ... ዙፋኔን ወረሰኝ
እንዳለችው ጋለሞታ ...
ማግስቱን ሞታ አድራ
ለጥቁር አፈር ተድራ
ሰርግሽ ዛሬ ነው ዛሬ ስትባል
አስከሬኗ ቀብር ይገባል
ታዲያ እኛስ ከሷ ተምረን ብናስተነትን ምን ከፍቶ
እንጂ ምን ይረባል ሞላው ...
ምን በወጣን እየሰበሰብን መና ከመቅረት ለፍቶ
ለምን ብለን እንደጨው ዘር እንበተን
መጀን ...
ሰው ስንል ሰው ፈጀን
አሉ
ሳይመሽማ ከመሸብን
እኛስ ምን አለብን
ነጋ ጠባ እዛና እዚህ ብን ብን ከማለት
ይለይለታ ይለይለት
ሞትንደሁ ግብር ፈራሽ ርስት ነው
መክነን ሕይወት ከስስት ነው
ድህነት መብት ነፍጎን
ጨፍግጎን
በግዴታ ብቻ ብንጠፈር
ዞሮ ዞሮ ቤት ...
ኑሮ ኑሮ መሬት
ከቀረ እትብታችን ከተቀበረበት ጥቁር አፈር
በእብሪት ተነቅለን በሞርታር ተቀቅለን
ጠፈር ወጥተን እንስፈር
ዘጠኝ ሞት ባንዴ ሞተን ... ዘጠና ጊዜ እንፈር?
ወገን
የመከራ ጎጆ ፌጦ ቢያስረጨበት
እምቦሳ አያወጣም እንኳን ሊታጨበት
ነው ያለው ያ አንጎራጓሪ ...
ዓሳ ጎርጓሪ
የፈራ ያፈራል ብለን እንጂ
የኔንም ያንቺንም እኔ ልውደድልሽ እንዳለው በረኛ
የረምባ እረኛ
ሞኝ ባያፍር ዘመዱ ያፍር ሆኖብን
የሱን ጉድ ተሸክመን ባስታመምን

ክሰን እንታረቅ ባለን
ከዚህ ወዲያማ ስለነፍስ ብለን
እንዴት እናስለምን
ይሁን እስቲ ...
የጨዋ ልጅ ጨዋታ እንዳመዳይ ካብማ ከፈረሰ
ተወልደን ያደግንበት ቀዬ ባዳፍኔ እየታረሰ
ሞትማ ካንገት ከደረሰ
ካለ ቄስ አይናዘኝ ...
ካለባሌ አያዘኝ
እንዳለችው ገመምተኛ
ደመኛ እንደአድአ ማኛ
ሊወቃን አውድማ በደቦ ሲለቀስ እያየን
አስችሎን እንዴት እንተኛ ... እንዳዘንተኛ
አገር ሳያዘን
ሕዝብ ሳይናዘን
ካለንበት ባንንቀሳቀስ
ቀስ ብሎ እንደቀትር እባብ
በደረቱ የሚሳብ
አገር ለመቁረስ ሲሰናዳ
እንደመርግ ከላይ ቁልቁል ብን አዳሩው እንዳናዳ
ግዳዩንኳ ስለት ብናጣው
የተገፋ ነው ወትሮም የማታ ማታ ቅቤ እሚወጣው
ብንሸሽ ... ከራሳችን አናመልጥ
ብንቆርጥ ... እንደጊደር ጋት አንፈርጥ
በለስ እስኪነሳን አይተው ዘንዳ
የመጣውን እንዳመጣጡ ለማስተናገድ
ቀድመን ብንሰናዳ
ፈርተንም ቢሆን እሰየው
ደፍረንም  ቢሆን ወዬው
ያልን ለት
ይህኔ ነው ...
ተንጋላ የሞተችው የመንታ እናት ጣር የታየን
ይህኔ ነው
ዋኔና እኔን እኔ ... ያሰኘን ...
የሆነስ ሆነና አባይ ስሙ ማነው አሉ ...
ዛዲያስ ...
ዓባይማ ... ዓባይ ነው ... አለ ጣና ...
መቸም አያሳጣ ... ጌታና ቀጣና ...
ዋሁዬ የሚያሰኝ ...
ዋኔን ዋኔ እሚያሰኝ

ዋሁዬ ... ዋሁዬ ...
አባይ ዳር ዋሁዬ
ጣና ዳር ዋሁዬ...
በልጅ ተበክዬ ...
ለልጅ ልጅ አክዬ
ያለችው ዳክዬ ...
መረብ ላይ ሊያጠምዷት
እንደወፍ ዘጌ ... በጥሬ ሊያለምዷት
ደሞ ዘነጣጥለው ለርኩም ግብር ጥለው
እሳት ዳር ተቀምጠው ጠራርገው አሚጠው
ደሞ በክራንቻ ወቸ ጉድ እያሉ
　　　ደሞ ወርች ገምጠው
ቀንጣና ቀስፏቸው ኋላ ለመበጣት
የቀሰሩ ለታ ባመልካች ሌባ ጣት
እሷስ የማን ሁና እንደዋናተኛ የብስ እየቀዘፈች
አገሬን አገሬን
አውጪኝ አውጪኝ እግሬን
እጅ አልሰጥም ብላ
ቁርባን ተቀብላ
ዛል አምበሳ ደብር ደብረ ዳሞ ህድሞ
　　　ሰላም ብላ አረፈች
የራሷንም ሳትሰጥ የሰውም ሳትሻ
የኛ ሆና ጋሻ

# ዋጋ እንዴት ልጠይቅ ...?

ምንም ጥበብ ሆኖ ... ቢያረቀኝ ቢያመጥቀኝ
እንኳን ለወደድኩት ... ለጠላሁት ቢሆን ...
        ዋጋ ካልጠየቅኩት ... እሱም አይጠይቀኝ
ወዲህ ቢሉት ወዲያ ...
እንዲያ ... ሲሉ እንጂ ነው ...
        እንግዲያማ እንግዲያ!
የልቤን መንትያ
ነቅሼ ጉትያ
እሰጥ አገባ ብል እንካ ሰላንትያ
ሁሉም ትላንት አልቋል
        ያውም ትላንትያ!
ዋጋ ብሎ ሥፍር ... ሥጋ ብሎ ንብረት ...
ይገባኛል ካለ ... አይቶ እስኪፈትነው
        እስኪያስተነትነው ... አረግንለት ክብረት
አንዲት ሽምብራ ራስ ...
ብርኩማዬ ብዬ ... የሰው ከምንተራስ ...
የነፍሴ ባለሟል ... ይቅጣኝ ባላምባራስ

ጢሜን ስጣልኩባት ቀን
3/3/95

# አለዚያ ወደዚያ …

«ሠላዕ» ጠርታን … መንገድ መርታን …
የነፍስ የሥጋን ግጥምጥሞሽ …
        በሃልዬ አሻግራ በህሊና አጋርታን …
ያፍላ ዕድሜን የስሜት ረመጥ ውጠን …
እንደመረዳታችን በረታን …
        የሰማዕት አፅም ተመርኩዘን …
አምባ ሸንተረር ተጉዘን …
እንደቄጠማ ለተጠማ ተጎዝጉዘን …
                አሜን …
አሜን ለዓለም ዓለም …
        አለዚያ ወደዚያ …
አረግኩ የምለው ምንም የለኝ …
        ቢኖርም ዕዳ ከመክፈል አያልፍም
ግር ያለው ካልሆነ በቀር … ቅር ያለውም ቢሆን …
        ይህንን ሃቅ አይከፍልም …
እንደየመረዳታችን አንዱን ጥለን አንዱን አንጠልጥለን
ካንደኛው ተምረን ካንደኛው መጥለን…
ክብር ለሰማዕቶቻችን
        እዚህ ደርሰናል እንደምንም …
                አሜን …
ከተጨባጭ ውጭ አናምንም!
                አለዚያ ወደዚያ …
«ሠላዕ» ጠርታ መንገድ መርታን…
        ሁሉንም በንቃትና በብቃት ተወጣነው …
ጓዶቻችንን እንጂ … ግባችንን መቸም ቀን አሳጣነው …
የቻለ ገሰገሰ … ደግሞ …
ያልቻለ አዝግሞ … አገግሞ …
ያረፈቀ ደሞ አለበት አረፋ እየደፈቀ
        ሁሉም ሊሸለም እንዳቅሙ …
አንዱ ብቻውን ቀረ …
        አንዱ ብቻ ለጥቅሙ …
                አሜን …
        አለዚያማ ወደዚያ …

እንዳስመለከተው ተሰማርቶ …
እጁ እንደቻለ በዘገነ …
የገዛ ነውሩ ካላነፈረው … ምንተዳችን እኛ …
ቢጤው ጋር በወገነ …
አጎራረስ ልክ ከነገረ …
ሞፈር ዘመት ወንዝ ካሻገረ …
ሁሉም በወደደው ነው …
ተከድኖ ይብሰል እየተባለ …
በሸፍን የነደደው
እና …
ቀኑን ካልተማርንበት …
ሌቱን ካልዘመርንበት …
አለዚያማ ወደዚያ
አሜን
«ሠላዕ» ጠርታ መንገድ መርታን …
የነፍስ የሥጋን ግጥምጥሞሽ …
በሃልዬ አሻግራ በህሊና አጋርታን …
ገሞራ እንደኮሶ እስኪያስቀምጠን
እንኳን በወደድነው በጠላነው ተርመጥምጠን
በላይ እንደገዳይ … አሜን ማለታችን
እንደሞኝነት ተቆጥሮ በማንም ጉርባ ተሸምጠን
ሁሉንም እንዳመሉ አስተናግደን ብንሸኘው …
ደኔ ይህንንም ተመኘው?
ፍቅር የህግ ፍፃሜ ነው እንዲል ቃሉ …
የሰው ልብ ለሰው ይታያል ብለው …
ልጄ ሆይ ሰው ሁን የሚለው
ያባታቸውን ምክር የተቀበሉ ብቻ ያውቃሉ
አንፎካከርም
አንከራከርም
አንወዳደርም …
ግን ቃል ለምድር ለሰማይ …
ከማንም ከምንም አንደራደርም
አሜን …
አለዚያ ወደዚያ …
አሜን …
ብቻ ሁሉንም አሜን ብለን ነው የተነሳነው
ለዚህም ነው ሞት ያልደፈረን …
እኛም ለኑሮ ያልሳሳነው
ፍራትም እንደሆነ ለመቆንጠር ሲሄዱ ነው
ብላለች እናታችን

ክብርም እንደሁ ከመስዋዕትነት ነው
ብላናለች እናታችን
ህድሪ ድዓ ... ዝባን አሕዋት
አድን አወድን
ህድሪ ድዓ ዝባን ስውዓት
አፍን ከብድን
ኢልካ ... ከምነፍስካ
ምስበአልካ ...
ብንለው ባባቴ ቋንቋ ...
እምዬም የግሸኗ
አንቀፀ መስቀል ነው ስንቋ
አሜን
አለዚያ ... ወደዚያ...
የነብር እልኩን
የኢትዮጵያዊ መልኩን
ልዩነቱንና አንድነቱን ለይቶ ያላጤነው
ወይ መጤ ነው ... ወይ ላጤ ነው ...
ያገኘነውን ለመዋጥ
የሚኳኳጥ ...
አሜን ...
ኢትዮጵያዊ ...
ኢትዮጵያዊ መልኩም ልኩም አንድ ነው
የናቱም ያባቱም ልጅ ጥንድ ነው ...
መንታ ክንድ ነው
ባንዱ ለክቶ
ባንዱ መክቶ
አያውቅም ታክቶ ...
እንደ ልበ አምላክ ዳዊት
በወንጭፍ ጎልያድን
እንደ በትረ ሙሴ ... ነገዱን
ከፈርኦን ባርነት ሲያድን ...
የናቱ ልጅ ወልደ እግዚአብሔር ካህን ...
ቀብሩን በመስዋዕትነቱ ባይከድን ...
እሱ ነው በራሱ ጉዳይ ...
ዘራፍ ብሎ ገዳይ ...
ተጋዳይ ...

# የቀረንን እንጫወት

ተኩሰን ብንስትም ሞት ፈርተን ግን ነፍስ አንሰስትም
ህልም ባንከስትም ራዕይ አለንና አንወሰልትም
ቢያንስ ሰው ነንና ሰው እንወዳለን
እንዳመጣጡም እናስተናግዳለን ...
ምድር ከተፈጠረ ምስጢር ከተቋጠረ
እስካሁን እስካለንበት
ከድህነታችን በቀር እኛነታችን
ሰው ፊት የማያስቀርብ ምንም እንከን የለበት
ደማችን ውስጥ ኢትዮጵያዊነት አለበት
ኢትዮጵያዊ ደም መልኩን እንዳይለውጥ
የብሉይ ግድ አለበት
ይኸ ሆነና ጨዋታው
ሁሉንም እንዳመጣጡ የመጣበት ረታው
እንጅ ምን በልተን ጉልበት አለን
ምን አግኝተን እንሰስታለን
ኢትዮጵያ የምትባል አገር እያለች
ኢትዮጵያውያን እያለን
ለጣሊያኑ ለድሙሹ ለምናምንቴው ጋጠ ወጥ
ሃሳቡ ሳትለወጥ
ያውም ልቡ እስኪሰወጥ
ለዚህም ወጥ ለዚያም ወጥ
ሳናቀርብ የቀረንበት ቀን ቢቆጠር
ቀኑ ራሱ ዕድሜው ይጠር
እና የፈሪ ምስክርነትም ቢሆን
በዚህ ዘመን ከተፈጠረ ገድል በላይ
ነበረ ቢሉኝ አላምንም
ከባድመ መውጣት ማለት
አኺሉዋ ፀሓይ
አራባ ጉተበለ ውይናይ
ሳላ ምቅናይ
አሳየና መለኮት እሱን መርጦ መሲህ ልኮት
እሱም እንዳይቀብጥ እኛም እንዳንኮተኮት

የሱ ነገር ያለቀው
ያኔ ነው በማን አለብኝነት ኢትዮጵያዊነቱን ሲንቀው
አብሮ መብላትንኳ ባያንቀው
ምንም ነገር ከልኩ ላያልፍ
　　　ምንም ነገር ከልኩ ላይዘል
ይኸ ሁሉ ግድየለሽነት ይኸ ሁሉ መንዘላዘል
እንደርጥብ ሥጋ ለመዘልዘል ...?
ቦታቸውን አሳይተን ...
ሁላችንም እንደየጎናችን ገብይተን
ያተረፈም አተረፈ ...
ያላተረፈም አረፈ
እና ... እንግዲህ በክንድ አይቀብጡም
ይተነኩሱት ግን አያጡም
እጃቸው በጣም ላፍ ቀርቦ ...
　　　ለሆድ ነው እጅ ቢሰጡም
ሥራ ስለሌላቸው ደሞ ... ያለ ሴራ አይቀመጡም
ቀብራቸው ተምሶ እስኪያልቅ ...
　　　ይሸርቡት አያጡም
እና ... ጠንቀቅ ነዋ! ልባም ...
ያንጀት ነው ከሆድ ባይገባም ...
ስንሞት እንጂ ስንስቅ ስለማያውቁን
የዛሬ ወዳጅ የነገ ጠላት ሊሆን እንደሚችልም ስላሳወቁን
የተማርነውን ረስተን ... ድንገት ደሞ ቢጠይቁን
መልሱ ጠፍቶን እንዳንቀጣ
ጠንቀቅ ነዋ  ከጥንቃቄ አንውጣ
ወትሮም ይኸው ነው ወታደር
ኢትዮጵያ ... አምና ያቆመችው ዘቢደር
እንኳን ትጥቁን ሚስቱን ላይፈታ
　　　የክፉ ቀን ባለደራ ...
በፍቅር ካልሆነ በቀር ... በእልህና ባደራ
ከመስዋዕትነት በስተቀር ...
　　　የጉሮ ወሸባ ልክፍት ስለሌለው
ቀድሞ ፈቅዶ መቿልና
　　　የሚሳሳለት ምን ነፍስ አለው
አየነው አይደል እንዴ ትላንትና
　　　ዓመትንኳ መች ሞላው
ያ ንስር ... ያ ያገር ጥቁር ሰማይ ጥላ
　　　እንደመተት ዳመና ሰሮ ...
ካደፈጠበት ሰርስሮ ... መላውን አስሮ

አየነው አይደል እንዴ
ለየነው አይደል እንዴ ... እንክርዳዱን ከስንዴ ...
እግረኛ እንደተርብ ሲናደፍ
የጥንስሱን ሲደፈድፍ
ጠርቶ እንደዘመራ
እዛው ራሳቸው መቼ መንግስት ...
        እዛው ፈላ እዛው እዛው ፀአዳ ... አስመራ ...
ልጅ ይውጣለት አስመራ ፀአዳ ፍንትው አርጋ ባታሳየን
        የነሱ ምላስማ ገና አልሞተም
ደሞ ንፉግ እንዳይባል የሚያቀርበው አጥቶ
        አሉባልታ አልሰስትም
እና ... ጠንቀቅ ነዋ ልባም ...
ስማችን ... ቅስማችን ... ደማችን አንድ ነውና
        ሌላ ስም ውስጣችን አይገባም
እና ጠንቀቅ ...
ባልበላውም እበታትነዋለሁ እንዳለው
        ስስታም አውራዶሮ
ለላዛኛና ለኮሚደሮ
መቃተታቸው አይቀርም ...
ሰው ላልሆነ ሰው ...
        የሰው ስጋ መብላት አይቀርም
እና ... ጠንቀቅ ...

# እነሆ ... ገድ !

የሰማዩ አባታችን ፍፁም እንደሆነ ሁሉ ...
እናንተም ፍፁማን ሁኑ ...
**የቀራንዮው አማኑኤል**

## ደገምኩኝ ገድ

የበላሁትን ተሸክሜ ...
የጠምኩትን ደግሜ ታክሜ ...
በመንገድ ደክሜ ... ተረት ሰፈር ደረስኩ ...
እኔም ተወራረድኩ ... እንደወላድ ታረስኩ ...
ክብሬን ነውሬን ወረስኩ ...
ፈላስፋ አየሁ ... ፋኖ አገኘሁ ...
ካህን ባልኩት ተሞሀኘሁ ... ካህን ባልኩት ተሸኘሁ
ከዚያም ዋኘሁ፡፡

## ሰለስኩ ገድ

ማነው የሚንገዳገድ ... ማነው የሚወላገድ
ማነው ከመንገዱ የሚታገድ ...?
ማነው እሱ ልቡ ዋሱ ...
ማነው እሱ ነውሩ ምሱ
ማነኝ ይላል ቢጠይቁት
ምን ያመጣል ቢፈጠርቁት...

## ገድ

እንካ ሰላንትያ
በመንታው መንትያ
በዋኔ ጉትያ
በምንትያ አልያም
ደሞ ለህልም አለም
ደሞ ለቀን ሸክም

## ገድ

እንደቅኔ መንገድ
እንደመጥኔ ሞገድ
    ታውቅ እንደሁ ሌላ አገር
    ሱሪ ማን ይጥፋል አንተ ሳትናገር
ጀመረው ፈላስፋ እንጀራ ሊያሰፋ
ሚዛኑን ማዕዘኑን ሁሉን አመቻችቶ
ዋሻ ያጣል እሱ ዓለሙን ተችቶ
    ምስጢር ገለጥኩ ይላል
    ሳይጣድ ይበስላል
    ቃል ያጠራው ለታ ሻሞላ ይስላል
ጀመረው ፈላስፋ ቀጠለው በገባው
    ሾተል ከሰገባው እየተመዘዘ
እሱ ኮርቶ ሊያድር ሌላ እያናዘዘ
የምሽት የማታ ዘልዓለም ሲናፍቅ
    ዕለቱን ፈዘዘ
ጀመረው ፈላስፋው እንዳስመለከተው
ዓይኑ ካይን መርጦ ቆራርጦ ባከተው
    በለኝ ልበልሃ እያለ ጥም ሊሞት
    ካማራ ተጣባ ወይ ጎጃም ወይ ዳሞት
    የድርሳኑ ብዛት የሃሳቡ ግዛት
    የኑሮው መንዛዛት
    የኛ ዕረፍት የሌላት ከንፈሩም አልወዙት
    እሱም አላገዙት
ጀመረው ፈላስፋ ...
እሱው በመጠነው እሱው በወጠነው
ሰው ባውጠነጠነው ሙጢ ባቀጠነው
ፋኖን አፈንፍኖ ፋኖ አሰለጠነው።
    ፉንን ያርገኝና እኔን በሱ ምትክ
    ቀጠለ ብትክትክ ጀመረው ትክ ትክ
    ስለት አለው ዓይኑ
    ሚዛን ነው ካይኑ ያገር ሞት ነው «ዓይኑ»
አመጣው ወሰደው አይሰራም እሱ ቤት
አለችው እመቤት የልቡ ጎረቤት
አምርቶ ላይሰስት ወይ አልሞ ላይስት
    ሰይፍ ነክሶ ምሎ
    ጓያ እንደሰበረው ፈርቶ
            ተሸመድምዶ ስሞኝ ተገምሎ
    በጉድጓድ አምሎ

ለጉዳይ አይውልም
አያወላውልም
ሁኔዋ ሁሌም ሁሌም ዘብ ቆሞ ዘብ ይደር
እንኳን ለእህል ውሃ እርሳስ ሳይበደር
ተወሰደ ኖረ
ሞተ ብለን ቀብረን በሳልስቱ ብናይ
ቀብር ሰብሮ ወጣ የውደየው ተዋናይ
ፋኖዬ አሸወይናይ
ላሳየሁት ካህን
አልኩት አደራህን
ጦም ጠሎት ስግደቱን ብታጣፍጥልኝ
እኔ አለሁ ለራሴ አትጋፈጥልኝ
በሱ ባህሪ ቀርፆ ቃል በደም አስርፆ
መስቀል ላሸከመኝ
አላውቅም ደከመኝ
የሰንበትን ክብር የትንሳዔን ህብር
የነፍስን ብር ብር
እሱው ቢያስተባብር
አስራትንኳ አልሰጥም እንኳንስ ልገብር
እሱን ያገኘ ለት
እኔም እንደናቴ እኔው እሆናለሁ
አቃቢት መበለት
ካህን እባክህን
ምህረትህን ለቸር ለንፉግ ባክህን
ለማይም ልክህን ለታማኝ መልክህን
መቸም አትንፈገው
ያ ያፈገፈገው
ደሞ ተፀፅቶ ወዶ እንዲፈልገው
ይድረስሽ ኢትዮጵያ
የመሰበ ወርቁ አለላው ወስከምቢያ
መጣልሽ ካህኑ
የዓለም መድህኑ

«ከሰው መርጦ ለሹመት …
ከእንጨት መርጦ ለታቦት»
(የአማራ ብሂል)

# ከሰው መርጦ ለሹመት

ከሰው መርጦ ለሹመት …
«ለሺሞት» ስልጣን ቢያጨት
ልብና ኩላሊት ይሆናል ይሏል እንደሰላይሰጥ ስጋ
በቀንጣጤ የማይነጬት
ከሰው መርጦ ለሹመት ለሸንጎ ለሽምግልና ቢሰይሙት
የበቅሎ ማህፀን መንታ መንታውን ያትባል
የማርዳው ወዳጄ ሞት … ይሙት
ቡቃያንኳ ዳዋ አይውጠውም መከር እስኪከተት ባያርሙት
ለታቦትም እንጨት ሲመርጡ
ግራር እንጂ ሌላ አይቆርጡም … «ለሸርጡ»!
አዎ ግራር ውሃ ጥም አያዝለው
የበረሃ ወረርሽኝ የቆላ ንዳድ ወባ አይጥለው
አዎ ግራር በራሱ ጠማማ ከሥሩ ተነቅሎ ካልወደቀ
ቢከለትሙት እንኳ በበጎነቱ በዕምነቱ
እያደር ነፍስ ይዘራል
እያደር እያንሰራራ እያደር እየጠደቀ
መልሶ ቦታውን ይይዛል
ለአስርቱ ትዕዛዛት ቃለ ህይወት
«ለወርቀ ቀለሙ» ይገዛል
እሸት ቢጠብሱት ልምጥ
በረት ሲያጥሩበት ሰባት ዙር ገረገራ ሽምጥ
አማናውን ሳያጎድል በዋለበት ይመረቃል
ማደገ መለኮት ነውና ድርሳነ ሙሴ ሥላሴ ቃል!
አዎ ግራር ፍሉን ውሉን አይስትም
የልቡን እንደሰላቢ ለግሞ
አፉን እንደ‘ፉኝት ለጉሞ አይወሰልትም
ለጥቅም አቅሙን አይሰስትም
ስትፈለጥ ምነው መግራትህ ታዲያ ብዬ‘ኳ ስጠይቀው
መልኬን ልኬን የውስጤን እኔ ስለማውቀው
የጨነቀው ምናል ገልጦ ቢያየኝ
አይቶ ገምቶ እስኪገለጥ ነው ያለኝ
አዎ እሳትም ላይ ሲጥሉኝ
እየማገዱ ሲያቃጥሉኝ

መጀመሪያ እጨስና ወዲያው ቶሎ እነዳለሁ
የቆሰቆሱኝን እደቁስና መልሼ የግቤን አድርሼ እበርዳለሁ፡፡
እሳትማ ማን ይችላል ማን ይችላል ጥቃትማ
ወይራና ጥድ እኔ አለሁ ወንድ ቢሉኝ…
    ውሃ ውሃ የምታሰኘውን
        በረሃ ጥም ግጥምን አያውቃትማ
እንደኔ ጣይ ካልበላው
እንደኔ ካልተንገበገበ የኔን መከራ ካቀለለው
ከፍርድና ቅድ ነገር ቀድሞ አሃዱ በስመአብ መጀመሪያ
    ቀልቡንም አልጠቀለለው
ወይራና ጥድ ዋቢ ጠርቶ ከእኔ እኩል ሙግት ቢቃጣ
ባለ መረሸት በቅሎ ባይቀጣ
ፅላተ ሙሴ ቃል ስላሴ ተሸክሜ ለነሱ እሰጥ አገባ ንትርክ
    እንግዲህ እኔ ከደብር አልወጣ
እነሱ የበሉብትን አምባ ቢያደምቁ
አጥር ቢሆኑ እንጂ
    አጀብ እንደኔ ለትንሳኤ ሞት አያጠምቁ

    አዬ ግራር አይታክቴ
    አባ አይደርቄ ራስ መክቴ
    ምነው ታዲያ ቅንቅን ይደፍርሃል ብዬ
        ደሞ ደግሜ ብጠይቅ
    «ከዚህ ላይ እውነት ታይቶሃል ይልቅ»
    አለና አረፈው
    እንደተወረፈ እያጎረፈው

አፈር ዕድሜ ሲግጥ እያየሁ አንጀቴ አልችል ብሎ ባስጠጋው
ቀን ቆጥሮ ጡት ስሬን እየቀሰፈ ግራ ቀኝ ጎኔን ቢወጋው
ከኔ በቅንነት መጠቃት የሱ ብልግና አይብስም
የዚህ አይነቱ እኩይ ተፈጥሮ
    የልጅነት ባሏን እንደቀበረች ኮረዳ …
        በቁም ከል አያስለብስም?
አዎ ሰው የሚጠቃው ወይ ሲንቅ ወይ ሲያዝን ነው
ፍትህ አልባ ሲያዝ ሲመዝነው
ታዲያ መስፈርቱም እያጋደለ
ብይን እየጎደለ
    ህልውና ያዛባል
ጤዛ ሳይረግፍ ካልነቀበት ደሞ
    በጠራራ እያንጠራራ የምሽት የማታ ይዛባል
ቼ ፈረስ እያለ ኮርቻ ሳይደለድል
እዚህ ላይ አዎ ታይቶሃል

እውነት አለህ የልብ እውነት
ወትሮም የጋጠወጥ የትንሽ ሰው ሰውነት
«ጤና አዳም» ማጥፋት ነው አገር መዳኒት እያሉ አብነት
ደሞም አንዳንዴ ስታየው ያለወቅትም ቢቀጠፉ
ቃል እንደ እዝን ቤት ጥሬ በልተው ኪዳነ ውሉን ካላጠፉ
የሥጋ ሞት ቢሞቱ እንጂ ከዓለመ ዓለም አይጠፉ?
የወጠኑትንኳ ባይጨርሱ
ወላድ በድባብ ትሂድ እንጂ
ልጅ ይተካ የለምወይ ባለታሪክ ባለቅርሱ
ለነገሩ ሰው በመልካም ምግባሩ አይመካም
የሴም ዘር ቢሆን የካም
ግን እኔን ለታቦት የመረጠ ሰው
የተግባር ግንባር ምስክር ነው ክህሎት እንዳላነሰው
የለምና የሞያው ባለሟል ደሞ ክንዱን ሳይንተራስ
እኔ አልሆንም ባላንባራስ
ሲራራ ነጋዴ ነጋድራስ
ታድያ ግራርን ለታቦት የመረጠ ሰው
ዛሬ ለራሱ መላ ካነሰው
እንግዲህ ማርያም ትዋሰው
ማነው ሹማችን እኛው ሙላችን እያለ
አውራ አልባ እንደቆሪ ውሃ እየዋለለ ካላስተዋለ
ላይተያይ ላይደማመጥ
እጁን አጣጥፎ ቢቀመጥ
ግዞት አይሆንም አይደመጥ ...?
ግራርን ለታቦት የመረጠ
ዛሬ የሱ ተራ ሲደርስ ለራሱ መሆን ተስኖት ካረጠ
ይበለው ነውጂ እሰዬ
የማየው ቀን ናፍቆ ከስዬ
አዎ እንግዲህ ማርያም ትዋሰው
ጣብራግ ለታቦት የመረጠ ሰው
ለራሱ መላ ካነሰው
ከሰው መርጦ ለሹመት
ከእንጨት መርጦ ለታቦት ነውና
ከሰው መርጦ ለሹመት
«ለሺሞት» ሥልጣን ቢያጩት
ልብና ኩላሊት ይሆናል ይሏል እንደሳላይሰጥ ሥጋ
በቀንጣጤ የማይነጩት
ከሰው መርጦ ለሹመት ለሸንጎ ለሽምግልና ቢሰየሙት
የበቅሎ ማህፀን መንታ መንታውን ያትባል
የማርዳው ወዳጄ ሞት ይሙት
ቡቃያንኳ ዳዋ አይውጠውም
መከር እስኪከተት ባያርሙት!

# አስምአኒ

አስምአኒ ነገረ ፅድቅ
ዘያስተፌስህ ህሊና
አስምአኒ ከጌታ ሰማኒ
ዕዝነ ልቡናዬን ክፈትልኝ
ዓይነ ህሊናዬን አብራልኝ
የጠጠረው እንዲላላ … ውስብስቡ እንዲገራልኝ

አስምአኒ…
ከጌታ ሰማኒ…
ህያዊት ልባዊት … ነባቢት ነፍሴ ጋር አስታርቀኝ
እኔም ጠፍቼ እንዳልባክን
አንተም እንዳትርቀኝ
ዝንጉ ነኝ እረሳለሁ … ስባዝን የሚመሽብኝ
እስኪነጋም ትዕግስት የለኝ …
ዕንቅልፍ አልባ ነኝ
እንዳልል
ሌት የሚቀሰቅስ
ያሳብ መስተንግዶ አለብኝ
አጥግበኝ ከፍቅርህ ድግስ
አስበኝ በመንግስትህ
ለከፈልክልኝ ሁሉ … ሌላንኳ ማድረግ ባልችል
ምስጋና እንዳልሰስትህ

አስምአኒ…
ከጌታ ሰማኒ …
ፈቃድህ ይምራት ቃሌን … ላንተ ሰጠሁ አንደበቴን…
በፈተና ወድቄ እንዳልቀር አፅናልኝ ዕምላት ጉልበቴን
ትዕዛዝህን ጠብቄ ለትንሳዔ ክብር እንድበቃ
አንተ ብቻ ነህ ያለኸኝ የኔ የምለው ጠበቃ

አስምአኒ…
ከጌታ ሰማኒ…

አስምአኒ ነገር ፅድቅ ዘያስተፌስህ ህሊና
ወያስዝብ ልቦና
አንተ ብቻ በውስጤ ከብረህ
ስላንተ ብቻ እንድመሰክር
ላክልኝ ጰራቅሊጦስን
በመንፈስ ቅዱስ እንድሰክር
አጥግበኝ ከወይን ጠጅህ
ለሥጋ ወደሙ ማዕረግ አብቃኝ
ካሸለብኩበት ቀስቅሰህ አንቃኝ

አስምአኒ
በአክናፍህ አቅፈህ ደግፈህ
አውጣኝ ከባቢሎን እሳት
ተማርኬ እጄን እንዳልሰጥ ያይኔ አዋጅ እንዳያስተኝ
እባክህ ነፍሴን አስታውሳት
በወረት ተደልዬ በውዳሴ ከንቱ እንዳልረክስ
ሁለት ዛፍ ልውጣ ብዬ ተፈልቅቄ እንዳልፈረከስ
የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ
እኔ'ንኳ ሌላ ሌላው ሌላው ቢያምረኝ
ፆም ፀሎት ስግደትን ብቻ አጣፍጥልኝ
ለኔ የሚበጀውን አንተ ራስህ ምረጥልኝ
ፍታልኝ እንቆቅልሹን እንካ ሰላንቲያ አታስወድደኝ
መከራ እንደደራሽ ውሃ በጠራራ ጧይ እንዳይወስደኝ
እንደመልከ ፃዲቅ ካህን
ጠርተህ መርጠህ ባርከህ
ቀብተህ እንደቀደስከው
ይኽን አጉራ ዘለል ልቤን ገርተህ
ቃለህይወትን ስበከው

ምንጊዜም ካንተ ብቻ ነው ተስፋ
ምንጊዜም ካንተ ብቻ ነው ድህነት
ማንም እንዳንተ የለው
ሰፍ ተፍ ቢል ስለቱ የሆነለት እየመሰለው
የሰማታትን ክብር አስረዳኝ
በመላዕክት ዝማሬ አጅበህ
ጠግንልኝ የነፍሴን ስብራት
እሷም ሞልቶላት ትሳቅ
ምሉዕ በኩሊሄ ነሽ ብለህ
ምህረትህን አብስራት
እግረ ሙቅ ተኮድኩዳ በደረቷ ከምትድህ
በይቅርታ ዓይንህ እይልኝ
መቸም አንተን አይገድህ

ሰምዓኒ
ከጌታ ሰማኒ
መንግስትህ በሰማይ እንደሆነች
እንዲሁም በምድር ትሁን
አሁን!

መንበረ ማርቆስ
ታኅሳስ/፺5

# የማረሻው ሹም ሽር

«በሬ ምንህ ክፋ - ዳብሬ ምንህ ክፋ
አንዳ ሲገቡ ይገኛል ድፍድፋ
በጎሮም ሲዞሩ ይገኛል ጥፍጥፋ
ዳብሬ - በሬ ምንህ ክፋ»
(የህዝብ)

በርዬ ብሩዬ ሆሆ ... ሆሆ አያበሬው ዳብሬ
እምዕንተ ውእቱ ... እኔማ ባንተ ተከብሬ
ቅርሽም ... አነባብሬ ሰብሬ
እኔማ ... የልቤ ደርሶ ሶብሬ ... ነብሬ
እኔማ ... እኔውማ ልጅህ
ጥሬው ጥሬ ፈጅህ ... መደቆሻ መጅህ
እኔማ ባንተ ደርጅቼ
አደይ ለምለም ... ባለም ባጅቼ
እኔማ ባንተ ቁረንጮ
በነደሌ ቦራ ... ያደራ ጮጮ
ጡቱን ጡቱን ተብዬ ... በእንኮኮ ተቀማጥዬ
ፍዳዬን የኳሊት ጥዬ ... ዳብርዬ ብሩ በርዬ
እድሜ ላንተ ... እኔማ ወልጄ ስሜ ... በስሜ
ቀሰም ዘርቼ ቅሜ ... እንዳቅሜ
ንሽ ሲሆን ምንሽንሽ ... እየተለምኩ እየረጨሁ
ሲጠር ...
እንደገበጣ አረር ጠጠር ...
እየተወራጨሁ ለቅሜ
እኔማ ... አንደራፋህን በልቼ
እኔማ ... ባንተ አለትልቼ
ሐሳቤን ጅብ አስበልቼ
ማን አለብኝ ማን ... ማን ባገር አማን ...
እምቧ ... በሬን ቧ አርጌ ከፍቼ
እርቦ ነጣላዬን አጣፍቼ
ህይወት እምቡጥ ... እምቡጥ ልጅነቴን
አፈር እየፈጨሁ ... ውሀ እየተራጨሁ ...
በሰኞ ማክሰኞ አሳለፍኩት
ያፍላ እድሜዬን ለጋ ስልባቦት ...

በጮርቃ ጭርቆዬ እየጨለፍኩት
የቁም የቅምጥ ... ፋት አልኩት!
እድሜ ላንተ አያ ዳብሬ ... እድሜ ላንተ አይያ ዋለ
አድሮ ጥጃ ሆንኩብህ እንጂ ... ለኔማ ለኔ
ላንተ እንደራሴ ምስለኔ ...
ለኔማ ለኔ ... ምን ያልሆንክልኝ አለ?
ጫንቃህ ላይ ፌጥ ብዬ
እድሜ ላንተ አያ በሬው
ማባያው ሳይገድ ጨው በርበሬው
ማድጋው እንዳረበበ ...
ጋኑ እንደተንጠረበበ
ጥናቱን ቢሰጠኝ ... ባንተ ጠንቼ ጠረቃሁ!
ሺ ሁንልኝ እንጂ ነብሬ አያ ዳብሬ ...
እኔስ ለሰውነት በቃሁ
በሻኛህ በማኛህ ጠረቃሁ
ብታመም በዋንጫህ ... ባይበጅ መዳጫህ ታግሜ
አንጓህን ወዝህን መጥጨ
ወኔህን በውስጤ አዳምጨ ... አገግሜ
እኔማ ያን ... ያይን ወለምታ ሥብራቴን
ልብ ውልቅ ... ድምብልቅ ፍራቴን
ያን የታብዮ ኩራቴን ...
ኩር ኩር ሁርንጫ እብርቴን
እኔማ ... ያን የክፉ ዘመን ሰመመን
አይደርቄ ጐመን ...
የርኩስ ራእይ ቅሪቴን
ሤራ ስሪቴን
በሞራህ እየታሸሁ ... ራስ ቅሌን እያሞካሸሁ
ጠርቼ ላልጠራ... እየደፈረስኩ እየጓሸሁ
ዋሸሁ
ከጥንድ አይኔ ምስክር ... ከህሊናዬ ፍርድ ሸሸሁ
አወይ ባህሪ ጥልቆ ... እንደ አውሎ ንፋስ አዙሪት
እንደ የንግዴ ልጅ ... ምንግዴ ቅሪት
እሹሩሩ ቢሉት በድን
ቢጠየፋትም ጐድን ...
ከምን ሊያድን?
ንስክ ብስክስክ
አፌ ድስት ... አፉን አይከድን
እንኳን ለባለቤቱ ... ላባወራው በላይ
ጣራ አይዘልም ሽለላው ...
ምላሱን ጐርሶ ቢያብላላው
ሾተላይ ... የደም ቃላይ

ስርክርክ ... የጠላውን እስቲማርክ ...
የማርዳ ወዳጁን ሊያሳድደው
ደራ ባያንደረድረው ... ሌት እንቅልፍ ሲወስደው
በለመደው ... ዘራፍ ያጓደደው
መክሰር መንሰሩን እስኪለይ አንዳንዴ
ወንድሳ ወንዴ
ትርፉም ባይገባው የነገደው
ባሳብ መጐሰጡ የት ይቀራል ...
አቅምና ጥቅም ካልገደደው?
ህይወት የጧት ገበያ ሆነና
ተምኔትም ባይችል ትወና ...
ለቀልበ ደረቅ ወና
ተሸንፎ ከማነፍነፉ ... ይልሰው የለ ወይ ወናፉ
ይኸ የነብር እራት «ቀልቀሎ»
ጧፍ ሰፌፍ መብራት ...
ደባል ነበልባል ክንድ አክናፉ
አንድ አንገት ራሱን ችሎ ለመፅናት ሊንገታገት
የኔ ቢጤ አብጦ ቀብጦ አውራጅ ሊሸከም ቢለገት
ጀምበሯ ብትሰግድለት
ጃሎ መገኔ ጐራውስ ቢያረግድለት
ምን ዋጋ አለው ...?
ነጋ ክፈት መሸ ዝጋ የሚል ነጋድራስ ካቀለለው
ከየት ይመጣል የሚቀበለው...?
ግዳይ እንደ ሙዳይ ወጥነው ለምርኮም ባይታደሉ
ባይነበብስ ድርሳነ ገድሉ
ከስፍር ቅንጣት ካላጐደሉ
ርቆ መች ይርቃል ድሉ መደላደሉ?
እርካብና መጣብር ... ለጊዜው ቢያጥበረብር
አይን ሸብቦ ምላስ ቢያስገብር ...
ማን እንደነፍሥ ክብር
ማን እንደ ልብ ... ድልብ ግብር?
በልብ ፅላት ... በደም ሙላት የለቆጧት እውነታ
ተግባር ላይ ፈራ ተባ ብትል ለለቱ...
ለመድፈር እንኳን ብታመነታ
እውነት የማታ የማታ ግምባሯ መች ይታጠፋል
እውነት የማታ የማታ ክንዷ መች ይዘነጠፋል
የማታ ማታማ ምላስ'ንኳ ቢቀጥፍ ...
መልህቅ የጣለ ሐቅ አይነጥፍ
ስንል
ያመኑት ፈረስ በደንደስ በለኝ ልበልሃ ባይሞግት
አኮሌ አጥቦ ባይለግት አግቶ ሊያስገተግት

ጮጮ አቅርቦ ባያልበን
አንደርብ አረብቦ ሌት መጋዣ ሰሮ እስኪሰልበን
ግገን ካልነከስን ጉበን
ባይቆጭም ያንገበግባል ከራስ አይወርድም ጥፋቱ
በቀል ባያጭር ክፋቱ
እህና ... እኔም ይኼን ብዬ ነው አብዬ
ሀ ብዬ ፊደል ስቆጥር
ለምሽት ለማታ መክሰሴ ስተቶ ፈሰሴ
ሆሆ ... ሆሆን ስቋጥር
እንደ ዘኬ ለቃሚ
ገድለ ተአምርክን ልደግም ሳዘግም
የማረሻ ለዛ ቢታየኝ መልኳ ሆሆ ሆ በል አልኳ
ቢገባኝ ያፈር የፈረፈር ልኳ ሆሆ ሆበል አልኳ
ሳንዲት ሆዴ ሁዳዴ ለዚች ሞልታ ለማትሞላ ሞላላ
ሳንዲት ሆዴ ለእልኳ ሆ በል አልኳ
እድሜ ላንተ አይያ
እድሜ ላንተ ምን ጐድሎብኝ እኔማ
ምን ጐድሎበት ነፍሴማ
ወፌ ዘራፌ ዋነሴማ
ዘርፌ አክናፌ የቆላ ገራዶ ቅምጥል
አንተን አምና ተለማምና ... ያሳር ጐጆ ቀልሳ...
እንቁላሏን የትም ስትጥል
ስምክን ካፏ እማትነጥል
እኔማ እሷማ ምን ሊከፋን
የበሬ ገበሬ ልክ አይጠፋን
ብቻ ዛሬ ሞይዘሬ
ብቻ ዛሬ ልብ ስገዛ ስጐለምስ
አይነ ጉልላት ጉብል እክብል ላባብል ...
ባለ እጅ የጠፈጠፈችውን ሙሀዶ ስደረምስ
አስብቼ ቀጥቅጩ ልስብ
በተለቅቶ ሳስብ አራጣ ... እጣ እጣ ስከስብ ስሰበስብ...
እንደ ገብስማ ዶሮ ... ኑሮ መሮኝ ሽበት ወሮኝ ስበግን
ዓይን በመግለጫዬ
ጐጆ በመውጫዬ
የሚስጥርህ ቋጠሮ አልፈታ ብሎኝ ... በቁጭት እንባ ስዘግን
ይኸውልህ አያ ዳብሬ ...
ይኸውልህ አለሁ እንዳስቀመጥከኝ
አለሁ እንደፈጠርከኝ
መስቃ እንደበስቃ ዝሃ እያነቀ ...
ቃል እንደ ቁም ነገር እያጠረኝ
እልህ እንደግሥላ ድንጉላ እያወራጨ እያፈናጠረኝ

ግብግብ ይዣለሁ ስግትር ራሴ ጋር መዳረቅ
ቀጥ ብሎ ለመቅናት ... ተለብልቤ ለመታረቅ
ግን አይያ ... የሆነስ ሆነና
ክህነት ሊቀበል ነው ድቁና
አንገቱን ቁልቁል ቀልሶ ...
ድፍት የሚለው የኛ ቤት ቁና
ኸረ እባክህ ጠብቀኝ ... አያ ዳብሬ
ባክህ ጠብቀኝ ... አታጣብቀኝ
ባክህ ፈርጄን ... አታስፈጄኝ
ያ ሳትር ... ባክህ ስትረኝ አታጋትረኝ
አዛዥ ወርቁ
እርድ የለሽ ግርዶ ባለጋዱ
እርቅ የለሽ ስንቅ ባለምርቁ ...
ጠገራ ጥግረራ ብርቁ
አሹቆ ሊዘፈዝፈኝ
እንደሙት ባህር ታንኳ ... ሊቀዝፈኝ
ይድፋህ ብሎ ይማርህ ... ድንገት ሲያደናቅፈኝ
አፈፍ አርጌ ሊልፈኝ
ገስግስ ይለኛል ገስግስ
እስክስ ... ጓያ እንደሰበረው ሊያስነክስ
ቼ ቢሉኝ እንደመጋዣ ...
ለርሚጦ መግዣ
ጌታን ብፈራ ለለቱ ...
እንደ እሙሃይ ወለቱ
እንዴት ብዬ ልገስግስ?
እንዴት ብዬ? እኔ እማውቅ አንተን ብቻ
እኔ እሚገባኝ ሆ በል ግሥ
የግምሻንሽ ... ታህሳስ ድግስ
ምንስ ቸርነት ካንተ ብወርስ ... የሌለኝን አለግስ?
ወፈ ሰማይ ያለቀመውን
ጉራማይሌ የቃመውን
የጣራ ሶራ የተልቀመቀመውን
በውን ከውን እያለ ...
ኸረ ምን አለ!
መስሪ ያውሸለሸለውን ጨምዳዳ
አባ ምንግዴ ጐዳዳ ... ስፋ የሚለኝ ቀዳዳ
አይያ ... በምን እዳይት ልጣፈው
በምን ካሉስ በምን ክር
ገበር ነኝ እንጂ የውስጥ ልብስ
እኔ ከላይኛው የለኝ ምክር
ምንስ የድሃ ጉልበት ቢረክስ ...
ለምን ብዬ አባብዬ ... አያገባኝ ገብቼ ልዳክር?

ለምን ብዬ አባብዬ … ለምን ብዬ ለማይረባ ቀረጥ ገራባ
የርጥብ እማኝ … ማን ሊሰማኝ
የጅብ ቆዳ የተለጐመ አታሞ ልደርባ!
ምነው? … ምነው ምን በወጣኝ
ሥራ ብፈታስ … ቀድጄ እምሰፋው እንዳሰጣኝ
ሃር ፈታይ ሸረሪት …
እቴ ሙሽሪት
እሷ ያልጠቀመችውን …
አይታ የናቀችውን
ለምን ብዬ አያዳብሬ …
ነብሬ
ዝተት ለብሶ …
የጐታውን አብሶ
የሚጠማረር … የጋሜ ሚዚዬ እያለ …
መልኩን ልኩን የማውቀው
የሰው ፊት ያሳቀቀው … አንጀት የራቀው
የጐጆ ገመና ያደቀቀው
ብሰፋስ ብለፋስ … የሱን ቀዳዳ ሳልሸፍን
ግምባረ ቦቃ ባለምልክት
የጥሻ በጠልሻ ሙክት … ላይገለግል ላይመክት
ደሞ በቁም የበከተ ልከፍን?
አያ ዳብሬ … የሆነስ ሆነና
ክህነት ሊቀበል ነው ድቁና
አንገቱን ቁልቁል ቀልሶ …
ድፍት የሚለው የኛ ቤት ቁና?
ዘጠኝ ድስተፈጅ ወጥቀው …
በሽንቁር ጭንቁላ ጠቅጥቀው
እንደ እረኛ ቂጣ ሊባጠቁ …
የባጥ የቆጡን ቢያሽቃብጡ
እንደ ቀላዋጭ … አፍጣጭ አግቦ
እዳ ጉዱን በጉያ አንግቦ …
ሃር አስነጥፎ ቢነሰነስ
ማን ይሙት … እኮ አሁን አንተን ይገፍ …
ለማደጐ ድርጐ … እኮ ለሱ ልኩነስነስ?
ምነው ታዲያ አያዳብሬ … በልግ ላይቃም መከር
እንዲህ ሁኜ ስደናከር … ዛጥ ያለ እዳ ስነከር
ምነው አይያ ምነው … አስተንትኜ አስተንክሬ
ካንተ ጋር ባንድ መክሬ … በወንዘኛ በዘንገኛ አስመስክሬ
ለጥምቀት …
ለእምነቴ ምጥቀት …
በድረጪት ወጭቴ ነክሬ

ሥለ ነፍስ ለስቅለት ተዘክሬ
እንዳፍላ ጐፍላ አሸንክታብ ... አንገቴ ላይ ቋጥሬ
የማረሻው ሹም መስሪ አንጥሬ
እንደበካር መካር የጡት ልግ ... ጥንዱን ይዥው ባለዘልዘው
ምን ነበር ምሥለ ቃሉን ... የቅስት ውሉን ብይዘው?
እንደጣረ መንፈስ ንስሐ ቃል ... ሰንጌ እንዳላናዝዘው
በመልኬም ሆነ በልኬ ... አንተው ሆንክ በኔ እምታዘው
አደብ ድብዳቡን የምትገዛው ... ብራ ብራይ የምትነዛው?
          ምነው ታዲያ አንድ ብትለኝ አይያ
                    ነክህን እያለች ነፍሴ ስትባክን
          የጥገት ጋቴ ሳይመክን
          የሥጋ ስጋቴ ቢሰክን?
          ረብ ቢልንኳ ለጊዜው ...
          ሰከን ቢልንኳ አባዜው
ከፌሻሌ ብሶ ክልስ ... ውልስ ምን ያረጋል
ዳብሬ አባመጋል
በዋል ፌሰስ ... ባሳብ ፈረስ ቢናወዝ
          ዋለለ ምን ጉዳይ ሊሞላ? ባንድ ይረጋል?
ምናለ መላ ባላ ብትረጥበኝ
የወዲያኛው ገንዳ ዘማች እንደሁ ...
          አላዋቂ እንደወጠነው ሸማ እድሜዬን ያሳጥረዋል...
                    ላጥራህ ብሎኳ ቢያጥበኝ?
አይያ ... ዋንጫችን ጥቅል
ዘራችን ቅልቅል ... ደማችን እየቅል
ኑሯችን ምስቅልቅል ...
እዛና እዚህ ነጋ ጠባ ብን ብን ቢሆንብን
          ንፍገት ወንዝ ባያሻግርም
ቸርነት ብቻውን ... ጠይም አሳ አያስግርም
ሁሉም ቢሆን ያለሰው
ተነፋነፍ ነው ብንዋሰው ...
እጀ ጠባብ ነው ብንለብሰው
ብዬ እንጂ የምነግርህ
እኔና አንተማ አንድ ነን እምወድህ!
መሬት ላራሹም ቢባል ... አንጣራሽ መስሎ አጫራሽ
ቆራሽ አሰፍስፏል ጐራሽ ... ወፍ ዘራሽ
ወሮ ተወርውሮ ደራሽ ...
ቁልቢጥ እያለ እንድምቢጥ
          ባንተው ርሥት ግብር ፈራሽ ...
ፈጥኖ አውጠንጥኖ ወራሽ!

እንደ መስከረም እብድ ውሻ…
ጥንት በቀንጣጤው ያንቀራጨን አንሶ
የምን ንሰብሆ ነው ዛሬ … ቁዝሬ … ዋሾ ጉተና ነስንሶ
እኮ ዘንድሮም ሊጠምዱህ?
ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ ብለው በሥጋ ሊዛመዱህ?
ከመሸ ኩለው ኮልኩለው ጠልፈው ሊያሽመደምዱህ?
እኮ ዘንድሮም ሊጠምዱህ?
ለወለድ አገድ ግብር ጥለው ዘነጣጥለው ሊያሻምዱህ
እንደሰራ አይገድል…
የጀግና አውራቀስት ተወርውራ …
ድንገት ኢላማዋን ብትስት
አንድም ህልሙን ባይከስት
አንድም አቅሙን ቢሰስት
ሆኖብኝ እንደሆንም እንጃ ግር ብላኛለት ምሥጢሯ
ለምነው የህይወት ቅኔ … በእንቆቅልሽ መቋጠሯ
ባክህ አግራልኝ አይያ … ምን ይሆን የቃል ሰጠሯ
አገርም ስጠኝ ትል እንደሁ … የአብን ፀባዖት ተመራ
የምድሩስ አይታየኝም … ወልድ አለበት አኬልዳማ
የደም መሬት … የደም አውድማ
በመሥቀል በደመራ … በህማማት በከተራ
እኛን ወዳንተ ሊመራ … ድብ መስሎልሃል ደብተራ
ግን ግን አይያ … የሆነስ ሆነና
ክህነት ሊቀበል ነው ድቁና
አንገቱን ቁልቁል ቀልሶ …
ድፍት የሚለው የኛ ቤት ቁና?
ለማንም እብቅ ገለባ
ሰለባ ሁነህ ከምታነባ
አልገዛም በል አሁንም … አሻፈረኝ በል እንደገና
በሱ እጅ ከመደርደር … እንደሁዳዴ በገና
ቅዳሜ ሹርን ሳይገድፍ
እንደ ጉም አመልማሎ … ስበቀው በደጋን አድፍ
አልቅቲያም … ይኸን የድሜ ጭቅቅት ጉድፍ
ሌት ወፍጮ ላይ ተሰቅሎ
እህህ እያለ እያላዘነ …
የራሱን መከራ ይገርድፍ
የማረሻው ሹም ሽር … የኔ ምንሽር
ታውቅ የለ እንዴ … ወትሮም ቢሆን የኮሶ ልጅ
ያለ ኮሶ እንደማይሽር?
ደሞ ለማንም ውሽልሽል
የፉኝት ሽል

ደሞ ለሱ ቀን መስጠት
የመሰሪ ጉጠት
ይፍገምገም እንጂ ከማዱ
ይጥመልመል እንጂ ለእማዱ … እንደልማዱ
እንዳልተቆራ ቁርባ
ጋሜው ሹርባ
          ጉድ አዝሎ ነዝሮ … እንደሚግል
          እዛው ነፍርቆ ቢነግል
          ግንዝ …
          የደንቆሮ ንዝ
          አትወራጭ በለው … ቅርሻ አትራጭ
          የጥንዱት ልጅ … እንጥል ቆራጭ
ዝንተ ዓለም … በሱ ነፍሰህ ከምትነግል
ገለል በል በለው ያግል
ገለል ለበው ያግል
እና የኔ ጌታ … የኔ ምንሽር
አለሁ እኔም … ከጐንህ ነኝ አብሽር
ወትሮም ቢሆን የኮሶ ልጅ …
          ታውቅ የለ እንዴ ያለኮሶ እንደማይሽር?
ምረር የማረሻው ሹም ሽር
አብሽር የኔ ምንሽር

ሳባት ዓለም ዱብሬ
ጥቅምት 1987ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ግዝመ ሥውር መሬት ...
# አጋፔ ሐዋርያት

ምንም ነን አንድ ምንም
ሁሉንም ነን አንዱን ብቻ አናምንም
የምንቸረው የለንም እንጂ...
ከማንም ምንም ...
ነውር ስለሆነ ብቻ ዘለልነው
ግን ... ያለአንቀልባ በልብ አዘልነው
በመጣን ... እድሜ ምንም አላሳጣን
በጐን እንደሰው በምድር ...
እንደባህር ዓሳ ትን እስኪለን ጠጣን
እቁብ አምጣን ... አጥበን አሰጣን
ለሥልጣኔ ሳይሆን ለሥልጣን
አዎ ለሥልጣን ...
ከራስ ወዲያ ነፋስ ቢሉን ፋስ አለ
ለኔ ካይኔ በላይ ቢሉን ... ጆሮ አለ
በእጅ የያዙት ወርቅ አያደምቅ
ቢሉን ... ቃል ኪዳን ቀለበት አለ ...
ከሞተ አንበሳ የቆመ ውሻ ይሻል
ቢሉን ... ይመከር አስከሬኑን ሲያይ ይሻሻል
አፍ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ
ቢሉን ... አለን እኛ ላመነው ... አለን እና ስጥ ለጥ
የት ናችሁ ቢሉን የትም
ጥግ የሌለው ፍጥረት ውስጥ እየኖርን
የማንንም ለማንም አንሰስትም
ከበጀው ያውጀው
ካልወጀው ፈጀው እየሆነብን
ነጋብን ጠባብን ምን አለብን
አላጠባን አላለብን
ለመብረር ምን ክንፍ ይሻል
ዕድሜ ላሳብ ፈረሰኛ
የነቃ ባያመረቃ ... የናፈቀም አርፎ አይተኛ

ምን አለህ ቢሉኝ ምንም
ስመጣም ምንጨን አላውቀው

ስሄድም አልተምንም
አጋፔ ... ኑሮ
አጋፔ ... ዕድሜ
አጋፔ ... ፍታት
አጋፔ ... ሳታት
እንኳን ፊትም ሞኝም አልሳታት

## አጋፔ

ሁሉም ባለለት ያለምንም
ምንም በሌለበት ሁሉንም
አማካይ ቢሽ
ዋሹ
አካፋይ ቢሉ ... ያውለዎት
መስታዎት ፊት ይቁምና
ምስልዎን የሚያሳይ መታዘቢያ አለልዎት

ነጋሪት አያስፈልግም
መቸም እንደልቤ አድራለሁ ብሎ
ምንገድ ያሰማራ ቀልብ
ያንጀት ለሆድ አይነፍግም
ከናፈቁት መቸም አይርቁት
ከጠሉት መቸም እየጠለሉት

እንዲሁም እንዲያም እያለ
ሁሉም ራሱን መሰለ
በስፋቱ ልክ ስፋቱን ...
በቸርነቱ ውስጥ ክፋቱን
በልማቱ ውስጥ ጥፋቱን

ሁሉንም ቀን እየገለጠው
ሁሉንም ሌት እየለየው አዋዬው
ሄድንበት ሽቅብ በእንቅብ ...
አለት በወንፊት ስናንቀረቅብ
ናኘነው ቁልቁል ...
ልንጠነቁል

ሰገርን አግድሙን
ፍቅር ዘውዘው መውደድ ሽሙንሙን
እና ... ምን ይሁን

በታየን ፈሰስን ... ባልታየን ረጋን
ሁለት ሆንና ... ጥንድ እያወጋን
ምንም ብንፈራ ... ፍራትን ሰጋን

መጥምቁ ዮሐንስ
ጥር 95

# ውድነሽ በጣሙ

እቴ እንዴት ከርመሻል
ውዴ እንዴት ይዞሻል
የሙታን ሰገነት
አፈሩ ድንጋዩ ... የመቃብር ዓለም
የቀብር ቤት እምነት
እንዴት ነው ቅዳሴው ... ውዳሴ ማህሌቱ
እንዴት ነው ገበያው ... መስፈርቱ ስሌቱ
ከዚህ ከኖርሽበት ሁሉን ካየሽበት
ከሰው ካራዊቱ ከቀን ሰራዊቱ አለው ይሆን ነገር
በአለሙ ስጋ ... በሰጠን አእምሮ የምንለይበት
አንቺ ካለሽበት
አለወይ በዛብህ ያ መከራ ትርፉ
ቀይ እዳይት ሽማ ባለ ጥበብ ዘርፉ
ምን ይላል አንዳንዴ
ያለፈ ትዝታ ድንገት ሽው እያለው
እያንጠራወዘው እየወዘወዘው
የልጅነት ስሜት ግለቱ ንዝረቱ ግርሻ ግርሻ ሲለው
ቀዞ ሲያስተክዘው
አንዳንዴም እንደሰው እንደማንኛው ሰው
ግራ እየተጋባ እያደናበረው እያዥበረበረው
ቅጡን እያሳጣው ሌላውን አክብሮ
መድፈር ሳይሆንለት ብይን ሊያደላድል ራሱን ሊቀጥፍ
ምን ይላል እንዳንዴ
ከራሱ ተፋልሞ
ከራሱ ተጋጥሞ
ልፊያ ከንፈር ሽሚያ
አፍ ገጥሞ ጨዋታ
ደሞ ልቧን ሊቀምስ
ጠዋት ማታ ሲታመስ
እንደ ጭዳ ዶሮ ቆለምመው ጥለውት
ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ እያንሰፈሰፈው
ልብ ወዳጁን አይስት

ሰብለ ሰብለ እያለ
ስሟን እየጠራ በስሟ እየማለ
ስንቱን የቅኔ ቤት ስንቱን ቤት ዘረፈው
ስንቱን ነይ ነይ ያም በሐሌ ገደፈው

ምን ይል ይሆን አሁን
ያኔ ተው ስትይው
ከፈቃድሽ ወጥቶ
ያ የፈራው ፍቅር ሰብለን ተመስሎ
ፊት አልፎ ጠብቆ በድንገት ሲልፈው
ተፀፅቶ ይሆን?
እናቱን ገፍትሮ ከፍቅረኛው ይልቅ የራሱ ፀንቶበት
እሷን ላውሬ ትቶ ጉሮ ሊያደላድል
ያርባ ቀን እጣውን አድሳባ ገብቶ
አራዳ ገበያ በሌላ ሊለውጥ ባልታደለው እድል

ፈርቶ አሽቶ ሊያመልጥ
ቶሎ ቶሎ አፍቅሮ ... አምሮቱን ሊወጣ
ባሳብ ብቻ ሲያስልጥ
አባይ ፈረሰኛው ፋኖ አባጆቢራ
ተከትሎ እስኪያንቀው ደፍቶ በጢንቢራ

መቸ ተከተላት
ውድነሽ በጣሙ ጓዳ የገባሽበት
የናት አንጀት ስለት
ያ ቅኔ ዘራፊ ያ ድምፀ መረዋ
ምግባረ ታብዮ ባይኖረው ... ሲመካም ባናየው
ሰው በህይወት ሲኖር
በአይን በጥርሱ እንጂ በልቡ አይለካም
እንዲች አይነካም
ካብ ነው የካብ ልጅ ካም

ውዴ ... ታውቂያታለሽ ሰብለን
ያቺ ሰብለ ወንጌል ቃለ ህይወት ተክል
ጥብቅ ያምላክ ክልክል
አንቺን የምትመስል
አንቺን የማታክል

አወቅሻት?
የልጅሽ እጮኛ የቃል ኪዳን ሚስቱ
የሳቅ የምሬቱ የጋሻ መሬቱ
የድሜ እራብ ስስቱ
ጋነ ገብ እርስቱ

የሷ ቀጥ ማለት
የልቧ ቅንነት
የምነቷ ፅኑነት
እኩያው ጠፉና
በፊት አውራሪ ቤት በነ ጦር ባፊና
ባሸከር በገረዱ በቅጥር ታፍና

እንደ ሸምብራ እሸት ሁሌ ተጠርጥራ
የሆዷን በሆዷ ያንጀት ባንጀት ቋጥራ
ስትፆም ስትፀልይ ባምላክ ፊት ተሰምታ
ላንቺ ልጅ ተሰጠች በሱ ተገምታ
ለካ ትልቅ ኖሯል
ለካ ክንዱ ከሯል

ያቺን ትመስል ልጅ ለሱ ከተሰጠች
እሱም አላነሳት እሷም አልበለጠች
ብቻ በልጅሽ ጦስ
ስንቱ ገደል ገባ ወረደ እንጦረጦስ
እሱን ተከትለን እሹን ብለን ስንሄድ
ምን የቀረን አለ ያላየነው ነገር ያልገባነው መንገድ

የነ አበጀ በለው የልቤን ልብ በል
የሞት ሞት ጣረ ሞት በኔዋ ሊቀበል
እራሱን መቻያ አንገቱ አይል ዘምበል
እንባው አይል ከምበል
ሁልጊዜ ተለፍቶ ተረግጦ እንዳቅማዳ
ና ውጋ … ና ቅዳ

የባላገር አንጀት ከምራን ይጠናል ብሎ ካስጨከነው
ያው ባለቤት አይደል መርቆ የካነው
አንድ አበጀ በለው
አበጀ እንጂ አበጀ
ሁልጊዜ ባርነት ወትሮስ ለማን በጀ

አያቴ ስይቴ
እምዬ ልበልሽ ወይንስ እመ እምነቴ
ውዴ ውዴ ብዬ
በፍቅር አባብዬ
ላጫውትሽ የሆዴን
አንጀቴን ገረዴን
አንጀቴ ዘመዴን

ይኸውልሽ ውዴ
ሁሉም እንደሰጠው እንደ አቅሙ ቢፈስም
እኔም እንደጐኔ እንደመረዳቴ ብሰጠው እንጂ ስም
ማንንም አልከስም
ማንንም አልወቅስም
ቢሞትብኝ ብገል
እኔም አልቀበል ደም ጉማም አልክስም

«በከንፈሩ ከሚወሰልት ሰነፍ ይልቅ
ያለነውር የሚሄድ ድሃ ይሻላል» ብሎኝ ጥበበኛው ሰለሞን ንጉሥ
ዛሬ በቃላት ጨዋታ በባልትና በቀልድ ጉግስ
በገና በጡር እድሜ አልፈጅም
ምነው ቢሉኝ ከራሴና ከምኞቴ አስቀድሜ
ለማንም ምንም አልበጅም
ምኑን ከምን አርጌ ምን ከምን ሊወጣው
ዥጉርጉር ሆነና የኔና የአዲስ የነፍሳችን አገር
እንደው ጥፌን ጥፌን
ባንዱ ላይ አሳበን ባንዱ ላይ ለጥፈን
ያወጣል ባልንበት ዝም ብለን ታጥፈን
ቆመናል አሁንም ለድል ተሰልፈን በፍቅር ተጠልፈን
በዛው በወደድነው በዛው ባጌጥንበት በዛው ልንከፈን

ውድነሽ በጣሙ ማህፀነ አውድማ
ነፍስን ቀደም አርጌ
ዘርቶ እያበቀለ
እያቀላቀለ ደግሞ እየደቀለ
አንዱ አንዱን አይመስል
አንዱ አንዱን አያህል
እንዳው እህል እህል እህል እህል ብቻ
እህ እልል እንድንል

አዋጅሮ ለመላው አንዱን ውጥር አርጌ አንዱን እያላላው
አንዱን ጥምም አርጌ አንዱን እያሰላው
ስንቱን አሳየና ፍቅር እስከ መቃብር
በደም ቀለም እርስት በአፅም መቃብር
ታዳ ሀድስ ሆኖ ሀድስ አለማየሁ ከበቃ ሊያድስን
እህ ብለን ሰምተን ላደርነው ተስማምተን
ምን ያጐድልበታል ቆሞ ቢያወድሰን
ለሰርጉ ቀን ባንደርስ ምላሽ አስጠርቶ በጫጉላ ቢያድሰን
ብቻ የሱ ነገር የሱ እየተሰማኝ
ያኔ ጥንት ዱሮ እሱ ላለፈበት ዋቢ አድርጌኝ እማኝ
እኔም ሆንኩ ሰው
ጥም ግጥም ህቅ እንቅ ማይ ህይወት ጠማኝ

ቼ በለው በሚል ልብ ቼ ሰንጋ መዘዞ
አየሁት ለየሁት የድሜን እንቆቅልሽ
የሰው ምን አውቅልሽ
ባባይ ጣና ታዞ

አዎ ያን የስለት ልጅ
የሀዲስ አበልጅ
እቀፍ እንጂ አትንቀፍ ይለኛል በዛብህ
አንድ ልብ እንድትሆን አንድ እንዲሆን ቀልብህ
እያየህ እንድትሄድ ጆሮህ እንዲሰማ
ምላስህ ቀምሶ እንኳን የቅርብ ወዳጅ ጠላት እንዳይሰማ

እንደሰው ተፈጥረህ እንደ መላእክ ነጥረህ
በህገ ልቦና በፅዋ ልቦና በንፅህና ታጥረህ
ተበድለህ ክሰህ ብፅእና አውርሰህ በፅደቅ ታስሰህ
እንደጌታ እየሱስ መቃብር ደርምሰህ ደሞ ተመልሰህ
አልሞትም አልሞትኩም እነሆ ትንሳኤ እለተ ፋሲካ
ቤትህን ጐዝጐዘህ ጨፌህን ጐዝጐዘህ
በጠጅ በጮማ ጋርደህ ስታጋፍር
ኩራቱ እንኳን ቢቀር
በሰው ፊት አታፍርም ይለኛል በዛብህ

አንተም ኑሮ ኑሮ ያፈር ግብር አስራት
አንተም ሞት አለብህ ይለኛል በዛብህ
የሌላውን ተወው በቃ አንተና ልብህ ይለኛል በዛብህ
ነውር ተጠይፈህ ላብህን አንጠፍጥፈህ
ኩርምት በል ታጥፈህ ለደግማ ትንሳኤ በክብር ተጥፈህ
አንተን የቆጠረ ምድርን የፈጠረ
ምንም ይሁን ምንም ሲከፍልህ

ምንዳህን
አይቀር መቀነሱ የጓዳ ጐድጓዳ ያፈር ስፍር እዳህን
ውስጥህ እንዳይከስህ
ብቻህንም ቢሆን ፊት ለፊት አቅርቦ ህሊና አያርክስህ
እንደው ሌላው ቢቀር
ሰው ሰውንኳን ሸተት ለራስህ ለልብህ
ተወው ምናምኑን በአንድ መታመኑን
ወዶ መመንመኑን
ጥበብ መሸመኑን
እንደው ላንድ እራስህ እንደው ላንድ ነፍስህ
አንተው እንደራሴ አንተው አባራስህ
ይለኛል በዛብህ

ዛሬ ራሱን መክሮ
ኑሮ ተመክሮ
ዛሬ እናቱን ሰምቶ ባይኖቹ አይኑን አይቶ
እራሱን ለይቶ ዛሬ ልብ ገዝቶ

ለታይታ ሽንጌ በምኑ በምኑ
አብጠህ ተወጥረህ ከርመህ ከመቀርሸት
እንደ ዳማ ከሴ ማንም እጅ ገብተህ ለምች ከመታሸት
በሞቴ ነውር እፈር አጉል አትዳፈር ይለኛል በዛብህ
ያለፈውን ትቶት አረፍ ብሎ አይቶት ጠንቅቆ ለይቶት
እሱ ከመከረን ቁርጥ ነው እንግዲህ ዋስ ጠራሁ ብእሬን
ጉራዴው ሰው በላ በሳንጃው ይሞክረኝ
ምን አፎካከረኝ ምን አከራከረኝ

ሰማችሁ እናንተስ ያገር ወንፈልተኞች
የብእሬ ቀለም ብራና ጉዳተኞች
ላፍ ብቻ እንጂ ያውቃል
ያንጀት የት ይርቃል
ሀቅስ ምኑ ያንቃል
ሀሴት የት ያወድቃል

ካልቋጠረ በቀር ልብ ምኑን ሊሰጥ ምላስ ይመርቃል
ሀዘንተኛስ ቢሆን ምን እጅ አለውና ደረቱን ይደቃል
ብቻ ብቻ ሁሉን እሱ ያውቃል
በህልም አለም ቅዤት ጠድቆ ለመዋዠት
እንደው ባሳብ ብቻ በምኞት ከማርጀት
ደሞ እዛው ሶስት ክንድ
የካበውን ሲንድ ገላ ሲሆን አፈር
እንዴት ማፈር ይቅር በስመአብ ስለፍቅር

ሲያምነኝ አመንምኘው
ሲወድ አናድጄው
እኔን ምን ሊውጠኝ እሱስ ሞቱ በጀው
ፀፀቱ ነው ደማው
ቼ ፈረሴ ዳማው
ቼ ፈረሴ ዳማው ቼ ቼ ሲኮለኮል
ዘራፍ ሲተናኮል

እሾህ ላጣሪና የስራ ለሰሪው
ግዳጁ ሲተረክ ቀሚስና ሱሪው
ኋላ ከማቀርቀር
ነውር እፈር በኔ ሞት ሌላውንኳ ቢቀር
ይለኛል በዛብህ ልክ ማታ ማታ
እኔ ሐሳቤን ጥዬ ቱማታ ስማታ

# እንደሰዶም!

ሞኝ አንግስ ተግቶ እንደሰከረ ፈትወት አናቱ ላይ ወጥቶ
የሚያደርገውን አሳጥቶ
ያለአባት አዳሩ ሲያወራጨው ...
መለኮት መቅሰፍት አውርዶ የሰው ልጅ በንፍር ውሃ
ሚሙቶ ሲቀልጥ እንደጨው ...
የነገሩ ምላሽ የጥፋቱ ቁርሾ የቅጣቱ ውርጅብኝ ...
ሂድበት ነው ሂጅብኝ ...
በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ምኑም ምናምኑ አለቦታው እየተወተፈ ...
ነውር እንደጓሮ አይደርቄ ጐመን ባዋጅ እየተከተፈ
ዓለም በቃኝ በራሱ ፈርዶ ...
ከፈንኳ ሳይበቃ መቀመቅ ገባ ተዋርዶ
ምን ግድ አለው ዲብ ኩሉ የፍትህ አምላክ እንጂ እሱ ...
ለሰውማ ራሱ ነው ዋሱ ... ልቡ ያመለከተው ነው ምሱ
ላብነት አነሳሁት እንጂ ሰዶምና ገሞራን ...
ጉዳዬ ከሰሜን ተራሮች ልጆች ነው ...
እንደድርጭት በስለው እንደባጬት ተሰደው
ያስከበሩት ደን አሞራን...
ከጀምበር መፍለቂያ ከጽዮን
ከቅኔ ቤት መርጌታ ... ኤዶንን እንደመቀነት
እስካቀፋት ግቢ አግዶ ግዮን ...
አለት እንደበቆሎ እሸት ፈልፍለው
ቤተ መቅደሳቸውን ንሰው
በፍቅርና በትህትና ተጋርተው
ሞኝ ባያፍር ዘመዱ ያፍር ብለው
ቁልቁል እንደጅራት ፍየል ይጠበቃል ማእረጉ...
ነገርን በወግ መርምሮ
ቢሆን ሎሚ ተሁለት አስታርቆ
እንደራስ ፈርዶ ... በቃ ጠብ በቃ ብሎ
በህሌ በማሳረጉ እንጂ ...
ዳኛ ፊት ማን ያረገው ነበር ባለሚል ...
ለሱንጂ ሰግሮ ስማችሎት ለሱንጂ ለማን ተሰይሚል

ከሳሽና ተከሳሽማ ግራና ቀኝ ነው መቆሚያቸው ...
ምሰሶው ... ቢሻው ከጭንቅ ሊያወጣ ... ቢሻው
ሊያዳፍን ምሶ ነው ...
ብቻ በቃን ...
ኢትዮጵያ እጆቿን የዘረጋችው ዛሬ ነው
ሌላም ጊዜ ካምላኳ ጐን አትለይም ...
ያሁኑ ግን ቁርጥ ነው
የትውልድ ጥንድ ምጥ ነው ...
ሞት አንገት ላይ ደረሰ ... ማህተብን ሊፈታተን
እኛው ቤት እምቦሳ ብለን ያደምነው
እልፍኞችንን ከፍተን ...
ለዚያውም እናቱ እንደሞተችበት ህፃን መሳለቅ ...
ተራው የእያንዳንዳችን ሳንቃ እስኪቆረቁር
አስረሽ ምቺው ሌቱን ሙሉ መደለቅ
ጆሮአችንን እንደአራስነት
አንጥፈን ከተኛንበት ...
ዓይን ባትና ተረከዝ ላይ ከቀረ እንደተተከለ
ምነዋ አቅል ሲጠፋ ልብስ አልተለከፈ
እኮ እንደሰዶም
በኮንዶም ...
ለድንግልና ባንታደል
መስቀሉን ተሸክመን ለመከተል ባንበቃ ...
ከቃል በላይ ምን አለ ከሥጋ ወደሙ ጠበቃ
ኧረ ጎበዝ ... ነገሩን ያልደረሰበት
እንደዋዛ ችላ ቢለው
ከዝሙትንኳ ታቅቤአለሁ ቢል ...
መርፌና ስለትን የመሰለ
የሚናደፍ ቡችላ አለው ...
እኛ በኃጢአት ነፍረን ስንንጣጣ ...
ዲያብሎስ አታሞ አስለጉሞ እየደረባ
ጉሮ ወሸባ
ከሚደልቅብን ...
ይብቃን በቃ ... ይቅርብን ...
ወልዱ ከማጣት በላይ ቅጣት ጋራ ሽንተረሩም ቢሞክረው
እንኳን እንደኛ ... እሱው በራሱ ይመስክረው ...
ጨውና በርበሬ ተጠይፎ የልቡን ለልቡ የሚመክረው ...
የቋንቋው ልሳን ርቆን ባይገባንም ...
ሳያጓድል በምስጋና ፈጣሪውን የሚዘክረው
አይበጀን በሚነክረው ...
እግዚኦ!

ነሐሴ ፳፮/፲፱፻፺፫ዓ.ም.

# ሹመት

ሹመቴ ... ሺ ሞቴ ...
እሱም እንደ ልቡ ... እኔም እንደአሞቴ
ባይልም ዳሞቴ ...
እንደክራሞቴ
ቢፈቅደኝ ... ሊያሞኘኝ ...
ቢያቅደኝ ... ቢመኘኝ ...
እኔ ምን ተዳዬ ... ሁሉም ያሻው ቢሆን ...
ስንቄን እና ትጥቄን ሳይሰጠኝ ... ላይሸኘኝ ...
ዓሜን ብዬ ካደርኩ ... ምን አለ እሚሳነኝ
አህዱ ለፍቅር ... ለሰላም ሽልማት
ምን አለ ልዕልና ... ከጣር ከህማማት ...
ዕድሜ እየነገረ ... ልብ እየሰገረ ...
እጅ እየጋገረ ... ቀን እየማገረ ...
ቢሾሙም ... ጥንስስ ነው
ሲመጡም ... እንጥስ ነው
ቢሄዱም ... ብጥስ ነው
ቢኖሩም ... ቅንጥስ ነው
እሁ ... ተነፈስኩ
ፈሰስኩ ...
እንደደም ባልረጋም ...
ካልተሾምኩ አልሰጋም

ለመለስ ዜናዊ

# ከናፈቅኩህ በቃኝ

በገናዬን ልቃኝ
ከናፈቅኩህ በቃኝ …
ፍቅርህ እየጠራኝ
መስቀሉ እየመራኝ
ጀምሬአለሁ ጉዞ …
ሰንሰል ተጎዝጉዞ …

ለኔ ልደታ - 94
ለእናትና ልጇ!

# ከወሎ ልጅ ውሎ

ከወሎ ልጅ ውሎ
አንድም ተወልውሎ አንድም አስተውሎ
ልጅትማ ልጅ ናት ...
የወንድ ልጅ ቅናት ...
  ስትስቅ ስቅስቅ ...
      ስታኮርፍ እርፍ ...
      ስትቀኝ ዝርፍ ...
እርግብግብ ... ዓይነ ርግብ
የንስሐ ምግብ ... የትንሳዔ ግብ ...
ዙፋን ነው ማህፀኗ ...
አብቦ ያፈራ ... በዘሩ የፀዳ
ልዕልት የጥበብ ስልት ...
የለይል የምዓልት ...
      ሲወዷት አንድዳ ... ሲጠሏት ታዝባ ...
      ጥዑም ናት ዝም ብላ ... የሕይወት ዘምባባ ...
      የበረሃ ተምር ... የደጋ ተአምር ...
      እምቡር እምቡር ስትል ... እንዳው እምር እምር
      ድንገት ሳይታሰብ ... ሰብሰብ እንደክምር
የተንሳይ ምሳውን ... ሳጉርሰው ወንድሜን ...
እንዲባርክልኝ ... ብዕርና ድምድሜን ...

ስስብሐት ስንዱ

# ምንም ነኝ ግን አማራ ...
# ለዚያውም ደሜ አረንጓዴ ...

ምንም ነኝ ግን አማራ ...
ሰዋሰው ... የሰው እኩል ...
በወለባ... የማልኩል
በስሜት የማልኮለኩል
ምንም ነኝ ... ግን አማራ ... የሰው አቻ ...
የማልንጠረበብ እንደ ቅምብቻ
ምንም ነኝ ... ግን አማራ ...
የፈጠረኝን አምኜ ...
በጐቴን ከተኩላ ጋር የማስማራ ...
አማራ ነኝ የጠራሁ ...
ኩራት እንጂ ሞት ያልፈራሁ
አማራ ነኝ መቃ አንገት ...
ራሴ ከብዶኝ የማልንገታገት ...
የሰው ጣባ ስር የማልለገት ...
ዙሪያ ገባውን ቃኝቼ ...
ትሻልን ከትብስ አገናኝቼ
አይበጆን ከነመናጆው ባህር ዙልማ ሸኝቼ ...
የቀኑን እያንቀራጨሁ ...
ደሞ ሌሊቱን እየፈጨሁ ...
ለጐጆዬ የታጨሁ ...
ባሰኝ ብዬ ያልጫጨሁ ...
በወለምታ ያልተቀጨሁ ...
ልጄ ለሰማዕትነት ተመርጦ ባንዳ ባረር ቢቀነጥሰው
ሞተ ብዬ ... ደረት ጥዬ ፊት ያልነጨሁ ...
ባለፈው ያልተቆጨሁ ...
አማራ ነኝ ... ዐይኔን ብከድን እንጂ ... እንቅልፍ አላውቅም
ማማ ላይ ነው አዳሬ ...
ገና አባርራለሁ ዋኔ እኔ አለቅም፡፡
አይኔ ዳሽን ...
ልቤ ግሸን ...
ደሜ አረንጓዴ ...
ጓንዴዬ ጓዴ ...

ቃሌ ደም ... ምግባሬ ደም ...
እንኳን ለቃጣኝ ... ላሰበኝ የማልቀደም ...
ለትንሳዔ የምታደም ... የትም የማልጋደም
የትም የማልስደመደም
ማንም እንዳስመለከተው ... ያሻውን ስም ቢያወጣልኝ
ዕድሜ ላባይ ጣና ልጅ ...
ያንቀን የማስቆርሰው ድፎ ዳቦ አያጣልኝ ...
ሰምና ወርቅ ቅኔ ...
ጠኔ ያጥን መጥኔ ...
ይኸው ነው ሥርወ ውልደቴ
አማርኛ ነው ውጥኔ ...
አማራ ነው ምጥኔ ...
እንኳን ሰው ወፍ አልምጄ ...
እንኳን ሌላ ጥላ አጥምጄ ...
አንድ እግዚአብሔር ...
አንድ አገዛዝ ...
አንድ ሥርዓት ...
አንድ ባህሪ ... በነዚህ ባራቱ ቅስት ተገድግጄ ...
በሞትኩ የምል ምንጊዜም ...
በፍቅር ተገድጄ ...
ውሌን ሳልስት ...
ጉልበቴን ሳልሰስት
የልቤን በልቤ ቅስት ሳልሰድር ...
ተኝቼ የማላድር ...
ቼ በወሎ ፈረስ ... ካይኔ ልቤ ድረስ እያልኩ ...
አዘቦት አልቦዘንኩ ባል አላበልኩ
የቀላወጠው ወጥሮት ... ክንዱን በኔ ሊፈትን
ገና ሲያስተነትን ...
ከነገር ቀደም ሳይመክር በፊት ...
ባባቴ ጋሻ በናቴ ወንፊት
ወደፊት እንጂ ... ምን አለ ሌላ ...
እንኳን መብላት ... ማብላት ቀርቶበት ...
ለታጠረ በዕምነቱ ኬላ
ነፍሴ አውጭኝንማ ማን አስቦት
ዘር ከልጓም ስቦት ...
እንደ ቅዱስ ላሊበላ ንጉስ
ሹመት አይጠናኝ ... አይጠፋኝ ጉግሥ
ግብር ጥዬንኳ ባልደግሥ ...
እንኳን ለጠላቴ
ለወዳጄስ ቢሆን ደም እንጂ ሌላ አለግስ!

ድሃ ነን ብለን ስንል እኮ ... በሰው ልጅ ፍቅር ተጠልፈን ...
እህል ተጠይፈን ...
ለሞት ተሰልፈን ነውንጂ ...
የምንበላው ቢገደን ... መለኮት ባህሪም አላሳነሰን
ክፉ ጥፉ ብሎ እንደጨው ዘር የትም አልነሰነሰን ...
ቦረናና ተንታ ... ዋ ክምብል ያድርገኝ
ምን አገር ቢሰፋ ... እንዳማራ አይገኝ ...
ቢሆን እማይደል ወይ ጨዋታው ...
አገሩን ... ልብ ውልቅ ድምብልቅ
እስክስታ እሚያስመታው
እና አማራ ነኝ ... መከራ የመከረኝ
መስዋዕትነት ያጠነከረኝ ... ፍቅር የተዘከረኝ ...
ብፈራንኳ ፍቅርን ነውንጂ ... በሌላ አልጠረጠርም
ማንም እንዳሻው ለክቶ ... እንዳሻው ሊቆርጠኝ ቢያልም ...
ከልክ አልፌ አላጥርም
ጉራም ቢሆን ልቀናጣ ...
ስሞ ባያሳድገኝ ... ነክሶ እሚያነቃኝ አላጣ ...
ያው ወንድሞቼ ይመስክሩ ...
በናት ጡት ወተት ባይሰክሩ ...
የዛሬ ሃያ ዓመት ... ተክራርዋ ወርደውም ባልመከሩ ...
ግቻ ነክሰው ... ጦር ባይሰብቁ
ለዛሬዋለትም ... ባልበቁ ...
ለዚያውም ውለታ ሳይጠይቁ...
ትሁት ነኝንኳ ባልል ... እንደጠሎተ ሐሙስ ...
ሽቀንና ሰቀቀን ላራግፍ ...
ጦም ሽሬ የማልገድፍ ...
ግን አማራ ነኝ ... ማንንም የማላስደግፍ ...
እኔው ገምቼ ...
እኔው ዘምቼ ...
እኔው ሞቼ
ክፉ መሻቴንና ምኞቴን ተጠይፌ ስጋዬን ልሰቅል
ድፍት የምል እንደብቅል ...
ጣቢያ ሳላቀላቅል!
ኮርማ ሳላጻቅል!
በአቅል!
እና አማራ ...
የፈጠረውን አምኖ በጉን ተኩላ ጋ ካሰማራ ...
እስቲ ደሞ በልብ እንደመሙላታችን ... ለደራ ሳይሆን
ካይንህ ይፍሰስ ይልቅ ...
እንደው ላይን ለመድመቅ
ፈፋው እምቅ ...
በጠመቅ ...

አምባውን እንደሹርባ ... በክትር ሰርቶ ...
ለሽማግሌ ጥላ ... ለእምቦሳ መገሌ ...
ለልጅ ሰተቶ ...
መውጫው ጠፍቶን እንዳንንገዳገድ
ደሞ ጨዋታ ... አንድ ለመንገድ ...
እሰጠው ባጣስ ... ለምን ጦም ልደር
እሳትና ጢስ ጠፍቶ ... ከመንደር ...
ንሳማ ጐበዝ ... ንሳ ተነስነስ ...
ከስፍርህ ጐለህ ከሰው አትነስ
ንሳማ ጎበዝ ንሳ አታደግድግ ...
ወገብን ጠበቅ ... ባንጀት ድርብ ድግ ...
እንኳን እቁቡ ... እድሩ ፈርሶ ...
የወላድ ማህፀን ... በዋይታ ታርሶ ...
አማንስ ቢሆን ... ለተቀመጠ ...
እያላመጠ ... እየገላመጠ ...
እየተርመጠመጠ ... እየተዳመጠ
ዕድሜውን ይፈጃል እንጂ በከንቱ ...
ማን ይለዋል አንቱ ...
ንሳማ ጐበዝ ... ንሳ ተነስነስ
ከስፍርህ ጐድለህ ከሰው አትነስ ...

በሞቴ ስኔም እንዲያቀብለኝ ፀልዩልኝ
ከፊታችሁ ስቆም እንዳላፍር

ህዳር ስላሴ
ንግሥ ጊዮርጊስ

# አዲስ ዓመት

እንሆ ቅዱስ ዮሐንስ ፈሰሰ …
እንሆ ካህንም አፈረሰ እነሆ ከንቱም ቀሰሰ
እነሆ ቆንጆም ደበበ
    እነሆ ዋይታም ታበሰ…
እንሆ ሰጋር ተለጐመ
እንሆ ርቱዕ ተልጐመጐመ
እንሆ ዱዳ አንደበቱን ፈታ …
እንሆ ለዋልጌ ድፍድፍ …
        ለጨዋ ልጅ ፅራይ ገፈታ
አዲስ ዓመት
    አልዘለው ቆንጥር ካለ አልሻገረው ፈፋ …
አዲስ ዓመት
    እንኳን ጥንድ አይኔ ልቤ ድባቤ ይጥፋ …

ስተሰለፍኩበት

# ግሼ ዓባይ ግዮን …

የሠራዊት ጌታ እሱ አለ ምስክር …
የክርስቲያን አምላክ እነሆ ማተብ ክር …
ምንም አላጠፋሁ … ልሳሳት አልሞክር …
እንኳን ጥርኝ አፈር …
ነውርም ይዠ አልነጐድኩ …
እኔ ራሴ ብቻ …
እኔው ራሴ ነኝ ወድጄ የታጐድኩ
እነሱም አልጠሩኝ … እነሱ አልቀጠሩኝ …
ብቻ በውዴታ በሙሃባ አጠሩኝ … ያንጀት አናገሩኝ
አለመዱ ገሩኝ … አልፌም እንድሄድ … ድምበር አሻገሩኝ
ሄድኩበት አለቀ
ልብ ተጠለቀ …
ነፍስያ ወለቀ …
እንደየናፍቆቱ እንደመቃተቱ ይሰፈርለታል …
ማንስ ቢሆን ማንም … ያው ያመነው እንጂ
ማን ይደርስለታል …?
አታመካኙብኝ … በላይ እንደገዳይ ጥላዬ አትናኙብኝ
ዋኝታችሁ ላትዘልቁኝ … አታላዝኑብኝ
አፈር አልነካሁም …
ምንም አልወሰድኩም …
ሰጥቼ አልወደድኩም …
ደሞም ደጅ ልጠና አላጐበደድኩም …
እኔም አላበድኩም
እኔስ ምኔ ድኩም …
ፈስሻለሁ እንጂ … ቀልጫለሁ እንጂ እንደበጋ ቅቤ
አንድ እንዳልተነፍስ ታፍኜ ታቅቤ …
ወዴት ነህ የማነህ የሚል በሌለበት …
ለመቼ ሊውል ነው ሃሞትና ጉልበት …
አዎና… ሄድኩበት

ልደታ ማርያም
ጥር - 1996ዓ.ም.
ለግሼ አባይ ግዮን

እኔ መዩ ...
ምንስ ባይ ... የምሸሸ ነኝ ወይ ...
(የበገና ድርድር)

# እኔ መዩ...

እኔ መዩ ...
የነፍሴ እንደራሴ ወርቅ እዩቤልዩ ...
እኔ መዩ!

እኔማ ገባር ነኝ ...
የብቻ ለብቻ የብራ ብራምባር
የበርዬ ግምባር ...
የላሞቼ ጌታ ... የልቤ መርጌታ ...
እኔማ ሰገል ነኝ ...
የሚያዚያ ወገል ነኝ ...
ደህና ሰንብት ማጣት ... ካንተ እሚገላግል ...
እናት የሰፋችው ያገር ልጅ አገልግል...
ቲም ብሎ ሞልቶ ... ላይል ፍንግል ፍንግል ...
ምንም የለኝ የግል!
እንዴት  እኔ እያለሁ ...
ያራስ ጡት ይደርቃል ...
እንዴት የጋሜ ሆድ ካንጀቱ ይርቃል?
ጥርስም ሳይከደን ... ውልም ሳይረሳ ... ልብም ሳይከፈል
ሁሉንም በደቦ ሁሉንም በወንፈል ...
መፍሳትንኳ የለም እንኳንስ መገንፈል!
... አለኝ ጉረቤት
«ሀ» ምግባረ ሰናይ የሚለኝ ቅኔ ቤት ...
እምዬ ተፈጥሮ ...
ለዚህ ክብር ያጨችኝ ... የሠራ አካላቴ ከሷ ተቆንጥሮ
እኛን ያበቀለ አፈርና ውሃ
እንዴት ቀለብ ነፍጐ ያደርገናል ድሃ?
አልተጋን እንደሆን
አልተባን እንደሆን?
እንዴት ነው ሰውነት ... ምንድንነው ሰው መሆን?
ለሌላው አርጄ ትኩሱን አብርጀ
በራሴ ፈርጀ ... ሆ በል ብል ወርጀ ...
ባንጀት መቀናጆ ... ከበርዬ ጋራ እኩል ተጠምጀ

ቀምበር ተሸክሜ በድካም ታክሜ
ወፍ ማልመድ አውቃለሁ … በሃሌ ዝማሬ…
ማሬ! ብዬ ማሬ …
ባልቀድስም ባልቀስ
በሥላሴ ፊት ነው የኔ መመላለስ
አንድ እሱን አምኜ ሰርዶ የምነቅል
ላገር ማገር ስሆን … ለድምበር ለጉበር
ሞፈር በመስቀሌ እንቅፋት ቢመታኝ …
ብወድቅ የሚያነሳኝ … እኔን የሚል አምባ አለ የማይረሳኝ
የሰው ብገነትር …
ህሊና እሚሰቅዝ … አለ የዕውነት በትር
ሳብ ገትር ባሳክር
ዕድሜ ሊመሰክር …
አልጕድልም ከስፍር …
ባልኮራ እንዳላፍር …
  እኔ መዩ …
ሽልም እንደፀደይ … መስከረም ጠባዬ
ከብቶቹ ሣር ጠግበው … ይሞላል ጠባዬ
ጕራ ተረተሩ …
ሰርጡ ሸንተረሩ …
በፍቅር ሲዳሩ
ክንዱን ተንተርሶ ያሸለበው ፋኖ ቸ በል ነው
ቸ በለው ነው ስንቁ … ለውሎ ላዳሩ
በዋዕይ እንዳይርድ … በሙቀት እንዳይቀልጥ
ካለበስኩት በደን …
ያን ጊዜ ይናኛል … ባንድ ጕን መኝታ ሳይበሉ መደንደን
ካጣህ በጉድ ወጣህ
አንድም ለላከህ ነህ … ወይ ለመለመለህ …
ካለህ ግን ሁሉ አለህ
ያኔ ነኪ የለም … እንኳን ሊያስደነብር
ባይሆን … ዛዲያ … ግብር …
ለዝምታ ሐሴት … ለልብ ምልአት ክብር
እናት ነው ወልዶናል
አባት ነው ደግሞናል
በህገ ልቦና ፀንቶ እሚያድር አገር …
በዓይን አዋጅ ተጠልፎ … ባይን እንዴት ይሞኛል
እንዴት ይለምናል
እጁን ቢዘረጋስ … ከልቡ መሆኑን … ልባም እንዴት ያምናል?
የፍልቅልቅ ቆንጆ
የጀግና ሰናፍጭ … የሁዳዴ ስልጆ

ይኸኛው በደዊ ... በጡት ሥር ጡር ውጋት ...
ያነኛው በስጋት ...
ለምን አንገት ይድፋ ...
ጋኑ የኛ ሁኖ ... የህይወት ጥንስሱ ... የኑሮ ድፍድፉ
እኔ እንጂ ወታደር ...
የወንዜ ዘብ ይደር ...
  እኔ መዬ ...
ያገር ጥቁር ሰማይ ... ቀጥ አርጌ ሳይደግፍ
ማነው በምን መላ ... እንኳንስ ድህነት
                    ተባይ የሚያራግፍ?
አዎ ወታደር ነኝ ... ያንጀት ገረገራ
ለአርማ ለአላማዬ ... በዕምነት የምገራ ...
መቸም የማላብል ... እንኳን ልቆነጥር ...
ወድጄ እማልጠግብ ... እንኳን ልጠረጥር
ውሎዬን ለደብር ... አዳሬን ለድምበር
ይኸ ነው ... ይህ ብቻ ነው ሳንቃው
                    የነፍሴ መግቢያ በር!
የአበው የቀደምት ... አርጌኝ መላክተኛ
ጌኤም ምንጣፍ አይዝ ... እንኳንስ ልተኛ
ሳድነው ስላልቻልኩ እኔ ለመግደሌ
ምስክር አያሻም ይኸው ነው በደሌ...
ወይኔ ወይኔ ወይኔ...
ወይኔ ወይኔ መዬ ...
ታዲያ በዚህ ዓይነት ... ምኑን ወርቅ ሆንኩት ...
          ልዩ እዮቤልዩ?
ይኸው ነው እንግዲህ ... ለዛሬ ይበቃል ...
የነገውን ደሞ ...ድምድሙ ጌፈሬ ...
ክንዴ ሞት አይፈሬ ...
          ባለቤቱ ያውቃል ...

ስመርጌታ ጌጡ
ቅዱስ ገብርኤል
ነሐሴ ፺፮

# አክሱም …
# የብቃት ስም!

የህያዋን ልሣን …
የሰማዕታት ድርሳን …
   አኩሱም … የብቃት ስም!
ያረጋውያን ምክር …
የነዳያን ዝክር …
የንፉግ ክርክር …
የጐጆ ፋክክር …
ማተብ ባንገት ሲውል ታሠረ ባንድ ክር!
በሦስትዮሽ ህብር …
በደሙ እንዲከብር …
ባመነበት ሊያብር …
ለሕይወት ሊገብር …
ህብር…
   የህያዋን ልሳን
   የሰማዕታት ድርሣን …
         አኩሱም … የብቃት ስም …
   ዕምነትና ዕውነት …
   ሰውና ሰውነት …
         አኩሱም … የብቃት ስም …
አንዱ ላንዱ ቆሞ …
   አንዱ ላንዱ ሞቶ …
ፍቅር ተሸምቶ … ብይን ተገምቶ …
አልሰሜንም አምቶ …
ብሎም ለራስ ጉዳይ … ብሎም ላንጀት ግዳይ …
ባይዘሩት ይበቅላል እንደበልግ እንጉዳይ …
   አኩሱም የጧት ፀሐይ …
የብርሃን ለሐይ …
   የግንባር ምስክር …
የዕምነት የፅናት ክር …
   የህያዋን ልሣን
   የሰማዕታት ድርሣን

አኩሱም ... የንጋት ስም ...
ባይን አይቶ ለይቶ ...
እህ ብሎ ሰምቶ ...
እንደሰም ተስማምቶ ...
ስውር የከሰተ ... ህቡዕ የገለጠ ...
ካሳብ ፍጥነት በላይ ... ቀድሞ ያሰለጠ ...
በነፍስ የታደመ ... ከነውር ያመለጠ...
ዕምነትና ዕውነት
ሰውና ሰውነት ...
አኩሱም ... የፅናት ስም ...
'ርጉምን ታግሶ ...
ንፉግን ደግሶ ...
አፈናን አንግሶ ...
በሦስትዮሽ ህብር ...
በደሙ ሊከብር
ባመነበት ሊያብር
ለሕይወት ሊገብር ...
አኩሱም ... የህብር ስም ...
ስርየትን ከፅርፃት ...
ፍቅርን ከይቅርታ ...
ንቃትን ከእምርታ ...
በህያዋን ህዋ ... በሰማዕታት ተርታ ...
እኩል ተሰልፎ ...
ፈተናውን አልፎ ...
እንደሰንደቅ ቆመ
ብቃቱን ጠቆመ!
ዝማሬውን ካዕዋፍ...
ቅኔውን ከቀን ጧፍ...
ማህሌቱን ከአፀድ...
ገድ አለን ግዴታ...
የህያው ውዴታ...
ከተፈጥሮ ታርቆ...
አሻግሮ ሲያማትር ... ሲመረምር ጠልቆ ...
ሲያስተውል አርቆ
ትንቢቱ ንግሩ...
የዕድሜ ሽግግሩ ...
በጊዜው ለሚዜው ...
ላገሬው ለወንዜው ...
አንደበቱን ከፍቶ ... ቃል አመሳጠረ ...
ሰማዕት በቀለ ... አኩሱም ሰው ፈጠረ ...

እንደወርቅ በሳት … በጋመው ነጠረ …
ደሞ አነጣጠረ …
        አለ አኩሱም …
በኛው ከኛው ለኛው …
        በኛው ስም … በኛው ስም …
ምድር ጦም አይደር …
አገር አይበደር …
ወራቱ መብራቱ …
እራቱ ኩራቱ …
ሠላሙ ፍራቱ …
በሽክላው ባራቱ …
ይጠገንለታል እንደስብራቱ …
ለነገ ብሥራቱ …
        አለ አክሱም
        በምፅዓት ስም …

## ምዕራፍ ሁለት!

እንግዲህ … ከእጅህ በጉንጭህ …
ኋላ እንዳይቆጭህ …
ምግባር እስኪያጭህ …
እንኳንስ ራብ አሞራ ይንጭህ!

በልደት ማግስት
በዓለ ወልድ ክርስትና
ታህሳስ ፺፮ …

# ከህሊና ልምሻ
# የዕምነት ክትባት ይሻል

ያመነ የተጠመቀ ቢድንም
ኢቅራዕ ሲባል ኪታብ ያልገለጠም
ጐኑ አይደነድንም
ንቃ ሲሉት በቁም ያሸለበም
ፅርዓትን አያድንም
በምንም ይሁን በምንም ...
የዕምነት ሚዛን የሌለው ... መቸም ቢሆን አይተምንም
እናም ...
ከተማሩና ከተሰማሩ ...
እንኳን ድልብ ትርፍ ... ወረት ያቃለጠ...
ኪሳራንኳ ማማሩ
እህል ውሃ ምን ቀን ቸግሮ ያውቃል ...
ዕውር አሞራ በልቶ እያደረ ...
ሰው መሆን ላሰበ እንጂ ...
ሰውነት ባስርቱ ቃላት ዕውነት
እንዳስር አውታር በገና ተቃኝቶ ካልተደረደረ
ድህነት ማለት ድህነት ነው ... አይኑን ገልጦለት ላየው
መውጫ መግቢያውን ላዋዬው
ካያያዙንጂ ካጠማመቁ
ካለት ድንጋይ ላይ አይደል ቤንዚን መፍለቁ
እንዲሉ የጥንቶቹ
ግሪኮቹ ...
እኛም
ዓባይም ቢሞላ
አለው መላ መላ
እንድንል...!
አይቶ ለይቶ ለመረጠ
ደክቶ ለክቶ ለቆረጠ
ከዚህ በላይ መንግስተ ሰማይ
ዋሸራ ቅኔ ቤትም አልሰማን ... ክርስቶስ ሰምራ እነማይ...

እስመ ዓለም ምሬቱ!

# የካህን ሱባዔ

እነሆ ዘማሪ …
　　　　የካህን ሱባዔ …
ካ'ዳም … እስከ ምፅዓት …
　　　　በፃድቃን ጉባኤ …
ከስብሐት በላይ ስም
　　　　ታውቅ እንደሆን ካህን
ምዕመን እባክህን
አለኝ መንፈስ ቅዱስ
　　　　ስሉስ ቅዱስ ስሉስ!
ለጋሽ ስብሃት ነፍስ
እኔ ላላናፍስ

ስብሄፈ-ህያው

# ሃበሻነት ምንድን ነው…?
# ሃበሻስ ማን …?

(የአንድ ኢትዮጵያዊ ምናባዊ ራዕዩ)

ሃበሻነት ምንድን ነው ብዬ ራሴን ስጠይቅ…
ሆደ ባሻነት ነው አለኝ ውስጤ።
ሃበሻስ ማን አልኩ
        ደሞ …እሱማ ባሻህ
        ባሰኘህ ባስመለከተህ …
        እስከደከመህ … እስከታከተህ …
የሚል ቃል ሰማሁ…
እ … ብዬ ከገባሁበት ያሳብ ሰመመን …
ቃል የሚለው ድምፅ አነቀኝ … አነቃኝ …
አንቀራጨሁት
        ብሎም እንደምርቅ አነቀኝ … አስጨነቀኝ
እንደበካር ምጥ ተንበርክኬ
        እስክፈለቀቅ ድረስ አስጨነቀኝ …
                የናቴን … የህቴን … የሚስቴን
        ወልዶ ማሳደግ ሚስጢር … ያባትን …
        የወንድምን … የልብን እንቆቅልሽ …
        የዕድሜን ምን አውቅልሽ
ሳትፈታ
        መንገድ አትግባ ብሎ አበክሮ አስጠነቀቀኝ …
ሃበሻ … ሃበሻ … ሃበሻ ቃሉ ውስጥ ተመላለስኩ
አወጣሁ አወረድኩ … አስተነተንኩ … ከለስኩ …
ሃበሻ … እንዳሰኘህ እንደመሻህ …
ሆደ ባሻነትን ሃበሻ ይንገርህ …
ለመሆኑ ማነኝ እኔ ብዬ ነፍሴ ጋር ተፋጠጥኩ …
        ማነኝ እኔ … ምንድን ነኝ …
የሌላው አስቆጥቶ … የራሴ የሚያደነድነኝ …
አዝኜ የሰጠሁትን አለመቁጠሬ …
        ባልበላሁት የሚያሳድነኝ …
ምንድን ነኝ …
ቀጠልኩ …

በአዕምሮዬ ውስጥ ችሎት ተሰየመ ...
አንቀጹ የሌለው ብይን ሊሰጥ ተወሰነ...
ከሳሽ በግራ ተከሳሽ በቀኝ ቆመ ...
ዳኛውም ቦታቸውን ያዙ ... የሚገርመው ግን
ሦስቱም ቦታ ያለሁት እኔ ነኝ ...
ተጀመረ...
ስምህን ተናገር ተባልኩ ...
መልሼ ራሴን ለራሴ ማስተዋወቁ አሳፈረኝና
ላፍታ ... ፀጥ አልኩ ...
ማነው ስምህ ...
ዝም ...
ስምህን አታውቅም ...
ሰርቆ እንደተያዘ ቀጣፊ እየተርበተበትኩ
« » አልኩ ...
ታውቀዋለህ ...
ማንን ...
ተሳከረብኝ ...
«ቃል» ...
ለካ ቃልም ይጨንቃል ...
ለካ ቃልም ያልቃል ...
ለካ ... ቃልም እያልኩ ባሳብ ማዕበል
እየቀዘፍኩ መነሻዬን ረስቼ ...
መድረሻዬን ትቼ
እንደአየሩ ፀባይ የሞት ሞቴን ተፈራግጨ ...
ልቤን ገዛሁ ...
ተመስጌን ብዬ በረጅሙ ተነፈስሁ ...
ሌላ የብርሃን ፀዳል ፍንትው ብሎ ፊት ለፊቴ በራ ...
ልብን መግዛት ... ሃበሻነት ምንድን ነው ...?
ልብን መግዛት ... ሃበሻስ ማን ... ልቡን የገዛ ...
ዋልያ ገብስ እያበላ የሚያሳድግ ...
ለባለጌ ጥቁር እንግዳ ባጭር ታጥቆ የሚያደገድግ
ሆዱ አገር አንጀቱ ድርብ ድግ ...
ሃበሻ ... ልቡን የገዛ ...
ሲማር ... በሰው ፊት እሳት ...
ሲቆርጥ ... ባገሩ ... በነገሩ ... በዘገሩ...
ብሎም በማገሩ ...
ሆኖ ሲገኝ ጊዜ ጉዳዩ ... ሙዳዩን ማየት
ጓጉቼ ስከፍተው ... ላይኔ ያው ኩሌ ...
ለልክፍቴ ... ያው ጨሌ ...

በቃ ... ሌላስ ...?
ሌላ ምን ያምርሃል ...
ሳይኔ ... ያው ኩሌ
ለልክፍቴ ያው ጨሌ
ብቻ ...
ቅምብቻ ካለህ ... ማጀትህ ውስጥ ስልቻህን
ቂም ካለህ ... ጭነትህ ውስጥ ቅምጣናህን
አልሰማም ካልክ ...
ጆሮ ገድፍ በጣም ጠንቶብህ
ደሞ ... አልበቃህ ብሎ ...
በሞትኩት ካልክ ...
ፀፀትህን በሞረድ እየሳልክ ...
ቅዠት መሰለኝ
የተነሳሁበት ሃሳብ ... ውሉ እንደጠፋ ፈትል
ልቃቂውን መዘርገፍ ቃጣኝ ...
ሃበሻነት ምንድን ነው ... ልብን መግዛት ...
ሃበሻ ማነው ... ልቡን የገዛ ...
እንግዲህ ልብን ሳይገዙ ሃበሻን
ማነው ምንድን ነው ማለት ያባት ቢሆንም
እንዳወዳደቁ ይጠባል ተብሎ ...
ሃሳቡን ሳልከተል ደንግጬ ተመለስኩ ...

ለሃበሻ ማስታወሻ
ሥላሴ-ህዳር/1995ዓ.ም.
ከመናገሻ

# ድስቱር

ልክን እንደሁ ቀብር ይነግራል ...
እስተወዲያኛው ... እስተመለየት ያሻግራል ...
ሁሉም በወደደው
በተቀፈደደው ...
ብሎም ደሞ በዛው ...
ሰው ጠልቶ በነዛው ...
ሰው ጠምዶ በወዛው ...
እስቲያንገዳግደው ...
ቀብር እንደሁ አይገደው ...
አለው መላ ...
ለገላ!
ምን ያጣል ያፈር ቤት
የምስጥ ጐረቤት ...
እያገላበጠ ... ደሞ እያቀለጠ ...
ደሞ እየለበጠ ... ደሞ እየቃበጠ ...
እንደቡሄ ጥንስስ ... እየበጠበጠ ...
አዛዥ በሌለበት ...
የራስ ያሉት ለታ ... የሚሰለጥነው ...
ምላስና ሰንበር ጨጓራና ጉበት ...
ያኔ ደብዛው ጠፍቶ ...
ስሜ ያሉት ሰበብ ... ቁጥር አስፈትቶ ...
አፍን አስከፍቶ ...
ምን አይሆነው አለ ...
ነዶ ከከሰለ ...
ባይመክትም ያመላክታል ...
የቆረጠውን እንደጨፈቃ ... ልጥ ሳይርስ ያክታል
እንኳን ሌላ ጥላ ገዶ ...
ሰማይ መሬቱ ተንዶ ...
የኔ ያሉት አንደበት ... ተሸክሞት በኖረው
ራስ ፈርቶ ... የራስን ሞት በራስ መርዶ ...
ለዚያውም መቀመቅ ወርዶ ...
እኔስ ካሁኑ ድስቱር ...
እኔስ ካሁኑ ስትር ...

ድስቱር ነው እኔስ አጥብቄ …
መጀን ነው ሆድ በቋጠረው …
ባንቀራጩው ባነጣጠረው
በገባው ባመሳጠረው …
እኔስ ድስቱር ተንበርክኬ …
ለዛች ቀን የድንግል ምጥ …
በሽልም እንድወጣ በአዋላጅ ተባርኬ …
ብቻ ለብቻ ተጋፍጦ … አማልዱኝ በማይባልበት …
ለምን ተዘናግቼ … ኋላ ኩበት ለቀማ ላም ባልዋለበት …
ልባዝን … ነፍስ ይማር እሚል በሌለበት …
የሞት ሞቴን
እኔው ደግሜ … ግቻ ነክሼ ላላዝን …
ለውሎ አዳሩ እንደሆን ዓይን እያለ ምን ይጠፋል …
ለውሎ አዳሩ እንደሆን እህ እያለ ምን ይከፋል …
ለውሎ አዳሩ እንደሆን እንቅልፍ አይንሳ እንጂ
ህልም እያለ … ምን ያለፋል …
የቀርብ ምራን ገረረ እንጂ …
እንደመለዘብ ቆርፍዶ …
በለዛ ሲያዋዛ አርፍዶ …
ወላጆቻችን በሰፉት ቁና ብንሰፈር …
ያኔ በምን ሰርዶ እንንቀል …
በማን በሬ … በምን ሞፈር …
እዚህ ያልኮሰኮስነው ቀድሞ አጥሮት …
ያላቅማችን ስናቀብጥ … ያለ እኩያ ስንዳፈር!
ወይ ንዳማ … አወይ ፀፀት …
ወትሮስ ከምን ይታደጋል …
የፈራሽ የሥጋ ለባሽ ርካሽ ምፀት …
የነፃ ገበያው ግርግር … የኑሮ ህቡዕ ንግር …
አንዱን ሲያሰግር … አንዱን ሲማግር …
ይኸው ነው የቀን ሽግግር …
ድስቱር
ለወዳጃው ለማንደጃው …
ለመሸኛው ለማገጃው …
ረከቦቱ በእጃችን …
ቀምበጡ ከደጃችን …
ዝየራው ሃድራው …ሉባንጃው …
የምኣና ሳንጃው
ድስቱር ላለ ተጐናብሶ …
ባጭር ታጥቆ ጥቁር ማቅ ለብሶ …
ሞልቶ እንዳይተርፍ ነውንጂ መስጋት …
አደብማ አለች ለፈለጋት?

ለማህሌቱ ለቅዳሴው … ለፀሎቱ ለድሎቱ …
ልብ አለ የአፀድ ደብር … ለጉባዔ ለችሎቱ …
ቅኔ አለ ለክህሎቱ
ወይ ጐራ ሁኖ … ወይ ለታመነው  ካድሞ
ጉተና ደምድሞ …
ሙሰብሐውን ስቦ ዳዊቱን ደግሞ …
በቸር ቤት ማን ለግሞ …
ስስት በፍቅር ጥንድ ዓይኑ ተደርግሞ …
ድስቱር ነው ሳይሰልሱ …
ክፉ ቀን መጥቶ ጤዛ ሳይልሱ …
መገን ነው መጀን ነው …
የዘወትር ምንዳው …
ባጭር የሚያቀረውን
ያለአቅሙ የሚያስከነዳው …
ባልተፈጠርኩ እስኪል ጭራሹን …
ኢምንትነቱ እስኪዳዳው
አሸን እስቲፈለፍል ገንዳው …
ፍግ እስኪያለመልምበት ጓዳው …
ማንም በራሱ ደጋን … እንደቆላ ጥጥ ተባዝቶ …
ማንም በራሱ ቅስት … ባነጣጠረበት ተገዝቶ …
ጢንጦውን እንደመክሊቱ መጠን እስኪጋራ …
ድስቱር ማለት ነው በጋራ …
የቀለጠፈ ተጠለፈ እንጂ … መቸ  ከልቡ አለፈ …
በታጠቁት መች ሆነ … ሃጋ ለይቶ በተሰለፈ …
እንግዲህ ልብ ይንገር
ድስቱር ካለ አገር …
ግድ ነው መተቃቀፉ … ግድ ነው ለመዋሃዱ …
ድስቱር አሐዱ …!

ስግሎባላይዜሽን
ሚካኤል ጥቅምት ፺፮

# የጎራው ወይራ ዝየራ!

ቢስሚላሂ ብዬ ልጀምር መደዱን
የሐርሽን ቀዳማ ቢያሳየኝ መንገዱን ...
ካላጣው ዋሪዳ ...
ኢልም እንደፍሪዳ ...
በልቶ ያሳየኝ ... የሩሂን ቐሪባ ...
ግለጥልኝ እንጂ ... ሞጥልልኝ አንተው ...
ደግሞ መሳቱ አይቀር ... ቀድሞ የቶበተው ...
አስረዱኝ ሸሖቼ ... የቁርዓኑን ተፍሲር ...
የኢማኑን ተውሂድ ... የሙሃባውን ሲር ...
የከዳም በረካ ... የኢልምን ጥፍጥና ...
አስተሳስሩኝ ኒካ ... በዲን ታጥባ ታጥና
ዱአዬ እንዲሰማ ... በዓለመል ዘራ ...
ያውጣኝ ከመናደፍ ... እንደጉም ናዜራ ...
ወለደል ኋሊሓ አይንሳኝ አውገረድ
የባጢኑ ዓይኔ ... ከሸፎ እንዳይጋረድ ...
ዚክርና ተስቢህን ... ጥንዱን ባንድ ገምዶ
ያግራልኝ ሐለቴን ... ነብስያን አጥምዶ!

ረመዳን ዋዜማ/፺፮

# ከነዓን ነው ዘንድሮ

«ቃል»
በቃል የነገሩንን እየሰማን
ለልባም እንጀራ አወጣን
ለለት ወስፋት መሸንገያ ... የጠይብ ልጅ ሆንና
 በገል የምንበላው ኩርማን አጣን
ማጣታችን መች ከፋ ነበር፡፡
 መገፋታችን ባሰንጂ እንደረጋ ወተት መናጥ
ጥበብ በማይሰራ ሸማኔ ግራ ቀኝ መዋከብ እንደመቂናጥ
ችግር ዓይኑ ይፍሰስ ስንል እኛ አይን ያለን ይመስል
 ያልተገናኘቶ ሆነና አራምባና ቆቦ ጠምደን
ውለን ባደርንበት ያይንህ ይፍሰስ ድርጌ ለምደን
 እሷኑ ስናንጋጥጥ
ባሳብ ሽምጥ እየጋለብን ...
ሳብ ሳብ እንዳለን
 ከግንባራችን ላባችንን ስናጥጥ
እየመሸ እየነጋ
እያደር እየተረሳ እያደር እየተዘነጋ
ኩርማው እያለ ሰንጋው እየተሰነጋ
እኛን እንቅልፍ አብክቶን
በህልም አለም ስንናውዝ
 የትል እሳት ያየውን
አይቶ በተራው ሊኛ
እንደኛ
ዓይኑን ገጥሞ ቅንድቡን ዘጋ
 አዳራችን ድብዳብ በዝቶበት ከነፍስ ቆፈን ሳያስጥል
እትት እያልን ...ሥንበጥስ ስንቀጥል
አንዱን  ስንጥል ... አንዱን ስናንጠለጥል
መሃል ቤት ሁለት ወደን
ሁለት አጥተን በጥንዱ ነደን
ወዲያ ወዲህ ተፈልቅቀን
ለዓይን እንጂ ከልብ ርቀን
በራሳችን ነውር አፍረን
በራሳችን ገመና ተሳቀን

ካንዱ ተጣብቀን
ላንዱ ከምፅዓት ወዲያ ርቀን
የጐናችንን ጠብቀን ወዲያ ወዲያ ሩቅ ናፍቀን
የልባችንን አይቶ መለኮት ጉልበት ነፍጐን
ምሥጢር አርጐ የራሳችንን
ምስጢር በልባችን ውስጥ ሸሽጐን
ጐድን እያልን ጐንለጐን ስንኳትን
እየለቀምን ስንበትን ውለታ ስናስተነትን
እንደፈረደብን
　　ሌላውስ ምንም አልነበር አንዲት ንብረት
　　　　　ይችው አይቶ ማደር ብትኖረን
እሷኑ ጋረደብን
　　አንዲት ንብረት ይችው ሰምቶ መቻል ብትኖረን
ጆሯችንን ጆሮ ነሳት
　　ከምትወደው አለያይቶ
　　　　　እንዳልነበረች
　　　　　እንዳልተፈጠረች
እስክትደነቁር ነገር ነሳት
ነገርም ቁም ነገር ሆኖ
ካንዱ ወስዶ ተቀብሎ
ዝፍዝፍ አርጐ አሳድሮ ለፋሲካ ዘመራ
እንደብቅል አብቅሎ
ይሰልቀዋል ያ ባለጠላ
ማመርም ባይኖረው
የቁም ሞቱን ፍታቱን
በቁሙ ተዝካር እያወጣ
እንደቅስሙ ስሙን እስኪያጣ ክንፍ አወጣ ...
ክፉ እጣ
ሲጠረጥሩን ሲያነጣጥሩን
በቀጋ ሳይሆን በዓይን በፊት ሲያጥሩን
በራሳቸው ግምት ሌማት ሲያበጥሩን
ሲገረድፉንም ሲሰልቁንም
ሲደልቁንም ሲያንደላቅቁንም
ቀጥ እንዳሉ ነው እነሱ ... እኛ ግን ገና አልቆምንም
ድሃ አይደለን ዘንድሮም እንድሃለን
　　በእጅም በእግርም እንደ ዝንጀሮ
　　ምን ይሰማ ይሆን ደሞ ጆሮ
እንዳልን እንደዋተትን
አቀበቱን ተያያዝነው
　　ዞሮ ዞሮ ምን ቢጠና ...
　　　　　ያው እዚያም እዚህም መያዝ ነው ብለን

ሁሉን ልንችል ተቀብለን
ምንም ሳናረግ ከማንም ምንም አለብን
ቀይ ባህርን አቋርጦ እሱ በሰጠው የሚስጢር ዘንግ
ከነዓን ፊት ለፊት እየጠራው
ዮርዳኖስ ፊት ለፊት እያጠራው
ልቀመጥስ ቢል ማን ሊያስቀምጠው
ጭን መሃል ገብቶ የሰማው እየቆነጠጠው
መውጫውን የመረጠ
   እጁ እንደቻለ እየቆረሰ
   አፉ እንደቻለ እየጐረሰ
እንደ ጉኑ ካላደረ
እንደ አቅሙ ካልተንደረደረ
እንደ ህልሙ ካልሰደረ
እንደተስፋው ካላደረ
ከዚህ የተሻለ
አገር አለ
ማንም ማላ ቢደረድር
ለኔ እንደ ከነዓን ምድር
የእድሜ አስራት እስራት እድር
የቀን ህልሜ የሌት ህመሜ ግድር
ከነዓን የምላትን አገር
ዝምታዬ ትናገር ...
ከእንግዲህ ቁልቁለቱን ደፍሮ
ሽቅብ ተንደርድሮ
ከነዓን ነው ዘንድሮ!

## «መጽሐፈ ጥበብ... »
## ቅዱስ ላሊበላ ንጉሥ

«ይህን ዓለም የምትገዙ መኳንንት ...
ጥበብን ውደዷት ... የእግዚአብሄርንም ቃል አስቡ ...
በበጐ ዕውቀት ... በበጐ ልቦና ፈልጉት ... »
**(መጽሐፈ ጥበብ)**

«በፃድቅ ላይ የሚናገሩ የሸንገላ ከንፈሮች ዱዳ ይሁኑ ... »
**(መዝሙረ ዳዊት)**

**አቤቶ ሰለስቱ ምዕት ...**
**አቤቱ ... ቤዛ አርድዕት ...**
**እነሆ ... የተአምርህን ርቀት ...**
**የብርሃንህን ድምቀት**
**የጥበብህን ጥልቀት ...**
**የማይገደብ ፍቅርህን ሙቀት ...**
**ይምር ያስተምህር ብለህ ... ወደህ መርጠህ በባረከው**
**አቤቱ ... እግአዚነ ዓለም ሥላሴ ...**
**አቤት ... እርቅህን በርቅ ቤት ... በዚች በምላሴ ...**
**ላንተም ለሰጋርህ ... ለኔም ለግላሴ ...**
**አሓዱ ሲል ዘመነ መሳፍንት ምዕራፉ**
**በልቦናው ሳንቃ ... ንቃ ንቃ ንቃ ...**
**በስሜ ይከፈት እዝነ ህሊናህ መስኮት በራፉ**
**በመሮህ በመዶሻህ ...**
**አንተ ስለሻህ ...**
**ከመነሻህ እስከመድረሻህ ...**
**ብለህ ብትታደገው**
**ውልደ ዛጉዬ ... ሥርው አገው ...**
**ቅዱስ ተብሎ ተመርጦ ...**
**ንጉሥ ተብሎ ተቀብቶ ...**
**በስመአብ ስለፍቅር ያለ ለት ...**
**ከደብረ አርያም ምስጢር ሲገለጥለት ...**
**ድምሩ ሁሉ ሰመረለት ...**

ቅዱስ ላሊበላ ንጉሥ ... መጽሐፈ ጥበብ ዘአምላክዬ
ያባቱን የዣን ሥዩም ... የናቱ የሕረወይላን ትሩፋት
ልደቱን በንብ ሠራዊት አደመቀለት ...
መቅደሱን በልቡ ... በፆም ስግደት ... ፊት በብሉይ ወጥኖ
በጊዜው ጊዜ እንደፈቃዱ አሰልጥኖ ...
ግሥ ገሦ ... ማህሌት አጥኖ ...
    እነሆ ቤተ ዕምነቱን ካንድ ቋጥኝ አለት ፈልፍሎ
        አቆመም ለዘልዓለም ...
    ሃሌ ሉያ ... ለኛም እንደሱ ... ለሱም እንደኛ የለም
    ሰማይ መሬቱን በቃሉ አጽንቶ ... ያዳም ዘር በሙሉ
    ባንቀፀ መስቀሉ ባንድ እንዲገናኙ አቀላቅሎ
ያለነውር ኑረው ያለ ነውር እንዲያልፉ
ተሰጠና ቁልፉ ለክብሩ ታጭቷልና
    የኢትዮጵያዊ ህያው ሰልፉ
የነቃም አድሮ መረቃ ያሸለበም ባነነ ከእንቅልፉ
    በመስቀል ኃይልነ
    በመስቀል ቤዛነ ...
    በመስቀል መድኃኒትነ ...
ቋጥኝ አለት እንደጠቦት በወግ በልቶ እየለዬ ...
የልቡን ባይኑ በብረቱ አዬ...
    ጥበብ ከቋጥኝ ...
    ችታት ከፊጥኝ ...
    ጽናት ከሙጥኝ
አገናዝቦ ...
ዲበኩሉን አመስግኖ ... የቀን ሰራዊትን ታዝቦ ...
የሌት አራዊትን አለዝቦ
መጽሐፈ ጥበቡን ...
ቅዱስ ላሊበላ ንጉሥ ... ተካነ ግዑዝ ማንበቡን
ተረድቶ አደረ የነገደ ህያዋን ... ህይወት ማበቡን
    አሰርቱ አሓዱ ... ከአለት ቋጥኝ ...
        እንደግራር እንጨት ... እንደታቦት ጠርቦ
    ላምላኩ ካይን ቅንድብ ቀርቦ ...
    ካለም ሳይለይ ካለም ወጥቶ ቆርቦ ...
        ላዳም ልጆች መናኸሪያ ...
        ከሥጋ ሥጋት መላቀቂያ ...
        አቅዶ ለነፍስ ማደሪያ
በመሶበ ወርቅ አቅርቦ የጥበብ ማዕድ ...
አለቀን በጥርኝ ዝባድ ... አላቆ ከድሁር ልማድ ...
    «ይህን ዓለም የምትገዙ መኳንንት ... ጥበብን ውደዷት
    የእግዚአብሄርንም ቃል አስቡ
        በበጐ ዕውቀት ... በበጐ ልቦና ፈልጉት»

እንዳለው ...
ላንድ ቅዱስ ኢትዮጵያዊ ...
ላንድ ንጉሥ ሰማያዊ ...
ለኛ አባት አብ ያደለው ...
ለመንግሥተ ሰማይ ቢያጨውንጂ መርጦ ቢያደላድለው
አባምን ግዴ ጐዳዳ ለሰለጠው ላጤ ምን ግድ አለው
ከዚያማ ... ኢትዮጵያዊ መልኩን
ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንዳይስት
አጥብቆ አለዋ ትጥቁን ...
እያመላከተ ምጡቁን
እየሰፈረ ስንቁን ...
ይመሰክር ዘንድ ድንቁን ...
ይናፍቅ ዘንድ የሩቁን ...
ተስፋ ያደርግ ዘንድ ፅድቁን ...
ብሩክታዊትን ከደራጐን አፍ ያዳነ ...
ትርጓሜው አራሽ ገበሬ የሆነ
ለቅዱስ ጊወርጊስ በስሙ፡-
ያመኑትም እንዲሰሙ
የካዱትም እንዲሰሙ
በማይሰለች በማይታክት
በማይወድቅ በማይመክት
በአምደ መስቀሉ በአምደ መስቀሉ መስሎ
ጥበብን በማየ ህይወት አብቅሎ ...
በብርሃን ሙቀት አብስሎ ...
አሜን ከእግዚኦ በቀር እንዲል ...
ለኩሶ አበራው ጧፉን ...
«እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ወደኔ ኑ» ብሎ ከጠራቸው
እሱን አውቆ ቀብቶ ... ያዝ አለው የብርሃን ቀንዲል
አቤቱ እግዚእነ ዓለም ሥላሴ ...
በኔ በባሪያህ ... በዚች በረከሰች ምላሴ ...
ባንደበቴ ጫፍ ቃል ከትበህ ...
ሥውር ኃጢአቴን አጥበህ
ምስር ብላም ባይሉኝ ምስራቹን ላለም እንዳበስር
ከፈቀድክ ...ውሃ በውሃ ላይ በሚሄድበት አገር
ሰምና ወርቅ ቅኔ በሚዘረፍበት ጉበር ...
ደምቆ በዕጣነ ሞገር ...
ግማደ መስቀልህ ምስልህ
እምዬ የግሼን ውሸን እያለች
ለልጆቿ ሳትሰለች
በምትማፀንበት ምኩራብ ...
እውነት ጠግበን እህል ስንራብ ...

ምን ይለኝ ይሆን ባዕድ … የጐራ ወዲያ ሰው ወሰንተኛ
ያለት ቋንቋ የሚተረጉም …
ልበ ብርሃን ልጉም
እንደዋለ ሊያድር እልፍ ብሎ ሲተኛ …
ሰው ነኝና ሰበብ ባይገደኝ …
የቅዱስ ላሊበላ ንጉሥ 11 ውቅር ቤተክሲያን
ለማቆም የ23 ዓመት ድካሙ ገደበኝ …
ፊተኞች ኋለኞች … ኋለኞች ፊተኞች ቢሆኑም …
ሰውን በልቡ ምልዓት እንጂ በእርሾው መነሾ አይተምኑም
ህልሙን ለወርቅ የሸጠ የመንፈስ ድህነታችንን
እንደነውር ቢቆጥረው … አንድም የሚያደርገውን ባያውቅ

# የናት ልጅ ወንድሜን

ቀን አፍስሼ ደሜን … ሰግሬ ቅዳሜን …
ሌት ፈታሁት ህልሜን … የመንትያ ዓለሜን
የናት ልጅ ወንድሜን …
በዚያም ሆነ በዚህ … ልኩን በማናውቀው …
ጠፍቶት መውጫ በሩ … መግቢያው ስለራቀው
አሳተችኝ ካላት … ከሷው ምድር ወርደን …
በበረት ተወልደን …
እንስሳት በረት ውስጥ በፍቅር ተጋርደን …
ምንም ቁፈን ቢሆን …
በፍፁም ሳይበርደን …
    ደሞ ጊዜው ደርሶ … ሁሉንም አይተነው
    ሁሉን ለይተነው … ሁሉን ጥለን ተውነው …
    በነፍስ ተወነው …
    ተፈፀመ ብለን … በመስቀል ዘጋነው …
    ቀብርን አወጋነው … ህልምን አተጋነው …
አበወልድ ቃሉ … የቀራንዮ በግ … የዚያ የመስቀሉ …
አፈሩን ዲንጋዩን … ሥጋንም ፈንቅሎ
ቅዳሜ ሹር ሌሊት እንደንጉዳይ በቅሎ …
ከባህሪ አባቱ ታዬ ተቀላቅሎ …
እንግዲህ ምን ቀረ … ወዶ ላፈቀረ
እንዳቀረቀረ … ዕድሜ እያነቀረ … ከተሰነቀረ …
    የናት ልጅ ወንድሜን …
    ቀን አፍስሼ ደሜን …
    ሌት ፈታሁት ህልሜን …
    ላይቆርጥልኝ ጥሜን …
    ሊያረክስብኝ ስሜን …
የሚል መንፈስ ሰማሁ …
የሱን አስታክኬ … እኔም ያለፈ አማሁ …
ከማንም አይደለም … ከራሴ ጋር ብቻ
ማተብ ባንገት ያምራል … ዳዊት በብብቻ!
    ምን አመጣህ ክራር … የቆንጥር መረዋ …
    አድ አቦይ ሠራዋ …

ሰሜን ጫፍ ቅርንጫፍ ...
የቆለኛ ወንጭፍ ...
የግሪሣ መንጋ ... ማማ ላይ ተቀምጦ ...
ባይኑ እሚጨፈጭፍ ...
አገር አይደለ ወይ ... የነፍስስ ቢጠና ...
ሞቶ ወይም መቶ ... ያኔ ልክ ይነግራል ...
አሥር ከዘጠና ...
ደሞ ሳዲስ ራዕይ ... እንደአዲስ ስልጠና...

ቀድስት ሥላሴ ጥር/95
ከፍቅር አዳራሽ

## «ጥበበኛውን አለማወቅ ገደለው»

መስፍን ነበረ
በቀለም ምትሀት የሰከረ
ውበትን በስዕል … እውነትን በቃል የመሰከረ
በሙዚቃ ቋንቋ የቀዘፈ
በዋለ ባደረ መጠን … እንደ ሰማዕት ገድል የገዘፈ
አጥቢያ በዘለቀ
ጀንበር በጠለቀ …
እንደተፍለቀለቀ
ለኛ ይበቃል ስንለው … ለራሱም ሳይበቃ «አለቀ»
ጥበብ ሲል
አትሰፋ አትሰራፋ ሲል
ሰብሰብ በል ሲል
ጠንቀቅ በል ሲል
ዝም በል ሲል
የነብይ ትንቢት ይመስል
የዛሬን በትናንቱ እያስታመመ
ነገን ዛሬ ላይ ሆኖ እያለመ
ልክፍታም እንደፈተለ … እንዳቀለመ
ደም ከፍሎ በቀዩ
በእምነት አድሮ በቢጫው
በአረንጓዴው ለመለመ
አሃ … አሃ
ደሞ በሰማያዊ
በዳዊት ኮከብ ምስል … ኢትዮጵያ ሰንደቅ ላይ
እስከ ዓለም ዓለም ታተመ
ማአስላማ
ግን … …
ማንን ሊያስከትል ነው … መስፍን የቀደመው
ማንን ሊታደግ ነው … በፊት የታደመው
ወስብሃት ለእግዚአብሔር …ወለ ወላዲቱ

እናቱን ይመስላል
የአባቱን ይስላል
ወንድሙን ያስባል
እህቱን ያስባል
አያቱን ይምራል
ለልጅ ይዘምራል
መሳ ያስተምራል
ቃል ይመረምራል
ቅኔ ቤት ይመራል
የተቆጣ እንደሆን … እንዳቅል ይመራል
አሁን ደግሞ አንተ አልኩት
ቅድም አንቺ ብዬ
የኔን ለሱ ትቼ
የሱን ተቀብዬ
በሞቴ አባብዬ
ልምጣ ወይስ ልቆይ የቱ ይሻለኛል
ከነበረ ይልቅ የሞተ ይለያል
ሙሌ አንዴ ይለኛል አብርሃም ወንድሜ
ቆሞ የሚጠብቀኝ እኔ ተጋድሜ
ሰፋ አርገው ቦታውን መቼም መምጣቴ አይቀር
ከሞት አያስጥልም ወትሮም ነዋሪን ማፍቀር
መስፍኔ ሽቅርቅር
እንደ ቡን እንደ ጫት ስትይኝ ቅር ቅር
የጠናብኝ ለታ
አለሁ አለሽበት ለፍቅርሽ ውለታ።

ስሰዓሊ መስፍን ሃብተ ማርያም
ቅድስተ ሥላሴ ጥር/፶5
ከፍቅር አዳራሽ …

# የምሥራች ተሰበረ

ተላከ ከሰማያት… ይኖር ዘንድ በምድረ ገነት …
በፍቅርና በሰላም … በቃለ ሕይወት ዕምነት …
ዘለቀ እንዳመጣጡ … ተከሰተ በዕለተ ቀኑ …
ታትሞ በቀለመ ወርቅ … ታትቦለት ሰቀቀኑ …
አድጎ ህልሙን እንዲከስት …
በስሎ ህልውናውን እንዳይስት …
ምኑንም እንዳይሰስት
ድካና ድምበር ሲያግደው…
ጃሎ ሊል በለመደው …
በሞቴ ሊል ለፈቀደው
አንዱን ጥንድ አርጎ አቀናጅቶ …
ይሰምርለት ዘንድ እንደወደደው
ለውሎ አዳሩ ጥልፍልፍ
ሰጠው ቁልፍ …
ላለፈው ለተከለፈው ትንግርት …
አነፀው ባንክሮ ትምርት …
ልደቱ መንፈቀ ሌሊት …
ድርጎው የትንቢት መክሊት …
መንገዱ የፅድቅ ፍኖት …
በዕውነት ያለ ሃይማኖት …
በመሻቱ ህዋውን እየቀዘፈ …
እየረቀቀ … እየገዘፈ …
እንደዋርካ ጥላ ተንዠርጎ …
የደከመውን አቅፎ …
ሳይሚገት ይረታል ይማርካል ነቅሶ
ነቅፎ …

ብሥራት ገብርኤል
ታህሳስ ፱፮
ሣር ቤት አዲስ አበባ!

# እምጽዋይሽ ሐረር

ቤት ለአንግዳ ... አርሒቡ ሐረር
በሙሓባ ... በሐድራ እንብረር ...
ሐረር በር ... ፈረስ መጋላ ...
ያ ሠላም ... ገላ ለገላ ... (ገላ ለገላ)
    እንደቶበት ጥላ ... እንደጀጐል አጥር ...
    አለች ሰፈር የለሽ ... ወርቅ አንጥፍ ስመጥር
    ለሣር ለቅጠሉ ... ቀድማ እኔን እያለች
    መቸም አትጠገብ ... እንኳን ልትሰለች ...
የሰው መወደዱን ... መደዱን ...
ገዱን ... ቀና መንገዱን ...
ቢያሳየው ሴቱን ... ቢያስረዳው ወንዱን
    ሓጃዋ ወጣ ... ሐረር እንጉዳይ ...
    ዕድሜ ለአባድር ... እድሜ ለአቦዳይ!
    እንኳን የሴት ወንዱ ... ያዕዋፍ የአራዊቱ
    ዝማሬው ያጠግባል ... ጥም ይቆርጣል ሰዓቱ
እንደልቡ አቅዶ ... እንደጐኑ ከሚያድር
የሰማይ መንገዱ ... ያስታውቃል በምድር
ሞትን ተጋፍጣ ... ኣናን ትፍራልኝ
በፍቅር ጠድቃ ... አድጋ ታፍራልኝ
    አቤት ቂምሓ ... አቤት ምርቃና
    ስታስቀና ...
    ሚዕራዥ
        የኡስታዝ ... የኢራዝ ሙዳይ ...
    እምጽዋሽይ ሐረር ...
        ሐረር እንጉዳይ ...

        (አዝማች)

ስቀን ተቀብለን ... ካልካደምነው ቆመን ...
ሰው ብሎ ሰው ወዶ ... ሰው ብሎ እንዴት ይመን
እንግዳ እምቦሳ አስሮ ... ያልናኘበት እልፍኝ
የወረርሺኝ ቤት ነው ... ያውም የልጅ ኩፍኝ

ምን ለሁሉም ቢጥም ... ለወራት ቢገጥም
ሰው አንገቱን እንጂ ... ማተቡን አይሰጥም
ባሩድ ሽታ ናፍቆ ... ካልቃጣ በአረር ...
ሠርግና ምላሽ ነው ... ዓለማያ ሐረር ...

ቢኢዝኒላህ
ኢንሽአላህ ከፈም!
ለአሹሬ ጨረቃ!

# ጌታ ሆይ ... ነፍሴን ባርካት

የጤናዬን ነገር አደራ ... የዘፍጥረቱንም ጭምር
ብቻዬን ችዬ አልቆምም ያለ ጵንፈ ዓለሙ ድምር
ብቻዬን ችዬ አልችልም ... አልፀናም ባንድ ራሴ
ድሃ አደግ ምን ቢተባ ... አይደምቅም እንደደራሴ
የሰጠኸኝን እንዳስተውል ...
የዓይነ ህሊናዬን ጉድፍ አንስተህ
    የነፍሴን መታዘቢያ ወልውል... በውል፡፡
ኩኬን አውጣልኝ ከእዝኔ ...
ሰምቼ ልብ አለማለቴ ነው የለት ተለት ማዘኔ
የጐደለኝን ሳላውቀው የጠፋኝን ሳልረዳ ...
ባሳብ ተኩስ እውላለሁ ... ሁሌም ስታኮስ በተራዳ ...
ደፈጣማ ለምኔ በደረት ማንጣጠር ...
የተሰለፍኩበት ዕምነት
    ምን ልክ አለው ልበል ለመጠርጠር
መቸም ምንጊዜም የማይገባኝ
        ምስጢር የሚሉት ነገር ነው ...
በህልም ያነጋገርነው ... በሐልዬ የተሻገርነው ...
ዘለለ - ዕለትን አትንሳኝ
በመከራ ሰዓት አትርሳኝ
እንኳን ወድቄ ደቅቄ ...ሳያደናቅፈኝ አንሳኝ
አፋፋኝ በእቅፍህ ሙቀት ...
ብርድ ብርድ ሲለኝ ነው የኔ ጭንቀት
አስጥለኝ ከሞት ግብ ግብ ...
እሱ አይደለም የኔ ግብ ...
    የኔ ጨርሶ መጨረሻ ... ያንተ ሰበር ሰሚ ችሎት ነው
    ስቅላት ቢፈረድብኝ እንኳ ... አንተ ስለባረከው ...
            ሳዳም ዘር ሁሉ ድሎት ነው
ምንም ይፈፀም ምንም
ካንተ መስቀል በስተቀር ሌላው አይታመንም
    ቃልህን ተከተልኩት ድምፅህ ደሞ ናፈቀኝ
    የልቦናዬን መስኮት ክፈትልኝ ...

ምንም ባለጌ ብሆን ... ማረኝና ...
ከጨዋ ልጅ ጋር ልቀኝ ...
ካይኔ አትራቀኝ ...
ያልበላሁት እያነቀኝ ...
ያላጠፋሁት አንዳንዴ ...
ከሳሽ መንፈስ እየላከ ... ያለነቃሽ እያሳቀቀኝ
አደቀቀኝ...
ጌታ ሆይ ነፍሴን ባርከኝ
ጌታ ሆይ ልቤን ማርከኝ ...
ለዘለዓለም ሎሌነት ልታጭ ...
እንደከብት ለምለም ባየሁብት ወርጄ ...
እንደከብት ሳር ከምነጭ ...
ምሬሃለሁ በለኝ በድንግል
የሕይወት ውሃ በውስጤ እንዲመነጭ ...
ባርክልኝ የሰጠኸኝን ... አጣፍጥልኝ እንደመላህ
ከአሐዱ እስተአሁን ... አንተ ብቻ ነህ ያልላላህ ...
ቃለሕይወት አሰማኝ ... በመላዕክት ዝማሬ አጅበህ ...
ምኩራብህን አሳየኝ ... በህያዋን ህብር ተከበህ
ወትሮም ቢሆን ልጅ ያላባቱ
ከቁምጣውና ከጉልበቱ ... ከስሜቱና ከደምግባቱ
መቸም ቢሆን ልዝለል ብሎ ... አንድ ቀን ቀብጦ ቢቃጣው
ያንተ ሚዛን እያለ ... መልኩን ቢስት ልኩን እንደሁ አያሳጣው ...
የማይሰፈር ስለካ ... ከማይደፈር ስፎካከር ...
በልግ የለኝ መከር ...
ድፍድፍ አላውቅ የጉሽ ጥንስስ ...
ያልሾምኩትን ሳስስ ...
እየመሸ እየነጋብኝ ...
ዓይኔ እያየ ዘጋብኝ ...
ጌታ ሆይ ... ክፍትም ብሆን የባለጌ ልቃቂ
ኮረት እንኳ ባልሆን የአሸዋ ዝርያ ድቃቂ ...
ቤት ለእንግዳ በለኝ በምሥራቅ በር ...
አንተ በሌለህበት ቦታ ... ሰማይ ተቀዶ ብሰፋ...
እንኳን ልሾም የማልከበር ...
የሰጠኸኝ ሁሉ ምሉዕ ነው ...
ግን እኔን የሚያብሰለስለኝ
እጄ የማይደርስበት ጀርባዬ ባልበላሁብት እያሳከከኝ
አወከኝ ...
መላ በለኝ አንድዬ ... አንድ በለኝ ፈጣሪ ...
ሌት አቁሞ የሚያሳድረኝን እንደኮከብ ቆጣሪ
ባርክልኝ ነፍሴን ... እሷ ናት የማር መሬቴ
የሳግ የደስታዬ ምንጭ የብሶቴና የምሬቴ

ጠብቀኝ ከማላውቀው አውጣኝ ከፍዳ ናዳ ...
መልአከ ሞት ነፍሴን እንዳይነጥቀኝ ... ዘንግቼ ሳልሰናዳ
ለክርስትና ወግ አብቃኝ ... ለሰማዕትነት ባልታደል
    ይቅር ማለት እንደሁ አይገድህ ...
በብርሃን ሸኘኝ ወደጽዮን ... አሳዬኝ የምዬን ፀዳል...
ከሷ መንታ መንታ ጡት ... የዘለዓለም ወይን ይቀዳል ...
ምላሴን ቆልፎታል ጥም ... ለቆብኛል የሳት ራብ
ቀላቅለኝ ከብሉይ ምንጩ ... አቅርበኝ ወዳንተ ምኩራብ...
ንዴት ስደት ሰለቸኝ ... የኑሮ አዟሪት አዋከበኝ
ጠልቶ እሚገስፀኝ ገደደኝ እንኳን ወዶ እሚክበኝ
    ጌታ ሆይ የነፍሴን ነገር ...
    ስንቱን ብዬ ልናገር ...
ብቻ ከዚህ በኋላ ...
ገላግለኝ ከሥጋ ስጋት ... ሰውረኝ ከሸክላ መላ ...

ስሰው ዘር በሙሉ
መስቀስ ኢየሱስ ድሬር
መስከረም/፺፮

# ኩኩሉ … አለ «ዲበኩሉ»

«በየጁ ወድመን …
በግሼን አምባሰል …
እንዴነህ ሰው መሆን …
እንዴነህ ሰው መምሰል …»
የድሃ ገመና ደጅ ይሰጣል ሲሉ ሰማሁ …
ዕውነት ነው ውሸት …
ወይን እሸት …
ሰው ሲወዱት ያብዳል እንጂ እንዴት ቅጥ ያጣል
እንዴት ያንቀጠቅጣል … እንዴት ባደባባይ ያሳጣል
ስም ያወጣል …
ሰማን … እኛም አብረን ኖርንና ከገቢር ተሰወርን
እንጂ በሃልዮ አብረን ተስማማን …
ውሃ እስኪጠማን …
ሰማን … የዘመን ትውፌት ተገለጠ …
ዓሳው ሳቢሳው እያለ ሳማው እያሚለጠ
የበረረው እያለ የሚንፏቀቀው አሰለጠ …
አይረባም ያሉት በለጠ …

ወድኖ!

# ወደሚቀጥለው

ወደሚቀጥለው
አለ የማጠብቀው አለ የምጥለው
የማንጠለጥለው
ኮተት ተሸክሜ ... ብወድቅ ብነሳም ...
እንኳን ለሥጋዬ ... ለነፍሴም አልሳሳም ...
        ጭራሽ ቃል አልገባም ... ነገን ስለማላውቅ
        ምን ይሆናል ብዬ ... አልችልም መጠየቅ
ሲመራኝ ስከተል ... ሲነግረኝ ስሰማው
እሱ ራሱን ሰጥቶ ... የኔን ልብ ቀማው
በፍቅር ሰክሬ ስሰግር እየዋልኩኝ
አይችሉ ቻል ሲለኝ ምኑን ችዬ ቻልኩኝ
        ያለመሰናክል ሰው ያላንዳች እክል
        ማንም ማንም የለም ... የልቡን የሚያክል
        አጋንንት አውጥቶ ... ስሜ ሞት ሳያስጥል
        ምን ሊያደምቀኝ ብዬ ግንጥል ጌጥ ሳንጠልጥል
እኔ እንዳሻኝ ልኑር ... እንደአመሌ ልደር
ወዳጆቼም እዩኝ ... በቅኔ ስሰደር...
አዳኝ ቆንጥር ፈርቶ ... ጭቃ ተጠይፎ
አይወረወርም ... ቀስቱ ደጋን አልፎ

ትንሳዔ ሚያዝያ ዓ.ም.

# አዎ ባላገር ነኝ

ዱዳ ነኝ ልጉም ...
ባገኘሁበት አፌን የማልከፍት መጪውን ስተረጉም
አዎ ዱዳ ነኝ ልጉም
ሞፈር ዘመት አገልግሌን ስለጉም ...
አዎ ባላገር ነኝ ልጉም ...
የናቴን እያንቀራጨሁ ... ያባቴን ሳልጐመጉም
ልብሴ አዳፋ ...
አንደበቴ ጐልዳፋ ...
አንዱን ሽቅብ እያወጣሁ አንዱን
ቁልቁል የማዳፋ ...
ሆ በል ብዬ ጠምጄ ሀ ግዕዝ ብዬ ተምሬ
አውድማ ለቅልቄ ላዳ ጥዬ ...
የመህር ፍሬዬን ከምሬ ...
የምሄድበትን መርምሬ ...
ማር መሬቴን የምመራ ...
የልቤ የጥምቀት አዝመራ ...
እሱ ሲያንቀላፋ እኔ ስታክት
ያኔ ነው ዘራፍ መዋጣ ምክት

መስቀል እዮሱስ
ግንቦት/፺5

# እንደቸርነትህ

እንደቸርነትህ እንቆቅልሽ ፍታ ...
ለቤተ መቅደስህ ... እፈትሳለሁ ግምጃ
እሰራለሁ በፍታ ...

ለልጄ እናት

# እልልል … እልልታ …

እልል … በእልልታ
ለቀራንዮ አምባ … ደሞም ለጐልጐታ
እልል በእልልታ

ከነገሱ እንዳንተ
ከታገሱ እንደአንተ …
መወደድ ካበ እግዚአብሄር
ለፍቅር ባለሚል … ዕውነት ህብረ ብሄር

ስዕስተ ስቀስቱ

# ቃል

ካስራ ሁለት ዓመት በላይ ያለን አገር ...
ፍቅርና ወሲብ ... የራሱን ይናገር ...
ሌላው ሳይጋገር ...
ውበት ሻተኝና ... ጦም ጀመርኩ እንደቀልድ ...
ጉልበት እንዳያንሰኝ ... ሰገድኩ እኔን ልወልድ ...
ለካስ በፀሎት ውስጥ
ቃል ኖሯል «አበ-ወልድ»

ጥምቀት/፺፭

# የጥምቀት ጨረቃ

ድፎ ዳቦ መስላ...
በብርሃን ማዕዶት በሙቀቷ በስላ ...
ካለፈው ተስላ ...
 በለስ ገጥሟት ዛሬ ...
 ፈታችው ቁጥሩን የዕድሜን ምንዛሬ ...
ተከፈተ በሩ ...
የምላስ ሰንበሩ...
 ያልጋው ... ያለንጋውን
 አብሮ ... እሚያነጋውን
ሰበብ ቀብሩን ምሶ ... ግባቱን ለፈፈ...
እንዳላንሳፈፈ ...
ታዬ ተረተሩ...
ተገልጦ ደብተሩ... ካልተውተረተሩ...
ወይም ካልገተሩ
ተስፋ ካልመተሩ...
ትላንትና ነገ ዛሬ ተገናኝተው
ያንጀት ወግ ጀመሩ... እኛን ለእኛ ትተው
ወራት እስኪገልጠው ... እንግዲህ ዝም ነው
 ዝምታ ይክተተው
የጥምቀት ጨረቃ ... ድፎ ዳቦ መስላ
በብርሃን ማዕዶት ... በሙቀቷ በስላ
ካለፈው ተስላ ...
በለስ ገጥሟት ዛሬ
ፈታችው ቁጥሩን ለዕድሜ ምንዛሬ

ስጀመር ነው ህያው ጉዞ
ጥምቀት ፃ፭

# ካየኸው በላይ ማን ይነግርሃል?

ካየኸው በላይ ማን ይነግርሃል
ከሰማኸው በላይ ማን ያሻግርሃል
ካበቀለህ በላይ ማን ይማግርሃል
ሌላ መጣ ቀረ ምን ያደርግልሃል...?
ብቻ ተመልከተው ማየትን አትተው...
ላንተ ቢጤ ድንጉጥ አሞት የከተተው ...
    ዓይንማ ዘመድ ነው ... ውበት ካልጠለፈው
    ዓይንማ ወዳጅ ነው ... ማድ ካልከለፈው
    ሁሉንም ሁሉንም ... ሁሉንም ባንድነት ...
            ሁሉንም አዋህዶ ...
    አይቶ ያሳድራል ... ለይቶና አዋዶ ...
ወዳጄ የልቤ ... እኔ ከራሴ አልፎ ...
በሰው እጅ ውሏል በፍቅር ተጠልፎ ...
ተባረክ ግን አንተ አሁንም ተባረክ ...
የሰማዕታትን ገድል ብቃት ለመተረክ ...
    መሄድ ያማረህ ለት ... ቅዘፈው በክንፍህ ...
    ብርድ ያማረህ ለት ... አውለው በእቅፍህ ...
    ይህን የሚፈታ ... ህልም አለ በእንቅልፍህ ...
            አንድም እንዳያልፍህ ...
እዬው እንጂ እንዴታ ...
ዓይንም  እኮ አንዳንዴ ... ይችላል ኩዴታ ...
እየው ያየኸውን ... ደሞም አመላልሰው ...
ሄዷል ያ ክፉ ቀን ወፍጮ የሚያሰልሰው
ሞክረው ግዴለም እንደ ዳንግላሳ ...
አንድ ነው ባንተ ቤት አንድና ሰላሳ
ባይሆን እንዳትፎክር
አትውጣ ከምክር ...
ያን ጊዜ ይወጣል ... ያንተ ዕዋ ዝክር ...
እዬው እስተወዲያው ... ወዲያ ወዲያን ዘልቆ
ማን ከልካይ አለበት ከፈጠረ አልቆ ...
    ቢቸርህ መስቀል ነው ... ቢመግብህ ቃሉን ...
    እነዚህ አይበቁም ... እነዚያ ያውቃሉን ...

ደጅም  ባትጠና አርያም ለመታደም ...
ካየው በላይ ማነው ፊት አልፎ ለመቅደም ...
አንተኮ የኛ ነህ
የረኛ መቆያ ... የለት ጢብኛ ነህ...
አፍህ እንዲጣፍጥ
ድምፅህ ሳይጐረብጥ ለዛህ ሳይሰነፍጥ
በብሂር ብሂር ... ብሂረ ህያዋን ቡራኬው ያለቀ
የጌታ ነፍስ ነህ ሥጋ ያሳወቀ ... ካባ ያጠለቀ
በስተምሥራቅ በኩል ጽዮን የፈለቀ ...
ቀጥልንጂ አንተማ ... ምን አቀማመጠህ
እንኳን ሰው ትልቁ ግዑዝ ካደመጠህ ልባም ካላመጠህ
ምን ግድህ ለወትሮው ምን ተዳህ ከጥንቱ ...
አንተ የለህ እዚህ ሥጋ ቤት ቆጠራ ከደምና አጥንቱ ...
ሌላ ነው ያንተ ዕዳ ... ሌላ ነው ያንተ አስራት
በስማም ብሎ አሐዱ ... ስብሐት ብሎ ብሥራት ...
ዋስ ሁኖ ማስፈታት ... ከሲኦል እስራት ...
ቃልማ ቃል ነበር ... አሁንም ያው ቃል ነው ...
ነገር ግን ችግሩ ማን ወዶ ያውቃል ነው?
ማነህ ካሉህ እኔ ...
የት ነህ ካሉህ ካይኔ ...
በላቸው ለጊዜው ...
ገስግሶ እስኪመጣ የጋሜ ስርሚዜው

ታህሳስ ፳፭/፺፭

እንግዲህ፡- የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ
እናንተ ፍፁማን ሁኑ ...

ሐዲስ ኪዳን

# እኳና እኔ ...

እንደ በትረ ሙሴ ቀጥ ብሎ
እንቅርት በሚያፈርጥ አቀበት
እየተንቀጠቀጥኩ...
ደሞ ሊያስመልሰኝ ሲተናነቀኝ
በደመነብስ ላቤን እያጠጥኩ
ወደላይ ሽብቅ  ስንጉጥ

የግመል ሳቢዎች የሰልፍ ረድፍ ተከትዬ
አሽቆልቁዬ እንደቃባ እየተናጥኩ
የልቤን በሃሳቤ
እንደአልተንገረገበ አገሬ አተር ...
እያንቀራጨሁ በቀኝ በግራ ሳልጐጠጉጥ

ምክቴን ምልክቴን የክቴን
አንዱ ጋ እንደሳጋ ሻጥ አርጌ
ስፍራ አስይዤ ሳልሸጉጥ

ካለሁበት አባነነኝ
ማቄን ይዞ ያስቀረው
የግራምጣ ጋሬጣ ጉጥ

ላምባ አልቆባት ...
ጭልጭል እንደምትል የትል እሳት ቢጤ
አንጀት የራቃት ትንሽ የኩራዝ ብልጭታ
ከዕውነታ ጋር አላትማ ከራሴ ጋር አጋጭታ
አመላከተችን የወንድ በር ...

እናም...
የቆለኛውን የደገኛውን
የመልከኛውን የዘንገኛውን

አሳየችን አጀብ ወጀቡን ልኩን
አደብ ገደቡን ... እልኩን
አንዱ ሲተውን
አንዱ ሲከውን ... በውን!

የተቀማጭ ያ'ማጭ ረማጭ
የአልፎ ሂያጅ የመንገደኛው
ከመነሻው...
ለካ አንድ ኖሯል እንደኛው
እስከወዲያኛው?!

ልብ አልኩለት የነፍሱን ጥሪ
በመኀመድ በመዛመድ
ወድጄ ... እንደ'ርጥ ብ ሌጦ ተገድግጄ
ያለወንፊል ተገድጄ እስክጠመድ

ስንቱን አሰስኩት ስንቱን ሰሰትኩት
ስንቱን አዝግቤ ዘገቤ ሳትኩት?
ስንቱን ተረገጥኩ በስንቱ አገጠጥኩ
የስንት እጅ አየሁ ከስንቱ ማገጥኩ

ስንቱ...
ምኑ ይወጋል አምባው ሸለቆው
ምኑ ተዘልቆ ኮሶው እንቆቆው
ስንቱ እንዴት ታልፎ
ምራን ማነቆው ...

ጐማዬ ጐማ ...
ከፈለጉማ ...
ነጋቲ ቡላ ... አካም ነጉማ ...

ዓይን በመርፌ ቢወጉ በማያሳይ
ጥቅጥቅ ባለ ውድቅት ሌሊት
የኔ ቢጤ ...
ጽዋ መጠጫውን ዋንጫውን ሊያስሞላ
እየተጋፋ እየተካለበ ሲጥደፈደፍ

ሁሉም እንዳመሉ እንደሸመሉ ...
እንደአዳዩ እንደየአደላዳዩ
ደጅ እየጠና ሲጉደፈደፍ

ከሱፍ ፍትፍቱ እንደልክፍቱ
በወጪቱ አስጨልፎ
ጦም ሽሮ ሊገድፍ
ቢናደፍ

ያለ አቆልቋይ ያለአደጌር
ሰማይ ሙሉ ግብረ በላ ታድሞ
የከዋክብት አጋፋሪ ...

አጥብቆ
ባጭር ታጥቆ
እንደየአመጣጡ እንዳቀማመጡ
ሊያስተናግድ እያሳለፈ ሲያረግድ

በጉሮ ወሸባ
በሃይ ሎጋ ሽቦ
በጋሜ ሽብሸቦ ...
ዕለቱን በእልልታ በሆታ አድምቆት

ለጓድራው እኔን ነጥሎ
ቁልቁል ተክሎ አንጠልጥሎ
የጓዳህ የጐድጓዳህ አዋለኝ እያዋየኝ
በቂ ነው ብሎ የናነይን አብሽሎ
የጠላውን ቂጣ ደረቆት ... አሳየኝ ...

ደሞ ወደማላውቀው
ደሞ ወደማልጠይቀው ወሰደኝ
አስግሮ ድምበር አሻግሮ
ወዲያ ወዲያ ወዲያ

የዳማ የንዳማ ...
የቀልብ ቀዳማ ንሹን
እያበራየሁ እንድለየው ...
አቀበለኝ
የውድማ ያውድማ መንሹን

የሉሊትን የሉላቫንዱን ...
ያዝ አጥብቅ አለኝ መንዱን ...
ንቃ ጠብቅ አለኝ ሥር ግንዱን ...
ያንዱን ... የወንዱን

መለሰኝ ደሞ በውነ ውነ ...
በእናትና ልጁ በኩል ...
ምንም ሳልተነኩል ...
ተረከብ አለኝ ሒዳያውን ...
የወልዲያውን ...

ምናለ...
ዳዋ ውጦት ቢጨኸኝ
ሓሩር በልቶትም ቢከስም ...
እሱ እንደሁ ወትሮም እርም የለው
መቼም ቢሆን
ወዬው ነው የነፍስ ይማር የክፉ ቀን ስም!

ወቅት ገጥሞት ቢዘናፈል
እሰዬው ነው ...
እልል በቅምጤ ሲፈለፈል...
የሚያዚያ ምንዳ መህር ሲከፈል!

ቀና አልኩ ደሞ
እንደምንም ... የቀረኝን ላንቃርር
እየተፍረከረኩ
ካፈርኩ አይመልሰኝ ብዬ አኩርፌ
ሌምቦዬን ጥዬ እንዳላንቋርር
ሰማይ መሬቱን ላቃቅር

ቀና አልኩ ቀን አለና! ቀና
ይህን ጊዜ ነው እንግዲህ
በስተቶ በለሴ በበለሴ ...
ሥጋ መልበሴ ቀረና
ገላዬ ከላዬ ላይ
ጋመ ምጣድ ላይ
እንደወደቀ ቋንጣ
አፍንጫ እስኪቆርጥ ድረስ
እንደዲያብሎስ የሲኦል ክርፋት
ሳይጠበስ ቀረና ...

ደግ ነው ሰውነት ወረት ያቀብላል
ላፍላነት ያበላል ... ለአርጅና ያዘግባል
ስለነፍስ ያስብላል በበልግ
በታህሳስ ያጠግባል ፍልሰታ ያለዝባል ...

ደግ ነው ልጅ መሆን
በባላ ባልቶ በፊዬንዳ ጠጠር
የሚበር ሰብሮ እየሳቁ ማንጠር
ፈደሉ ገደሉ
ስንቱን ዞረው ዞረው...
መጡ ተመልሰው
በመከራ ጽዋ በቃል ተከልሰው

ሃዬዬ
እንደአባ ጨጓሬ ባምሣ እግር እየተሳቡ
እንደቅምቡርስ ከመዳህ
ያንድ አመት ክራሞትን
ቆፍጠን ብሎ ... ስትር ...
ሆምጠጥ አድርጎ አሞትን
ፍልቅቅ ነው እንጂ እንደቢራቢሮ
ባለፈ ልጅነት በቀረ ሲምቢሮ

በጐጆ መናጆ ...
ቢያፈጡስ ቢድፈጠፈጡስ ...
ቢመሽቅ ቢያደፍጥስ ...
ብጥስ ነው እንጂ ምናለ?
ብጥስ ሲሉ ቅንጥስ
ይማርህ አይባል ቀድሞ ሳያስነጥስ ...
መቸስ

አወይ ይኸ ድጓ
ወይ ይኸ ስንክሳር
ለካ ጉድ አለበት ... ሽርጉድ እስተ እሁድ
የሳር ክዳን ክፍክፍ ...
ሰባራ ሰንጣራው ጥሪ አለበት አሳር
በል በል
በል እስቲ ... እስቲ እንግዲህ...
ዓይኔን የኔን ያዬህ
    ና በለኝ ና ወዲህ ...
አርምሞ ...
ለከርሞ ሰው

ቶጳዝዮን እንደተሞላ ...
ፍኖቱ ሰባቱን ሰማዩ ከሚያካልል
ልዩ የምልአት የምትሃት ውቅያኖስ
ተነስታ ...

እንደሜሮን በውስጤ እየፈሰሰች
44 ጅማቴን እያረሰረሰች
ህያዊት ልባዊት ነባቢት ነፍሴ ጋ
የሰከነች ሠፊና ደረሰች!
   ሠላም ለኪ !

ያለድምፅ በልሳን
ያለቀለም ያለ ብራና በድርሳን
ከኢትዮጵስ
የበላይኛው ዕውነት አገር
አዘለቀችልኝ አንዳች ነገር
ለማንም የማይነገር ...

ሰው ካላዬ አያምንምና
ሰምቶ እንጀራ ያወጣ ...
ምጣድ ብቻ ነው ልባም
ምጐጐ ብቻ ነው ገምና

እንደሐጋይ ገላጋይ ...
የግንቦት ልደታ ጣይ ...
የጉስንታዬ ቅጣይ ...
የመንትያዬ ንጣይ
ፈታችልኝ ምስሉን ...
አሰረፀችብኝ ቃሉን
የዓለመዓለም ውሉን ...

ቢበድሏት ክሳ ታርቃ
በልቦና ተንሰራፍታ ...
እንቅልፍ ባይኗ ሳይኳል
ለቅፅበት ሳታሸልብ ...
ሣር ቅጠሉን የምትመግብ ...
ደሞ እንዳይጠግብ ደሞ እንዳይቃጣ ...
ቅጥ እንዳያጣ ...
እሳቱ አይጠፋ ምጣዷ
እንግዳ አይመትር ማዷ
አይጓደል ልማዷ
በትዕግሥትና በአርምሞ ካልሆነ በቀር
በጭራሽ አይታይም ጥማዷ ...

ከዚህ ወዲያ ያለውን
ታውጋችሁ ፋናዬ ሠፊናዬ

የሷ አንደበት ይጣፍጣል
ቃሏ ልብ ይመስጣል
ትንፋሿ ህቡዕ ይገልጣል
ትህትናዋ ደሞ
ጐራ እንደሰም ያቀልጣል

ፈገግታዋ እንደጡት እንገር
ሲያስቡት ያቅባል ያቅበጠብጣል
እጇ መድሃኒት ... አንገቷ ቅኔ
ምጥን ውጥኔ
ደጌ ድርብ ድግ
ዓይኗ እንደብይን ውሉን የማይስት
ጋሻ መካሻ ማር መሬት ርስት
ስሟ ወይን ጠጅ ግብሯ ሙጌራ
የገና ድፎ የባለአደራ

የዳመና አምድ ... የእረኛ በግ ለምድ
ራማ የሚያድም ... ጽዮን የሚያለምድ

ደብሯ ዱርቤቴ ... ከግራሩ ውስጥ
ሚመር የሚከፍል ከፍልፈል ከምስጥ
የቃል ብራና ... የሕይወት ቀለም
ቡራኬ እሚያሰጥ ... የምህረት ዓለም

የስብሐት ማህደር ... የካህናት መንደር
የደጀ ሠላም ... የዕምነት ዘቢደር

እኔም ልሰደር ... እሷም ትንደርደር
ባስሩ ቃላት ... ልደት ልደርደር!

የሱ ሥራ ማን ይመራመራ ...
«አድን»
አድን

Peaceful at most, "EVEN"
in the Worst "Civil - War"
የሰከነች ሠፊና!

# አንድምታ

አንድም ...
   መስማትህ ምን ያህል ማየትህ የት ድረስ
   እንዳዲስ ተሰርቶ ደሞ አድሮ ለመፍረስ
አንድም
   የኑሮን ቡቱቶ ዝተት የሚያስጌትት
   ልብ አለማለት ነው በልብ ውስጥ ክትት
አንድም
   ከሆነልህ ተማር ካልቻልክ ግን አስተምር
   መቀነስ ማባዛት ማካፈል ይመጣል አንተ ስትደምር
አንድም
   ሰው ራሱን ማየት ሲጀምር
   አይነ ኅሊናው ይከፈታል ልቦናው
አንድም
   ሕይወት ከመተንፈስ በላይ ሌላ የሚጠይቅ ከሆነ...
   መኖር ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አይገባኝም ...
አንድም
   በራሱ የቆረጠ
   በሞቴ ነው እንጂ በህግ አምላክ አይባልም!

እስቲ ከዚህ ጀምሮ እስቲ ይኸን መርምር
አንጥርና ቀምር ... መንገድህን አስምር
መድረሻህን ዘምር ... ትጥቅህን አሳምር
አውድማህ ላይ ከምር ...
ለምርትና ግርዱ
እንዳንተው አያያዝ ይወሰናል ቅዱ
እንዳነጋገርህ ይበየናል ፍርዱ
የትም ቢሰየሙ ምንም ቢጋርዱ!
ቃል ያልቅስ እንግዲህ
ቃሉ ተፈፅሟል!
ትንሳዔ የራስ ነው
በቀብር ትራስ ነው ...
አንጀት እንደራስ ነው!

ሱባዔ ምሽግ ነው
እሱም የለገመን እኛም የሸሸግነው

እንደሻው ይቆንጥር
እንደሻው ይመስጥር
ቁና ግን ...
መልክና ልክ አለ ... ቃል ያለ ጥርጥር
ምንም የማይቋጥር
ምንም የማያጥር የትም የማይነጥር

ቃል ግን አለ ለሁሉም
ይፋ ቢሆን ስውር
ዓይን ቢጋርድም ...
ልብ እንዳይሆን ዕውር
ወንድም ያሉት ወንድም
ሚዜ እንዳያስነውር
እንደአባቱ  ዘገር ፊቆ ሳይወረውር

ቃል ነው የሚያቆመው
የሚቆለምመው
እጁን ሳያሳርፍ
የጌታን ስጦታ በባሪያ እሚያዘርፍ

ቃልማ ግድ ነው ...
ግድና ወግድ ነው
ቃልማ ሕይወት ነው
የዕድሜ መታዘቢያ
«የአዳኝ» መስታወት ነው ...
ልስፈር ቢሉ አይመች
ከቶ እማይሰለች
አባቱን ሳከለ ... እናት ለመሰለች
ገና በቡቃያ ...
ማሳዋ ውስጥ ሁና ቀድማ ለበሰለች
ለልጅ ተንሰፍስፋ ነዳ ለከሰለች
ቃልማ ባህር ነው
የስሜት ውቅያኖስ የሰማዕታት ጀኖ ...
የነፍስ ሽምስያ ... የቅኔ ቤት ፋኖስ!

ቃልማ ወረት ነው
የሳት ዳር ጨዋታ ... የማጀት በረት ነው
እዚህ ያደረሰን ... ያላደፋረሰን!

ተስፋ አይደል ወይ ቋንቋው
ሳንቃውና መቃው
አንድም እንደራሱ
አንድም እንደምሱ
ጧት ማታ እሚያስወቃው
ወዶ እስከሚበቃው ...

ቃል ነው መቀነቱ
የነፍስ አብነቱ
ብቻ እሚገርም ነው ...
የራሱን በራሱ አጥቶት ይቋምጣል
ኮቴ ያዳምጣል
መልዕክተኛ ወርዶ በይፋ እስኪያበስረው
ደሞ እሰጥ ሌላውን
ይዶልታል ሊያስረው ...

ቃልማ ተውኔት ነው
የመድረክ አበጋዝ ...
ወደ መስክ የሚጓዝ ...
ሁለትዮሽ መጋዝ ...
እጅም አረም አይልጥ እግርም ወርዶ አይጠምድ
ወዴት ይደረሳል
ወዶ ያመጣውን ገፍቶ ሳያራምድ

ቃልማ ማተብ ነው
ዞሮ በሚያይ አንገት
በአደራ የካነው
መስቀል ለመሸከም
የበቃ የበቃው ኮበሌ ከመከም!

ቃል ሁኖ ተፈጥሮ ... ቃል ሁኖ መስክሮ
ቃል ሁኖ ሞት ሽሮ
በቃል ተሞሽሮ?
የፀና ዘለአለም ... ከቃል በላይ የለም
ቃልማ ፊርማ ነው
የሰለሞን ማህተም
እንደጉም ደመና እንዳሻው የሚተም
የአውራ ጣት ያመልካች ...
ያባቱን ... ቅባቱን ...
የናት ደም ግባቱን
ሌት ቀን የሚናፍቅ
እስኪያየው መጥባቱን

ጐህም በፈጀሩን ...
ጐርፍም መጅበርበሩን
በወዲያ በወዲያ የሚያነጋግሩን
በቃል ካልማገሩን ...

እንቅልፍና ኩርፊያ
ጩኸትና ግርፊያ ...
ቅኔና ቀነኖ
የቃል ልጅ ቃል ዝርፊያ ...
ሳይወድ እየመራ ያሳያል ማረፊያን!
ዘንቶ መደገፊያን!

ቃልማ ነፍጥ ነው
ያለጥይት አረር የተቀባበለ
ላያነጣጥሩት ...
እንደየአመጣጡ ቆሞ ተቀበለ...

ቃልማ ችሎት ነው
ከሳሽም ተከሳሽ ... ዳኛም ራስ ሆኖ
ለሦስት ተከፍሎ
ብይን እመስጠት ላይ
አለ ተፈልፍሎ

ቃልማ ሞገድ ነው
የቀላያት ገድል
ማዬ ሕይወት ቀድቶ ...ተቀባይ የሚያድል...

ቃልማ ህዋ ነው
የመንፈስ ጉልላት...
ላንዱ ሥነ ውበት ... ላንዱ ጥበብ ብዛት
ተንፍሳ ሳታድር
ብቅል ሳያብላት ...

ቃልማ ጽዋ ነው
በሱ ሥልጣን መንግሥት
ባንድ እምናነሳት ...
ዛሬ ያሳነስናት ...

አድሮ ለመግኘት ለለት የሰሰትናት
ለዕድሜ ዓለም ዘለዓለም
እንዳታውቅ ያፈናት ... ያላፈናፈናት

ቃልማ ሰንደቅ ነው
የቀለም ቤት ህብር
እንዲተጋ ...
የቃለ አብ ደብር ...
በክርስቶስ ግብር
ና! ሲባል እንዲያብር!

ቃልማ ከንፈር ነው
የጥርስ ባለሟል ...
ማር ቢያስቀምጡበት የሚገኝ ባመቱ
ሽልም የሚወጣ ... በአደብ በሹመቱ

ቃል ብቻ ነው ዕውነት ሁሌም መንደርደሪያ

እንግዲህ ቃል ያልቅስ
አገልግል ሳይለጉም ስንቅ ሳያስጠቅስ
ዕንባ እንዳለው ይውረድ
ልብ እንዳለው ይፍረድ
ፍቅር እንዳለው ይብረድ
ሰም እንዳለው ይልመድ

ደሞም ሞያ ካለው ...
በማያውቀው ዓለም በፍቅር ተነጥቆ
በሸረብነው ሴራ ... ባተትነው ማነቆ
ወዶ እጁን ይሰጣል
ልቡን ባጭር ታጥቆ!

ቃልማ ሁሉም ነው
አሉም ቤት የሉም ነው
የሉም ቤት አሉ ነው
ቃልማ ሁሉም ነው!

... በቃሽ ሠፌና
እኔ ልተርትር
አሹቅ አቅርቤ ቀፈት ልቀብትር ...

ሠፌና በቃሽ
ላንቺ ለራስሽ ቃሉ ነው መስቃሽ
የፍቅርሽ ነቃሽ ...
የክብር ቦታሽ ... አንቺን ናፍቆ አልቃሽ
ለዛሬው በቃሽ ...

እኔው ላዘብዝብ
እኔው ልወትውት
እኔው ልዛብር ...
በሞቴ ገዳይ ... ስሞት እንዳብር!

እንግዲህ ቃል ያልቅስ
ይቀስቀስ ...
ካስፈለገው ያጥቅስ
በእጁ ነው ለሁሉም
ያልፈቀዱት አፀድ
መቸም መቸ ቢሆን ቀድመው አያፈሉም
እንግዲህ ቃል ያልቅስ
    ደረት እየጣለ ፊቱን እየመታ ...
ገበያ አምሮት እንደሁ ... የረፋድ ሸመታ

ደሞ እንደሐምሌ ጐርፍ
ይውሰደው መልሶ ...
አዙሮ እስኪያመጣው
የዘሩን አልሶ ...

እሱማ ያዝንበው
ቃል እንጂ የሰማይ ...
የቅኔው መርጌታ አሉ አይደል እነማይ

ምነው አምና ሞቼ
ታች አምና ብቀበር
አረፍቆ ደፍቆ ... ሳይበቁ ለቀንበር
ቄራ ወርዶ ለቁርጥ
ሲያንሰው ነው ምንጊዜም ...
ለኔ ቢጤው ... እርጥ!

ዶሴው ባይዘለቅ የመለኮት መዝገብ
እዛ ላይ ነበረ ... እያለሙ ማዝገብ
ሰው እየተራቡ ... በሃሌ ለመጥገብ ...

ስዘጌ ኪዳነምህረት ... ጣና!
Plesure is:-treasure of no measure!
ወጽሐስቃ!

«ልጄ ሆይ ... ቃሌን አሳጥፍም ...!»
’ርግቤ ሜላ ...

# የእምዬ ...
# የልደት ስጦታ ...

ንፅህናን በድንግልና
   ልዕልናን በብቃት ሳላጐናፅፍህ
እንዴት ልፀየፍህ?

ዕውነት ያንጀት ልጅ ነህ
ክቡር መልካም ህብር
ከማንም ከምንም ለእንጀራ ’ማታብር
የትንሳዔ ግብር ...

ውድ ነህ ደርባባ
አጣሁ ነጣሁ ብለህ መቸም የማትባባ
ያ ናፋቂ ልብህ ...  ያ ቀዛፊ ቀልብህ
ሳይዘራ ሳያጭድ ... ይደልባል ድልብህ ...

እንዳትዘናጋ
ሁለት ስታወጋ ...
በምላስ እጅ ነው የሰማይ ቤት ዋጋ

ስንፍናና መርሳት ካልተጣቡህ በቀር
ምነው ሠላም አይሰጥ ... ከተገኘ ማፍቀር

መቸም አትጠርጥር ... መቸም አትገምተው
እስኪበቃ እንጂ ነው ... የታል አይቶ መተው

ውለጂኝ ያልከኝ ለት
እንዴት እንዳዘንኩኝ
እንዴት በታደልኩኝ

አንተማ ጥንድ ነህ ... የግምሻ ለት እርሻ
አንተማ ጥዑም ነህ ... የፍልሰታ ጉርሻ

አንተማ ፍቅር ነህ ... የደናግል ፀዳል
አንተማ ቅኔ ነህ ... ቃልህ ቀን ይወልዳል

አንተማ የኔ ነህ ... የልቤ እንደራሴ
በባቢሎን ሸንጎ ... የክፉ ቀን ዋሴ

ፀጋ ልበስ እንጂ አንተን ማን ከልክሎ
ራሱን ለቻለ ራሱን አክሎ

ስሜን ልታስከብር በቆምክበት ሁሉ
ከማንም አይደለም ከኔ ጋር ነው ውሉ

የናትን የጣር ምጥ ... የፍቅሯን ትኩሳት
ስትቆም ስትቀመጥ ... ምንጊዜም አትርሳት
ከልብህ አስታውሳት ...

ውዳሴ ማርያሜን እስክትፅፍልኝ
የተረፈ ዕድሜህን ... ቤቴን ደግፍልኝ
የፅላቱን ጉዳይ ... የቅኔውን ነገር
መቸም ችላ ብለህ ... ወንዝ እንዳትሻገር

«ለእናትና ልጁ» - ወልድያ!

«የሰው ልብ ስሰው ይታያል ...»
ምሳሌ ሰለሞን...

# ምነው አንተ ሙሽር

አገር በራብ ሲታለብ
መፃጉኡ ተጣሞ ነብሱ ስትንገበገብ
ትቢያ ልሶ ሞት ሲደፍቅ
ከብናኝ አፈር ሊደባለቅ ...
እናት ብላቴናዋን ...
ከደረቷ ሳንቃ ስትነጠቅ
አባት በሰቆቃ ምርቅ ሲታነቅ ...

ምነው አንተ ሙሽር ...
ባለሞሰብ ባልንጀር ...

ማንባትህ ቢቀር ማብላቱ
ምዝጋ እጅህን መዘርጋቱ ...

ትደለቅብኝ ... ትዘፍንብኝ
አይነጋ መስሎህ ሌቱ ...
አይፈጀር ...
አይገሰስ ፅልመቱ ... ከንቱ ...

መልዓከ ሞት ሲያካበኝ
ነፍሴን ከሥጋዬ ሊነጥቀኝ
ቀን እስኪጥለኝ ጠብቀህ
ማዘልሽን ...
አንቀልባሽን ልግዛሽ ትለኝ ...

ምነው ልጄ
ማዘሌንማ ለምን ...
የናቴን የማዬን ጥሪት ...
ልጄን ውዴን የማዝልበት
የኔም የናትነቴ ምልክት ...

ነፍሴን ግዛት በቁርጡ ...
መቸም እርም የላችሁ እናንት ...
ያኔ ለመጨረሻ ሳካት
ለማትሞተው ሚስትህ ስጣት
ማን ደፍሮት ... የናንተን ቤት
እሷን እንደሁ ሞት አይነካት

እኮ የጨው ቅሌንም ጨክነህ ...
የሴት ወጌን ማረጌን ...
ስም አልባ አርገኸኝ ልትቀር ...
አብረህ ልትቀብር ሞያዬን ...

እምቢዬው ...
እኔስ እምቢዬው ...
ይብላኝ ላንተ ለቁርጥ አልባው
ቆርጠህ ጨክነህ ለማታውቀው
እኔስ  ባለቁርጥ ነኝ
በቁርጤ ጠፋሁ ቢሻው ...

መግደልም አውቅ ነበረ
ዛሬም በሞት ተፈተንኩ
ይብላኝ ላንተ ለቁርጥ አልባው
ይብላኝ ላንተ አበስኩ ገበርኩ!

ለቁራኛ ውለታ - ወሎ!
1977ዓ.ም.

# እግዚኦ

ከእግዚኦ በቀር …
ሞቼ
ቀባሪ አጥቼ
እላይ እታች የምላጋ
አስከሬኔ ተኝቶ ባልጋ …
አለሁ እየመሰለኝ …
ለካስ በድን ኖሬአለሁ …
እንደጠይብ ካፊር አቡኩቶ …
ቆርሶ … እየኮላ አበሰለኝ

መሻትህን ... ግንባርህ ትምራት ...
ተግባርህን ሰውነት ይሙላት ...

**የራስ ቤቶች**

መተሳሰፉ የቀረችለት
ሃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው

**ልበአምላክ ዳዊት ...**

# የባለ ቅኔ ምህላ!

የጐደለኝን ሳላውቀው የጠፋኝን ሳልረዳ
እንደተለኮስኩ ... እንደተጋፈጥኩ
እንደተታኮስኩ ... እንደተፋጠጥኩ
አለሁ ...
ሳንጃ ባፈሙዝ ተቀላቅዬ ስመሻለቅ
በቁሜ እንደተራዳ ...

ልንገብገብ እንጂ ልቃጠል
የከርሞ ሰው እስኪለኝ ...
ክፉ ጥፉ ...
ጠፉ እስኪመነጠር ...

አላውቅበት መመሳሰሉን ...
አይሆንልኝ ቆርጦ መቀጠል
አልችልበት ደፈጣ ...
እንደቆላ እባብ በደረት እየተሳቡ ማነጣጠር

መቸም ያልተብራራልኝ
ምንጊዜም ያልገራልኝ
ይኸ ምስጢር የሚሉት ሰጠር ነው
በጧት በማታ ያልጠረጠርነው
በምንተዳዬ ያጠርነው!

የማይሰፈር ስለካ
ከማይቀመስ ስፎካከር
እሰጥ አገባ ስጐሰጥ
ጉንጭ አልፋ ስከራከር

እየመሸ እየነጋብኝ
ዓይኔ እያዬ ዘጋብኝ!

የሰጠኸኝን እንዳስተውል ጌታ ሆይ
ተለብልቦ
ታርቆ መቅናት ተስኖኝ
እንደቆሪ ውሃ እንዳልዋልል
መሃል ቤት እንዳላወላውል ...
የዓይነ ህሊናዬን ጉድፍ አንስተህ
የነፍሴን መታዘቢያ ወልውል!

የጤናዬን ...
የጤናዬን ነገር አደራ
የዘፍጥረቱንም ጭምር
ችዬ አልቀምም ብቻዬን ...
ያለፅንፈ ዓለሙ ድምር!

ችዬ አልችልም ብቻዬን
አልፀናም ባንድራሴ
ድሃ አደግ ምን ቢተባ
አይደምቅም እንደእንደራሴ

በእምርታህ ... በይቅርታህ ማርከኝ
እንደእዝነትህ ... እንደቸርነትህ ባርከኝ

እንኳን የጐረስኩት ... የቆረስኩት እያነቀኝ
ስርቅታው እያሳቀቀኝ
አቁማዳ ሲፈታ እንደተያዘ ቀጣፊ
እንዳልበላ እንዳልዘራ
በቅሌት እያደቀቀ ... ሰለቀኝ!

ኤሎሄ ኢላሄ
ምሉዕ በኩሊሄ
ዕለተ ሞቴን አታስረሳኝ
ወንፊት እንጂ ፊት አትንሳኝ

እንደፊኛ ተወጥሬ ... በሽንገላ ታጥሬ
ያላቀበጠጠኝን የሰው ላላማ
እምብስ ቀስቁሼ ሳራግብ ...
ቁጭት እንደዙር ዝናር ታጥቄ
ቁልጭት እንደወጨፎ ከማነግብ ...

አታደናክረኝ ...
ስቼ ተርሸቼ
ተሰንክዬ እንዳልረግብ ...

አፋፋኝ በእቅፍህ ሙቀት
አውጣኝ ከሰንበት ስደት
ሰውረኝ «ከነይ ነይ» በቀት

ያዝልኝ አዛን ...
ያዝልኝ በጠበሉ እዛው
ከናጅናዛው ...
ያዝልኝ እዛው በርቀት ...

ምንም ይሁን ...
ምንም ይሁን ምንም ምንም
የፍቅር ሽልማቱን ...
በሰላም ካላጐናፀፈ
እንኳን ለዘለዓለም ዓለም
ላፍታ ... ለእፍታም አይታመንም!

ጌታ ሆይ ...
ቃለ ህይወትን አሰማኝ
በመላዕክት ዝማሬ አጅበህ
ፅርሓ አርያምን አሳየኝ
በህያዋን ክብር
በትጉሃን ስብሐት ተከበህ!

ምላሴን ኩን አድርገህ...
አጣፍጥልኝ ሁለመናዬን
ለምለም ነው ብዬ
ከማንም ጋር ስዳይ ውዬ
እንደአባያ ሣር እንዳልነጭ
ምሬሃለሁ በለኝ በድንግል ...
ዘለዓለማዊነት ...
ከምንጩ በውስጤ እንዲመነጭ!

መቸም ቢሆን ልጅ ያለአባቱ
ቁምጣው እንጂ ... መች ጉልበቱ
ስሜቱ እንጂ ... መች ምጥባቱ ...

አንድዬ
ቤት ለእንግዳ በለኝ በማምላክ
ቤት እምቦሳ እንድል በምሥራቅ በር
ከጥሬ ዱለት አላለፈም
የኔ ያልኩት ምላስ ሰምበር!

ጥም ለቆብኛል በጥና
አቃጥሎኛል የዕምነት ራብ
ቀላቅለኝ ከብሉይ ማህቶት
አቅርበኝ ወዳንተ ምኩራብ ...
ጠብቀኝ ከማላውቀው
አውጣኝ ከፍዳ ናዳ ...
መልዓከ ሞት ነፍሴን እንዳይነጥቀኝ
ሳልታጠብ ሳልታጠን ...
ቦዥ ሳልሰናዳ ...

ስደት ንዴት ሰለቸኝ
አጒበጠኝ የኑሮ ሸክሙ
አስረዳኝ
በሀ ግዕዝ ሁ ካዕብ
በአቡጊዳ ሂውዞ ...
በመልዕክተ ዮሐንስ ...
ሐዋርያ ወልደዘብዴዎስ ... ንዜንወክሙ

ገላግለኝ ከሥጋት ሥጋት
ከሸክላ ከሸክላ መላ ...
አንተ እንጂ ማን አለኝ ሌላ ...
አንተ እንጂ ... ከዚህ በኋላ!

የንጋት አጥቢያ ጒህ መቅደድ
በኔ መላ እየመሰለኝ
ስንት ዘመን አንጠራውዞ ...
ስንት ወቅት አብሰለሰለኝ

ስሉስ ባዛውር
ዕድሜ ሰጥቶ ... እያገላበጠ ጠብሶ
በቃህ ሲለኝ ነው መሰለኝ
አበሰለኝ!
ክብር ለሱ ... አዎ በሰልኩ
ጥንት ... ጥንት በልጅነት የተማርኩትን
ያመንኩትን ... የታመንኩትን
ከለስኩ ...

ክፉ መሻቴን ምኞቴን ኮለስኩ
ዘንጌን ምርኩዜን ይዤ
የልቤን ሸለፈት ገረዝኩ …
ሃሌ ሉያ ቶበትኩ … አማተብኩ …
የጐጆዬን ቀዳዳ ወተፍኩ
ጐታ ጐተራዬን መረግኩ …
ስብሐት ለእግዚአብሔር ብዬ …
ያለፈውን በምስጋና አሳረግኩ!

ዝም ብዬ ስቆዝም
ዝም ያልኩ የምመስል ዘገምተኛ
የዱዳ ስሞተኛ …

ሳልናገር ሳልጋገር
እ … የሚለኝ አገር …
ነክህን ነው እንጂ እንግዲያ
የምን ወክ እንዲያ ወክ እንዲያ
የምን ወክ እንዲህ … ወክ'ንዲህ

በብርዕ በቀሰም
በወርቅ በሰም …
በአዲስ ራዕይ … በልዩ ምዕራፍ
እንግዲህ ዘራፍ …

እናቴ ጽዮን
ወንዜ ግዮን
ወፌ ከራድዮን …

እህና … አዎና!
በቀኙ … ካልባረከ
በግራው ካልማረከ
ምን ያደርጋል እንቶ ፈንቶ
ትርኪ ምርኪ በተረከ፡፡

አሳታሚዋ - ስስ ገጣሚው፡-

# ደብዳቤ ለ«ሲኦል»

ጉኖዬ - እንዴት ናችሁ? ከብቱስ? አዝመራውስ? ፀሀይዋስ? ነፋሱስ? እንደው ባጠቃላይ መላ ተፈጥሮስ እንደምን ከርመዋል?

ይኸውልሽ አዲሱን አመት «በይቅርታ» ተቀብለነው እንከውናቸዋለን የተባባልናቸውን ነገሮች ሁሉ አስጥሎ ሞት ወሰደኝ፡፡ መረጠኝ፡፡ ብቻ እኔም የተባበርኩት ይመስለኛል፡፡ ምን ላድርግ? ለምንስ አልተባበረው?

በምድር አብሬያችሁ እያለሁ ገና ወደናንተ ስቀላቀል አመጣጤም አስገራሚ ነበር፡፡ እናቴ ጠላ እየሸጠች ነው ያሳደገችኝ፡፡ አባቴ በህይ-ወት ቢኖርም ብዙ አላውቀውም፡፡ አብሮኝ አልኖረም ገና ዳቦ መንከስ ስጀምር አንስቶ ራሴን በራሴ እያስተዳደርኩ፣ ሊስትሮ እየሰራሁ አስኳላ ቆጠርሁ፡፡ ፈረንጅ አፉን፣ አማርኛውን ትግርኛውን፣ አፋርኛውን ለማቀላጠፍ ጊዜም አልወሰደብኝ!

በምድር ስኖር ለግሌ ብዬ ያከማቸሁት ምንም ነገር አልነበረኝም፡፡ እንግዲያውስ በእርዳታ ድርጅት ውስጥ ከመስራት እስከ ኢህዴን - ብአዴን - ኢህአዴግ ድረስ ታገልኩ! በግሌ ያገኘሁት ነገር፣ መናቅ፣ መዋረድ፣ ለዓይን አለመሙላት ሆነ፡፡ ዋጋና ችሎታዬን ያወቁና የተረዱ «ጓዶች» እንኳ የሚፈልጉኝና የሚያስፈልጉኝ «የድል በዓል» በሚል ሰበብ ቅኔ እንድቀኝ፣ ግጥም እንድገጥም፣ በአጭሩ የድግሳቸው አድማቂ፣ ተራ «አዝማሪ» የሆንኩ እስኪመስለኝ መጎሳቆል ተሰማኝ፡፡

ይህንን ይሁን ብዬ ጓዶቼን ፈትቼ፣ ህዝቤን አምኜ፣ ችሎታዬን ለዘፋኞች ልስጥ አልኩና ተነሳሁ፡፡ ገበያው እጅግ የደራ ከመሆኑ የተነሳ እንኳን ሌላ ነገርሽን ከዓይንሽ ላይ ኩልሽን ሊሰርቁሽ የሚችሉ ሰዎች የበዙበት ሆነ፡፡ ይህን ትልቅ የገበያ ስፍራ ለመቀላቀል ስንት አሳር እንደቆጠርኩ ዛሬም ሳስበው ይዘገንነኛል፡፡ በቃ የስልጣናቸው የመጨረሻ ዳር ድንበር አሁን ትዝ አለኝ! «የኢኮኖሚው ባለቤት የፖለቲካውም ዋና ባለቤት» እንደሆነው ሁሉ የስራው ባለቤቶች ነጋዴዎች ብቻ ሆኑ፡፡

«እኔ እበላ - እኔ እበላ» እያሉ ከሚሻሙት ጋር ለጨው ለበርበሬ፣ ለውሎ ላዳሩ እንኳ ብዬ አብሬያቸው ለመቆየት አቃተኝ፡፡ ይልቅ ጠጋ ያሉኝ ጋር በማርያም መንገድ፣ በማተብ፣ በክርስትና ለየግል ተነጋ-ግረን፣ ቀኑን አሳምረን፣ ዱአ እያደረግን፣ ተፈጥሮንና ፈጣሪን ሳይቀር

እያፋጠጥን አብረን ጎጆ ልንወጣ ሰርተን ፈረንካው ሲገኝ አይኔን ለማየት 'ንኳ ይፀየፋሉ:: አልፈው ተርፈው ብኩርናዬን ሳይቀር እንድሸጥላቸው ሁሉ ጠየቁኝ::

ጉኖዬ - እንጂማ እኔ ወንድምሽ፣ ጥንቅቅ፣ ጥንፍፍ ያልኩ ጀግና ነኝ:: ቅዱስም ንጉስም እሆናለሁ አላልኩሽም ነበር? ካልሆንኩ ኋላ ትታዘቢኛለሽ:: ለጊዜው «ብርዕ በደም ዕንባ»፣ «አንተሙሽር»፣ «ከመንበርህ የለህማ»፣ «ከነዓን ነው ዘንድሮን» ግጥሞቼን ብቻ 'ንኳ ልጥቀስልሽ:: እያደር እንደምትሰሙኝ ተስፋ አለኝ፣ ታዲያ እኔ እንዴት አባቴ አድርጌ ብኩርናዬን ልሸጥ!?

ወደ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ግጥሞችን፣ ሁለት ቲያትሮችን (ደጀ ሰላምንና ግምሻን) እና በርካታ ዘፈኖችን ሰርቻለሁ:: ውድነሽ በጣሙ፣ አማራ ነኝ ያውም ደሜ አረንጓዴ (ራዲዮ ፋና ሳነበው ቀድቶኛል ጠይቀሽ ስናፍቅሽ ደግመሽ ስሚው:: «ከመንበርህ የለህማ»ም ኢትዮጵያ ሬዲዮ ነበረ:: ...እና ታዲያ ጉኖዬ አንቺ ግን «ጉዳዬ ሞተብኝ!» ብለሽ በጣም ያዘንሽው ለኔ ነው?

ይልቅስ ለሁሉም ሰው ይቅርታ ማድረጌንና ይህ አካሄድ በኔ ቢያበቃ ደስ እንደሚለኝ ንገሪልኝ:: የሰራሁበትን፣ ህቄን፣ ገንዘቤን አንድጂ ብሞቀው 'ንኳ የሚያገባው እንዳልነበረ ደሞ መንገር እንዳትረሺብኝ!

ቀብሬን ለማከናወን በእጅጉ የተባበሩሽን ጓዶቼን፣ መላ ጓደኞቼንና ቀባሪዎቼን አመስግኝልኝ:: በምድር ሳለሁ አብረን የተሸከረከርናቸው ሰፈሮች የማስታውሳቸውን የምድር ጀለሶቼን አለምገናዎችን፣ ተረት ሰፈርን፣ ፈረንሳይ ለጋሲዎኖችንና ስድስት ኪሎዎችን፣ ቅድስተ ማርያሞችን፣ ዶሮ ማነቂያዎችን፣ ሀብተጊዮርጊስ ድልድዮችን፣ አጠና ተራዎችን፣ ሰንጋ ተራዎችን ... መላውን ወዳጆቼን እንገናኛለን እኔ አልቀርጥም ተስፋ! ብሏል በይልኝ::

ከልጆቼ ቀጥሎ የወለድኩዋቸውን ስራዎቼን እያስታወሳችሁ «አደራ ልጄን አደራ» የሚለውን የብፅዓት ስዩምን ዘፈን እንድትሰሙልኝም ጋብዣችኋላሁ:: ጉኖዬ - ሆድ ሲብስሽ ደግሞ የህና ሸንቁጤን «ሆዴ ባለአብሾ»ን ስሚ:: በጣም ደግሞ የአበበ ተካን «ወፍዬ»ንም ስሚ!

ስሚ 'ንጂ አንድ ቀን «ያንተን የተለያየ ዘፈኖች መደዳውን ዛሬ አራት በኤፍ ኤም ሰማሁ ብለሽ» በልብሽ ያጨበጨብሽልኝን ዕለት አስታውሼ ምን ትዝ አለኝ መሰለሽ! ያወጣሁላቸው ስሞች! ታምራት ሀኪሜነሽ፣ መሰረት ጉምጉም፣ ፀደንያ ገዴ፣ ብፅአት ገዳዬ፣ ሸህ አብዱ ሀዋብስል ኧረስንቱን አድምቄዋለሁ አያ! ምንስ ቢሆን ሙሉጌታ ተስፋዬ ወዲ ሀለቃይ! ተጋዳላይ ነኝ'ኮ!

በነገርሽ ላይ መስፍን አሸብር የሬዲዮ ፋና ጋዜጠኛ የነበረውን እዚህ አግኝቸው ወግ ስንገምጥ እግረመንገዱን በጨዋታ መሀል ትዝ አለውና

«ለመሆኑ የኔ ግጥሞች ታተሙ ወይ?» ብሎ አይጠይቀኝ መሰለሽ? ደንግጬ! እኔንጃ፣ ብቻ አንድ ሰሞን ጉኖ ዘበናይ ሬዲዮ ፋና ሊያሳት-መው ነው ብላ ደፋ ቀና ስትል ትዝ ይለኛል አልኩት! ተስፋዬ ካሳንም አግኝቸው ነበር፣ ያለኝን ግን አልነግርሽም፣ ሆድሽን ይብላሽ።

ጉኖዬ - በይ ይብቃ! «ወሬ ቢበዛ ባህያ አይጫንም!» ግን ደግሞ ምነው በኔ! እኔ ነኝ አህያ? አህያ ነው እኔ? ለማንኛውም ሁላችንም ተገናኝተን እስክንፋጠጥ ሰላም ሁኑልኝ!» ይላል ሰሞኑን የደረሰኝ ደብዳቤ!

ጥቅምት 1997 የታተመና ከጋዜጣ የተወሰደ

